አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# [illegible] ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት የመ[illegible] [illegible]ረጃ ትምህርት ቤቶች የሰባተኛ ክፍል የአማ[illegible] ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ግም[illegible]

በ
ሰርጉ ይማም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋካልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ግምገማ

በ

እጅጉ ይማም

CLEARED
FROM
ILS LIBRARY

የካቲት 2003 ዓ.ም

# በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ግምገማ


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋካልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


ለተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር

ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

እጅጉ ይማም


የካቲት 2003 ዓ.ም

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ፋካልቲ

## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ግምገማ

በ

እጅጉ ይማም

የካቲት 2003 ዓ.ም

CLEARED FROM

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ስም ............................ ፊርማ ............................

አማካሪ ............................ ............................

ፈታኝ

ILS LIBRARY ADDIS ABABA

የካቲት 2003 ዓ.ም

# ም ስ ጋ ና

ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው በየጊዜው የማቀርብላቸው ጽሁፍ በጥልቀት በመፈተሽ ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ፣ የጥናታዊ ጽሁፍን ምንነትና አከናወን በሚገባ እንድገነዘብ ለረዱኝ ለአማካሪዬ ለዶክተር  ብርሃኑ ማቴዎስ ላቅ ያለ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው። አቶ ግርማ ገብሬም ዶክተር  ብርሃኑ ማቴዎስ በዋና አማካሪነት ከመመደባቸው በፊት ያማክሩኝ ስለነበር እና መጽሀፍ ስላዋሱኝ አመሰግናቸዋለሁ።

ለጥናቱ አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ ላደረጉልኝ ለደብረ ብርሃን ትምህርት ጽህፈት ቤት ባለሙያዎች ፣ የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሙከራ ለተደረገበት የሶሬሳ አፀደ ህፃናት እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሳነ መምህራን ፣መምህራንና ተማሪዎች፣ ጥናቱ ለተካሄደባቸው ሶስት ትምህርት ቤቶች ርእሳነ መምህራን ፣ ዩኒት አስተባባሪዎች ፣ ለሰባተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ፣ መጠይቁን ለሞሉልኝ የየትምህርት ቤቶቹ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ፣ በክፍል ውስጥ ምልከታ በረዳትነት ለተባበሩኝ (ተስፋዬና ውብሸት) ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

የኃይለ ማርያም ማሞ ትምህርት ቤት ዲጂታል ካሜራ በመስጠት ፣ የዚሁ ትምህርት ቤት የአይ.ሲ.ቲ ቴክኒሻን ባለሙያ (ሚኪ) ምልከታውን በመቅረጽ ፣የደብረ ብርሃን አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪዎችን የፅሁፍ መጠይቅ በማባዛት፡ የኔዓለም ተስፋሁን፣ ሙላት ፈንቴ፣ሰይድ መሀመድ እና ጫንያለው ፈንታዬ መጽሐፍ በማዋስና አስተያየት በመስጠት ስለተባበሩኝ ለእነሱም ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም ትምህርት የቀሰምኩበት እንዲሁም ለጥናቱ የሚያስፈልገኝን ገንዘብ በመመደብ የተባበረኝ ስለሆነ ምስጋና ይገባዋል።

# ማውጫ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|
| ምስጋና | i |
| ማውጫ | ii |
| የሰንጠረዥ ማውጫ | v |
| አጠቃሎ | vi |

## ምዕራፍ አንድ ፡- መግቢያ

| | | |
|---|---|---|
| 1.1 | የጥናቱ ዳራ | 1 |
| 1.2 | የጥናቱ መነሻ ችግር | 4 |
| 1.3 | የጥናቱ ዓላማ | 5 |
| 1.4 | የጥናቱ ጠቀሜታ | 6 |
| 1.5 | የጥናቱ ወሰን | 7 |

## ምዕራፍ ሁለት ፡- የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

| | | |
|---|---|---|
| 2.1 | የቀደምት ጥናቶች ቅኝት | 8 |
| 2.2 | የመናገር ክሂል ፅንሰ - ሀሳብ | 10 |
| 2.3 | የመናገር ክሂልን የማስተማር ዓላማ | 10 |
| 2.4 | የመናገር ክሂል ተግባራት ባህርያት | 13 |
| 2.5 | የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት ዓይነቶች | 14 |
| 2.5.1 | የመረጃ ክፍተትን መሙላት | 15 |
| 2.5.2 | ጨዋታዎች | 16 |
| 2.5.3 | ችግሮችን አፍልቆት መፍትሄ መሻት | 16 |
| 2.5.4 | ታሪክ መናገር | 17 |
| 2.5.5 | ሚና ጨዋታ | 18 |
| 2.5.6 | ውይይት | 19 |
| 2.6 | የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችና ችግሮቹን ለማስወገድ የሚረዱ ተግባራት | 21 |
| 2.6.1 | የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች | 21 |
| 2.6.2 | የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ የሚጠቅሙ ተግባራት | 22 |

2.7 የክፍል አመራር ---------- 23

2.7.1 በመናገር ክሂል አቀራረብ የክፍል አደረጃጀት ---------- 24

2.7.2 የመምህራንና የተማሪዎች ሚና በመናገር ክሂል አቀራረብ---------- 25

2.7.2.1 የመምህራን ሚና ---------- 25

2.7.2.2 የተማሪዎች ሚና ---------- 31

2.8. የመምህር-ተማሪ ተራክቦ ውቅሮች ---------- 32

## ምዕራፍ ሶስት ፡- የጥናቱ ዘዴ

3.1 የናሙና አመራረጥ ---------- 33

3.1.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ---------- 33

3.1.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ---------- 34

3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ---------- 34

3.1.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ---------- 34

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ---------- 35

3.2.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ ---------- 35

3.2.2 የፅሁፍ መጠይቅ ---------- 37

3.2.3 ቃለ - መጠይቅ ---------- 38

3.3 የመረጃ አተናተን ሂደት ---------- 39

## ምዕራፍ አራት ፡- የጥናቱ የመረጃ ትንተና ውጤት

4.1 የመናገር ክሂል አቀራረብ ክንውኖች የመረጃ ትንተና ---------- 40

4.1.1 የአቀራረብ ደረጃ ክንውኖች የመረጃ ትንተና ---------- 40

4.1.2 የልምምድ ደረጃ ክንውኖች የመረጃ ትንተና ---------- 47

4.1.3 የአፍልቆ ደረጃ ክንውኖች የመረጃ ትንተና ---------- 54

4.1.4 የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ክንውኖች የመረጃ ትንተና ---------- 60

4.2 የመምህር - ተማሪ ተራክቦ ውቅሮች የመረጃ ትንተና ---------- 63

4.3 የመምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ግንዛቤ የመረጃ ትንተና ---------- 66

4.4 በመናገር ክሂል አቀራረብ የተከሰቱ ችግሮች የመረጃ ትንተና ---------- 68

## ምዕራፍ አምስት ፡- ማጠቃለያና አስተያየት


5.1 ማጠቃለያ ---------------------------------------------------------------------------------------- 75

5.2 አስተያየት ---------------------------------------------------------------------------------------- 78

ዋቢ. ፅሁፎች ---------------------------------------------------------------------------------------- 80

አባሪ ---------------------------------------------------------------------------------------- 82

# የሰንጠረዥ ማውጫ


| ርዕስ | | ገፅ |
|---|---|---|
| ሰንጠረዥ አንድ፡- | በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች ፣ መምህራንና ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛትና የናሙና መጠን መግለጫ | 35 |
| ሰንጠረዥ ሁለት፡- | የመምህራንን የአቀራረብ ደረጃ ክንውኖች የሚያሳይ ሰንጠረዥ | 41 |
| ሰንጠረዥ ሶስት፡- | የፅሁፍ መጠይቅ የሞሉና ያልሞሉ ተማሪዎችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ | 43 |
| ሰንጠረዥ አራት፡- | የቅድመ- መናገር ተግባራት አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ | 44 |
| ሰንጠረዥ አምስት፡- | በጥናቱ የተካተቱ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መግለጫ | 45 |
| ሰንጠረዥ ስድስት፡- | የመምህራንን የልምምድ ደረጃ ክንውኖች የሚያሳይ ሰንጠረዥ | 47 |
| ሰንጠረዥ ሰባት ፡- | የልምምድ ደረጃ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ | 50 |
| ሰንጠረዥ ስምንት፡- | የመምህራንን የአፍልቆት ደረጃ ክንውኖች የሚያሳይ ሰንጠረዥ | 54 |
| ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- | የአፍልቆት ደረጃ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ | 57 |
| ሰንጠረዥ አስር፡- | የመምህራንን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አቀጣጥ የሚያሳይ ሰንጠረዥ | 60 |
| ሰንጠረዥ አስራ አንድ፡- | የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ | 61 |
| ሰንጠረዥ አስራ ሁለት፡- | በመናገር ክሂል አቀራረብ የመምህራንና የተማሪዎችን ተራክቦ ውቅር የሚያሳይ ሰንጠረዥ | 63 |
| ሰንጠረዥ አስራ ሶስት፡- | የመምህር ተማሪ ተራክቦ ውቅርን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ | 65 |
| ሰንጠረዥ አስራ አራት፡- | በመናገር ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተከሰቱ ችግሮችን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ | 70 |
| ሰንጠረዥ አስራ አምስት፡- | ተማሪዎች በመናገር ክሂል ተግባራት ያልተሳተፉበትን ምክንያት የሚያሳይ ሰንጠረዥ | 71 |

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በደብረ ብርሃን ከተማ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂልን እንዴት እያቀረቡ እንደሆነ በመፈተሽ በአቀራረቡ የታዩ ችግሮችንና የችግሮቹን መንስኤዎች በመለየት የመፍትሄ ሃሣብ ማቅረብ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በአፄ ዘርዓያቆብ፣ ብሩህ ተስፋ እና አንድነት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በቪዲዮ ቀረፃ የተደገፈ ምልከታ በዋና መረጃ መሰብሰቢያነት፣ የፅሁፍ መጠይቅና ቃለ -መጠይቅ ደግሞ በአጋዥነት አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ መረጃዎችን ለመተንተን በጥናቱ ዓይነታዊ ዘዴ በዋናነት፣ መጠናዊ ዘዴ በአጋዥነት ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ትንተናውን ለማከናወን በመጀመሪያ ከምልከታና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች የድግግሞሽ መጠን በአሃዝና በመቶኛ የተሰላ ሲሆን ፣ ቀጥሎም ከቃለ - መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደዚሁ በመልክ በመልክ ተደራጅተዋል፡፡ ከዚያም ከሶስቱም መሣሪያዎች የተገኙ መረጃዎች አንድምታ እርስ በርስ እየተመሳከሩ በገለፃ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ ከጥናቱ ውጤትም በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎቹን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ብቃት እንዳላቸው ፣ መምህራን የመናገር ክሂልን ለማቅረብ የሚረዱ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች መኖራቸውንና ዘዴዎቹ የተለያዩ የመናገር ክሂል ተግባራትን ለማቅረብ ያላቸውን ፋይዳ አለመገንዘብ ፣ የተማሪዎችን ተራክቦ ለማሳደግ የሚረዱ የአቀራረብ ቅደም ተከተሎችንና ብልሃቶችን በሚመለከት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን ፣ በመናገር ክሂል አቀራረብ የተማሪዎች የእርስ በርስ ተራክቦ ጉልህ ድርሻ የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የችግሩ ዋነኛ ምንጭም መምህራን በሰለጠኑበት የትምህርት ተቋምም ሆነ በስራ ላይ እያሉ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት ስልጠና አለመውሰዳቸው ሲሆን፣ የተወሰኑ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ስለሆነ አውቀዋለሁ በሚል እምነት ለመናገር ክሂል ትኩረት አለመስጠት፣ የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት ባለመሆኑ ለመናገር ክሂል አቀራረብ አመቺ አለመሆን ሌሎች ተጠቃሽ ችግሮች እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ችግሮቹንም ለመፍታት በዋናነት መምህራን ከአዳዲስ አስተሳሰቦችና አሰራሮች ጋር እንዲተዋወቁ ለማድረግ ስልጠና እንዲያገኙ ቢደረግ ፣ የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ በስታንዳንዱ መሠረት ቢሆን የሚሉ የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ለበርካታ ዘመናት ቋንቋ ማስተማር የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ህግጋት በመተንተን ላይ የሚያተኩር ሲሆን ከክሂሎችም ትኩረት ይሰጣቸው የነበሩት ማንበብና መፃፍ ብቻ ነበሩ፡፡ ይህ ዓይነቱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን የዘነጋ ነበር Bailey(2006:130) ፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መፈንዳት ጋር ተያይዞ ብቅ ያለው አዳምጦ የመናገር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ዓላማ ተማሪዎች ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ የመግባባት ብቃታቸውን ከፍ እንዲል ማድረግ ነበር፡፡ የማስተማሪያ ዘዴው ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች ቅድሚያ የሚሰጥ ቢሆንም አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች ለማስተማር ሞክሯል፡፡ ተግባቦትን ለማሳደግ በተማሪዎች መካከል የእርስ በርስ መስተጋብር እንዲኖር ማድረጉና የቋንቋ ቤተሙከራ መጠቀሙ የዘዴውን ጠንካራ ጐኖች የሚያጐሉ እንደነበሩ Dinzil (1987:18) እና Dailey (2006) ጨምረው አስረድተዋል፡፡

ይሁን እንጂ የማስተማሪያ ዘዴው የሚጠቀምበት ድሪልና ሽምደዳ ተማሪዎችን የሚያሰለችና የሚያዳክም በመሆኑ ተማሪዎች በሚማሩት የቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ የሆነ አመለካከት እንዲፈጥሩ አድርጓል፡፡ ይህም ሜካኒካዊ የሆነ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ የሚናገሩትን ቃላት ፍቺ የማያውቁ ተማሪዎች ከመፍጠር ውጪ ትርጉም ባለው መንገድ የተማሪዎችን የመግባባት ብቃት ማሳደግ እንዳልቻለ Dinzil (1987) እና Bailey (2006) አዳምጦ የመናገር ዘዴ ይዞት የተነሳውን ዓላማ በሚፈለገው ደረጃ ከግብ አለማድረሱን ጠቁመዋል፡፡

ለዚህም ነው በ1970ቹ እና በ1980ቹ ሰዎች ቋንቋዎችን ሊማሩ የሚችሉት እርስበርስ በሚያደርጉት መስተጋብር ነዉ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ሀሳባቸዉን በንግግር መግለፅ ይችሉ ዘንድ በቋንቋ ትምህርት የርስበርስ መስተጋብር ማድረግ አለባቸው የሚለው እሳቤ ግንዛቤ ያገኘውና ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ብቅ ያለው Bailey (2006:132) ፡፡

ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በስራ ላይ ውሎም ቢሆን የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ትኩረት ያላገኙበትን ምክንያት Sesnan (1997:103) ትምህርት ቤቶች አብዛኛውን ጊዜ ትኩረት የሚያደርጉት በማንበብና በመፃፍ ክሂሎች ነው ፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን በፈተና መመዘን

አስቸጋሪ ነው ከሚል እምነት የመነጨ ነው። ነገር ግን በአንድ ቋንቋ በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ለመገልገል አራቱን ክሂሎች መገልገል የግድ ስለሚል አስተሳሰቡ ሚዛን እንደማይደፋ ይገልፃሉ።

እኚሁ ምሁር አራቱን ክሂሎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ መለማመድና መገልገል እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነና ከእነዚህ ክሂሎች ውስጥ ለአንዱ ወይም ለሁለቱ ብቻ ትኩረት ሰጥቶ ሌሎቹን ክሂሎች ቸል ማለት ከቋንቋ ትምህርት ዓላማ አኳያ የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ከአልጋ አራት እግሮች ጋር በማወዳደር እንዲህ ይላሉ። "አንድ አልጋ፣ አልጋ የሚባለው አራት እግሮች ሲኖሩት ነው። ከአራቱ እግሮች መካከል ሁለቱ ቢጐሉ ግን ሰዎች አልጋ ብለው ሊጠሩት አይችሉም። አልጋ ለመባል አራቱ እግሮች የግድ ማሟላት ይኖርባቸዋል" Sesnan (1997፡ 103)።

ንግግር ሰውን ከእንስሳት ከለዩት ክስተቶች አንዱና ዋነኛው ሲሆን የፅሁፍ ጥበብ ከመምጣቱ በፊት ጀምሮ ለረጅም ዘመናት ከሰው ልጅ ጋር አብሮ ኖሯል። ይሁን እንጂ ከእሱ እጅግ በጣም ዘግይቶ ከመጣው ከፅህፈት ጋር ሲነፃፀር የሚሰጠው ግምት አነስተኛ ነው ። ክሂሉ ትኩረት የተነፈገው መሆኑን MC Donough and Shaw (1995:151) ለፅሁፍ በተለይም ሊነበብ ለሚችል ስነፅሁፍ ከፍተኛ የሆነ ግምትና ክብር ሲሰጥ ንግግርን ማስተማር ግን ብዙውን ጊዜ ተራ የንግግር ቋንቋን (Colloquial) ማስተማር ተደርጐ ስለሚታሰብ ዝቅተኛ ግምት ይሰጠዋል። ... የሰዎች ማንነት አብዛኛውን ጊዜ የሚለካው ከሌሎች ክሂሎች ይልቅ በንግግራቸው ስለሆነ ንግግር ጥበብ ነው ። ስለሆነም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ሲሉ ያስረዳሉ።

(Bygate 1987: Viii) በበኩላቸው ንግግርን ማስተማር ቸል የማይባል ጉዳይ መሆኑን እንዲህ ሲሉ ያስገነዝባሉ። ተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት በማዳበር በሚያደርጉት ንግግር ዕለታዊ ተግባሮቻቸውን ማከናወን ይፈልጋሉ። በንግግራቸውም ማንነታቸው ይለካል፤ በተግባባቱም ጓደኝነት ሊመሰረቱ ወይም ሊያጡ ይችላሉ። ንግግር አመርቂ የሆነ ማህበራዊ ትብብር ፣ ማህበራዊ ቦታ ፣ ሙያዊ ከበሬታ ... መመስረቻ መንገድ ከመሆኑም በተጨማሪም ቋንቋን ለመማር በመሣሪያነት በማገልገል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ይህም መናገርን የማስተማር ተገቢነት እሳቤ ያጐላል።

ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከአካቢያቸው ስለሚለምዱት የመናገር እውቀትን ይዘው ወደ ትምህርት ቤት ይመጣሉ። ስለዚህ በቋንቋው አፋቸውን የፈቱ

ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚማሩት (የሚያዳብሩት) ክሂሉን ነው፡፡ ተማሪዎች ክሂሉን መማራቸውም ከኢመደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ወደ መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም መሸጋገር እንዲችሉ ይረዳቸዋል ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (ቅማዩኮ) (2006፡91)፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የመናገር ክሂልን መማራቸው በክፍል ውስጥ ለሚያቀርቡት ንግግር መረጃ በማሰባሰብና ልምምድ በማድረግ ሐሳባቸውን አደራጅተው መናገር እንዲችሉ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ አተገባበርን በሚመለከት ደግሞ ከመምህር - መር (Teacher- centred) የመማር ማስተማር ይልቅ ቡድኖችን በማደራጀት ማስተማር ውጤታማ እንደሆነ Bygate (1987:96) Long እና Porter (1985)ን በመጥቀስ እንዲህ ይላሉ ፡፡ አነስተኛ የቡድን መስተጋብር እያንዳንዱ ተማሪ የተለያየ ሀሳብ በማፍለቅ እርስ በርስ የተሻለ እንዲነጋገሩ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎቹ ብዙውን ጊዜ የሚያጠፉት ሀሳቡን ለመረዳት ስለሆነ መምህሩ፣ በመምህር- መር አቀራረብ እንደሚያደርገው አብዛኛውን ጊዜ መተራረም አይኖርም፡፡ ስህተቶችንም ከመምህር መር አቀራረብ የበለጠ በጣም ተዘውታሪ (በርካታ) ሆነው አያገኟቸውም፡፡

መምህራን ጠመኔንና ሰሌዳን በመጠቀም ብቻ የቋንቋን ትምህርት ማስተማር እንደሌለባቸውና የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው የተለያዩ ምሁራን ቢያሳስቡም የቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ መስተጋብር ከዚህ ዓይነቱ ባህል ብዙም የተላቀቀ አይመስልም፡፡ ይህ ዓይነቱ አቀራረብ መለወጥ እንዳለበት Sesnan (1997:172) ሁሉንም ነገር ከአንድ ሰው አንደበት መስማትና ሁሉንም ነገር ሠሌዳ ላይ ማየት አስልቺ ነው በማለት ተችተዋል፡፡

ቀጥለውም እኚሁ ምሁር የገለፃ አቀራረብ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ተማሪዎች ባሉባቸው የቋንቋ ክፍሎች የተለመደ የማስተማሪያ ዘዴ እየሆነ ነው፡፡ ይህ ግን ብቸኛው መንገድ መሆን የለበትም ምክንያቱም ተማሪዎች በተለያዩ መንገዶች ይማራሉ፡፡ የተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ በሆኑባቸው ክፍሎችም ውስጥ ቢሆን ሌሎች የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን (የቡድን ስራ ፣ ሚና ጨዋታ ፣ ታሪክ መንገር ፣ ችግር ፈቺ ዘዴ...) በመጠቀም ማስተማር እንደሚገባ ያስገነዝባሉ sesnan (1997)፡፡

Ur (1996 ፡ 227) በበኩላቸው የክፍል ውስጥ መስተጋብራዊ ክንውኖች አነሳሽነት ሁልጊዜ በመምህሩ እጅ መውደቅ የለበትም፣ መስተጋብሩ በተማሪዎች መካከል ወይም

በተማሪዎችና በማቴሪያሉ መካከል ሊሆን እንደሚችል በመጥቀስ የቋንቋ ክፍልን ገፅታ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

ከላይ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን እንደተገለፀው የመናገር ክሂል ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለመመስረትና ዕለታዊ ተግባሮቻችንን ለማከናወን ጉልህ ድርሻ የሚያበረክት ቢሆንም ክሂሉን ለማዳበር የሚረዱ ተግባራትን በማስተማሪያ መሣሪያዎች በማካተትም ሆነ የክፍል ውስጥ አተገባበሩን በሚመለከት ብዙም ትኩረት ሳይሰጠው እንደቆየ መረዳት ይቻላል ፡፡ ስለዚህ እንደነዚህ ዓይነት ችግሮችን ለመቅረፍ የመምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር (Statement of the problem)

የጥናቱ ትኩረት የሆነው የአማርኛ ቋንቋ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሥራ ቋንቋነት ሲያገለግል በሁሉም የትምህርት እርከኖች እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጣል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (7ኛ እና 8ኛ ክፍል የሂሳብና የተፈጥሮ ሣይንስ ትምህርቶች በስተቀር) ደግሞ የማስተማሪያ ቋንቋ በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ የቋንቋውን የአገልግሎት ደረጃ ለማሳደግ የተማሪዎችን የማንበብ ፣ የመፃፍ ችሎታ ከማሳደግ በተጨማሪ ሀሳብን በንግግር የመግለፅ ችሎታን ከፍ ማድረግ የግድ ይላል፡፡

የቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ልምድ እና አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት እስከ 1970ቹ ድረስ በበርካታ አገሮች ቋንቋ ማስተማር የሚያተኩረው በሰዋስው፣ በማንበብና በመፃፍ ላይ ነበር Scrivener (1994:21)፡፡ ከ1970ቹ ወዲህ የመናገር ክሂል እንደአንድ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ቢካተትም ትርጉም ባለው መንገድ ይቀርብ ነበር ለማለት አያስደፍርም፡፡ በዚህም ምክንያት "አብዛኛዎቹ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁት ጥሩ የንግግር ችሎታ ሳያዳብሩ ነው፡፡ በመሆኑም ከትምህርት ቤት በኋላ ባለው ህይወታቸው ያለምንም ችግር ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለጽ ይቸገራሉ፡፡ በራስ ያለመተማመንና መልዕክትን በምክንያትና ውጤት አደራጅቶ ያለማቅረብ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው" ብሎክ (1997) በቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (2006:24)፡፡

የራሴ የሙያ ልምድ እንደሚያሳየው ዛሬም ቢሆን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር የመግለፅ ችግር አለባቸው፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ማለትም ስነልሳናዊ ፣ ማህበራዊ ፣ተግባቦታዊ ብልሀቶችንና ዲስኩራዊ ችሎታዎችን Baiely

(2006:127) በማሳደግ ሀሳባቸውን መግለፅ ይችሉ ዘንድ የትምህርት ስራው በየደረጃውም በጥናት መደገፍ አለበት፡፡

የዚህ ዓይነቱን ችግር ለመፍታት የመናገር ክሂልን በሚመለከት ያጋጠሙ ችግሮችን ለይቶ መፍትሔ ለመስጠት መንግስቱ ታደሰ (1977) "በአዲስ አበባ መስተዳድር የ9ኛ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ አተገባበር ግምገማ" በሚል ርዕስ ያደረገው ጥናት ሲሆን አጥኚው መምህራን የመናገር ክሂል የሚያከናውኑበት ሥነ ዘዴ ተማሪዎች ነፃ ሆነው እንዲነጋገሩ የሚያበረታታ ሆኖ አለመገኘቱን ጠቁሟል፡፡

የጥናቱ ውጤትም የመምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ግንዛቤ በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረሱን ያመለክታል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመጀመሪያው እርከን (9-10) መሰረት የሆነውን የትምህርት እርከን (5-8) የመናገር ክሂል አቀራረብ በመፈተሽ ችግሩ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ተጨማሪ ጥናት ማድረግን የሚጋብዝ ነው፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ የቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን የመናግር ክሂል ለማሳደግ ምን ምን የመናገር ክሂል ተግባራትን ይገለገላሉ? የተግባራቱን አቀራረብ በሚመለከት ግንዛቤው አላቸው ወይ ? ግንዛቤው ካላቸው እንዴት እየሰሩ ነው? ተግባራቱን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡስ ምን ምን ችግሮች ያጋጥሟቸዋል ? በአንፃሩ ግንዛቤው ከሌላቸው የችግሩ መንስኤ ምንድነው ? መፍትሄውስ ? የሚሉትን ጥያቄዎች ፈትሾ ምላሽ መስጠት የጥናቱ መነሻ ሀሳቦች ናቸው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች በየክፍል ደረጃው አራቱን የቋንቋ ክሂሎች እንዲሁም የስነልሳንና የስነፅሁፍ ዕውቀት ማዳበር ነው፡፡ ሁኔታውን የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት (አብክመ) ትምህርት ቢሮ ለሰባተኛ ክፍል ባዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ መግቢያ ላይ " የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለደረጃው የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት መሰረት በማድረግ የክሂልና የዕውቀት ዘርፎችን የሚያዳብሩ ይዘቶችን ይዟል " አብክመ ትምህርት ቢሮ (1997)፡፡ ይህንኑ ሀሳብ Ur (1996:120) ተማሪዎች በንግግር ራሳቸውን መግለፅ የሚያስችሉ የክፍል ውስጥ ተግባራት መካተት ለቋንቋ ትምህርት ጠቃሚ እንደሆነ በመግለፀ ያጠናክሩታል፡፡

በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህሩ ሚና ጉልቶ የተማሪዎቹ ሚና እንዳይቀጭጭ በመማሪያ መፃህፍት /በመምህሩ መምሪያ ዝግጅት ወቅት ማን ምን እንደሚያከናውን መፃህፍቱ መጠቆም እንዳለባቸው Cunningsworth (1995:110) የመማሪያ መፃህፍት የመምህሩ ዋና ተግባር መምራት ፣ ማደራጀትና መከታተል እንደሆነ ይለያሉ። ስለሆነም መምህር በመሰረተ ሀሳብ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን የሚመራ ፣ የተማሪዎችን የትምህርት ርምጃ የሚከታተል ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለስህተቶች ምጋቤ ምላሽ የሚሰጥ ነው ሲሉ አስገንዝበዋል።

ስለዚህ የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ በደብረ ብርሃን ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ለመፈተሽ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

1. መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የታዩ የአቀራረብ ችግሮችን እና የችግሮቹን መንስኤዎችን ለመለየት፣
2. በመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ ክንውኖች ወቅት ለተከሰቱ ችግሮች የመፍትሄ ሐሳብ ለማቅረብ ነው።

ስለሆነም ጥናቱ ከላይ የቀረቡትን አጠቃላይ እና ዝርዝር አላማዎች መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን መሪ ጥያቄዎች በመመርመር ይመልሳል።

- መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የሚረዱ ምን ምን ተግባራትን /የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ ?
- በመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ የመምህር - ተማሪ ተራክቦ (ውቅሮች) ምን ይመስላል?
- የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አቀራረብን በሚመለከት የመምህራን ግንዛቤ ምን ይመስላል?
- መምህራን የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ወቅት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምንድናቸው?

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚያቀርቡ ግንዛቤው ካላቸውም መምህሩ ተናጋሪ ተማሪዎች አድማጭ፣ መምህሩ ጠያቂ ተማሪዎች መላሽ ወዘተ... ከሚሆኑበት የመማር ማስተማር ሂደት በመቆጠብ አብዛኛው የክፍል ውስጥ

መስተጋብር በተማሪዎች መካከል የሚሆንበት አውድ ለመፍጠር ይረዳቸዋል። ይህ ዓይነቱ የክፍል ውስጥ ክንውን ደግሞ ተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት በመፍጠር ሀሳባቸውን በነፃነት የመግለፅ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል።

**ስለዚህ ጥናቱ፡-**

- መምህራንና ተማሪዎች ውጤታማ የመናገር ክሂል የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለወደፊቱ እንዲገለገሉባቸው ለመጠቆም ይረዳል ፣
- መምህራንና ተማሪዎች የመናገር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ የተለያዩ ተግባራትን ለይተው በማወቅ በመማር ማስተማሩ ተግባር በቀጣዩ እንዲገለገሉባቸው ያግዛል ፣
- በመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አቀራረብ ለሚታዩ ችግሮች የመፍትሄ ሀሳብ ሊሰጥ ይችላል ፣
- በርዕሱ ዙሪያ ጥናት ለሚያካሂዱ ሌሎች ተመራማሪዎች መነሻ በመሆን ተጨማሪ ምርምር እንዲያደርጉ ለማነሳሳት ይጠቅማል።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የተካሄደው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ስር በሚገኙ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፣ ብሩህ ተስፋ እና አንድነት የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ነው። ጥናቱ የሚያተኩረውም በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አቀራረብ ግምገማ ላይ ሲሆን የዚህ የክፍል ደረጃ መምህራንና ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪዎች ናቸው ።

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

## 2.1 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ "በየደረጃው ከሚጠበቀው የባህሪ ገፅታ ብቃት (ለውጥ) አንፃር ተማሪዎች በትምህርታቸው ሂደት የማዳመጥ ፣ የመናገር ፣ የማንበብና የመፃፍ ክህሎታቸውን፣ እንዲሁም የስነልሳንና የስነፅሁፍ ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩ" ማድረግ እንደሆነ ስርአተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት (ስ.ት.ዝ.ጥ.ም.ኢ) (1994፡ I) ይገልፃል፡፡ ከእነዚህ የቋንቋ አላማዎች ውስጥ አንዱ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ማሳደግ የሚለው ነው፡፡

የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ደግሞ ለክፍል ደረጃው ተገቢነት ያላቸውን የመናገር ክሂል ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ስርዓት በመጠቀም ሀሳባቸውን በንግግር እንዲገልጹ በክፍል ውስጥ መለመማድ ይኖርባቸዋል፡፡ የክፍል ውስጥ ልምምዱን ውጤታማ በማድረግ የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ወደላቀ ደረጃ ለማድረስም መምህራን የመለማመጃ ተግባራቱ የሚቀርቡበትን መንገድ ጠንቅቀው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይህንንም ተግባር ከግብ ለማድረስ መምህራን በክፍል ውስጥ በሚደረገው ተግባቦታዊ ሂደት ብዙ ከመናገር በመቆጠብ ቀስቃሽና አጋዥ መሆን ይኖርባቸዋል እንጂ አዘውትረው ከተማሪዎቹ ጋር መስተጋብር ማድረግ አይጠበቅባቸውም፡፡ ተማሪዎችም የመናገር ክሂል ችሎታቸውን የማሳደግ ሀላፊነት ያለባቸው መሆኑን ተገንዝበው በጥንድ / በቡድን በመሆን የርስበርስ መስተጋብር ማድረግ የግድ ይላቸዋል፡፡

የዚህ የቀደምት ጥናቶች የሚለው ክፍል ዓላማ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቀደምት የጥናት ስራዎች መቃኘት ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያለው አንድ ቀደምት ስራ መንግስቱ ታደሰ " በአዲስ አበባ መስተዳድር የ9ኛ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ አተገባበር ግምገማ " በሚል ርዕስ በ1997 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያደረገው ጥናት ነው፡፡

የጥናቱ አቅራቢ "በክልል 14 የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂል የማስተማር ስነዘዴያቸው ምን እንደሚመስልና የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር

የተመረጡ ይዘቶችን በመጠቀም ... የተለያዩ የንግግር ማስተማር ደረጃዎችን ተከትለው የትምህርት ሂደቱን ማከናወን አለማከናወናቸውን በመገምገም ጥሩ ጐኑ እንዲቀጥል ፤ ደካማ ጐኑ ደግሞ እንዲሻሻል የመፍትሄ ሀሳብ .... ለመጠቆም ነው " በማለት የጥናቱን አጠቃላይ አላማ አመልክቷል፡፡

አጥኚው ከላይ የተጠቀሰውን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ ሶስት መሪ ጥያቄዎችን ይዞ የተነሳ ሲሆን በጥናቱም ለክፍሉ ደረጃዎች የቀረቡት መርጃ መሣሪያዎች በውስጣቸው ያካተቷቸው ይዘቶችና መልመጃዎች ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር የመግለፅ ችሎታቸውን የማያዳብሩ ፣ በተማሪዎች መካከል የርስበርስ መስተጋብር ለመፍጠር የማያስችሉ መሆናቸውን ፣ እንዲሁም የቀረቡት የንግግር ተግባራት የሚከናወኑበት ስነ-ዘዴ የክፍል ውስጥ ትግበራ ተማሪዎች ቀስ በቀስ ነፃ ሆነው እንዲናገሩ የማያበረታቱና ስራው ቀጣይነት እንዲኖረው የማያደርጉ ሆነው እንደተገኙ በጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ከጥናቱ ውጤትም የመናገር ክሂል መለማመጃ ተግባራትን በማስተማሪያ መሣሪያዎች በማካተትም ሆነ ተግባራቱን በክፍል ውስጥ ከማቅረብ አኳያ ችግር እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመጀመሪያው እርከን ችግር ይቀረፍ ዘንድ በቀዳሚዎቹ የትምህርት እርከኖች ባሉት የክፍል ደረጃዎች ጥናት ማካሄድና የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም የግድ ይላል፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት ከመንግስቱ ታደሰ ጥናት ጋር ተመሳስሎ አለው ፡፡ ተመሳስሎውም የመናገር ክሂል ተግባራትን አቀራረብ ክንውኖች መፈተሹ ነው ፡፡ ልዩነቱ ደግሞ የመንግስቱ ታደሰ ጥናት የተካሄደው በአዲስ አበባ መስተዳድር የ9ኛ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ አተገባበር ግምገማ ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ትኩረት ያደረገው በአማራ ክልል በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሰባተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አቀራረብ ነው፡፡

ስለሆነም ይህ ጥናት ከቀዳሚው ጥናት ከቦታ በተጨማሪ በክፍል ደረጃ ይለያል፡፡ የተጠኝዎች መለያየት ለጥናቱ ውጤት መለያየት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ከክፍል ደረጃ በተጨማሪ ጥናቱ ከቀዳሚው ጥናት የሚለየው በዘመን ነው፡፡ የመምህራን አሰለጣጠን ከዘመኑ ዕድገት ጋር ለውጥ ስለሚያሳይ ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ማሻሻያ ስለሚደረግባቸው ወዘተ ... በጥናቱ ውጤት ላይ ለውጥ ያስከትላል፡፡ በመናገር ክሂል አቀራረብ የመምህር-ተማሪ ተራክቦ ውቅር ገጽታን ትኩረት ሰጥቶ ማየቱ ጥናቱ ከቀዳሚው

ጥናት የሚለይበት ሌላው ነጥብ ነው። በመጨረሻም በትኩረት ነጥብ አቅጣጫ ጥናቱ ከቀዳሚው ጥናት ይለያል። ቀዳሚው ጥናት የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለመሆኑን የፈተሸ ሲሆን ይኸኛው ጥናት ግን የአፍ ፈት ተማሪዎችን ክፍል መነሻ ያደርጋል።፣

## 2.2 የመናገር ክሂል ፅንሰ ሀሳብ

መናገር በርካታ ገፅታዎች አሉት ። ምንነቱን ለመረዳት የትክክለኛነትን (accuracy) እና የቋንቋ ፍሰትን (fluency) ምንነት ማየት ይጠቅማል። ትክክለኛነት የቃላት፣ የሰዋሰውና የንበት አግባባዊ አጠቃቀምን የሚያመለክት ሲሆን የቋንቋ ፍሰት ደግሞ ሰዋሰዋዊና መሰል ስህተቶችን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ሀሳብን አቀላጥፎ የመግለፅ ችሎታ ነው Gower et al. (1995:99) ።

ከዚህ የምንረዳው የመናገር ክሂል የአንድን ቋንቋ ውስጣዊ መዋቅር ማለትም የቃላት ፣ የሰዋስውና የንበት ስርዓት ጠንቅቆ በመረዳት ፍርሃትን እና ጭንቀትን በማስወገድ ሀሳብን ፍሰትን በጠበቀ መንገድ የማስተላለፍ ችሎታን የሚጠይቅ መሆኑን ነው።

ንግግር የሰው ልጅ ፍላጐቱን ፣ ስሜቱን አመለካከቱን ለሌላ ሁለተኛ አካል የሚያስተላልፍበት መስተጋብራዊ ሂደት ነው። ስለሆነም የመናገር ክሂል የማዳመጥን ምላሽ የሚፈልግ በመሆኑ ከማዳመጥ ክሂል ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። ስለዚህ የመናገር ክሂል ይዳብር ዘንድ የማዳመጥ ክሂልም መዳበር እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል።

ባጭሩ የመናገር ክሂል ዳብሯል ማለት የሚቻለው ሀሳብን በብቃት ለሌላ ሁለተኛ አካል ማስተላለፍ ሲቻል ነው ። ብቃቱን ለማምጣት ደግሞ ሀሳብን የማደራጀት ፣ አሳማኝ ነጥቦችን የማፍለቅ ፣ ተገቢ ቃላትን የመምረጥ እንዲሁም የንግግር ማበልፀጊያ ዘዴዎችን (የአካል እንቅስቃሴ ፣ የገፅታ መለዋወጥ ፣ የድምፅ ቅላፄ) የመጠቀም ችሎታዎችን የሚጠይቅ ነው ። ስለሆነም ተማሪዎች እነዚህን ችሎታዎች እንዲያዳብሩ መምህራን ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## 2.3 የመናገር ክሂልን የማስተማር ዓላማ

Mc Donough and Shaw (1995:152) እንደሚሉት መናገር ፍላጐትንና ዓላማን መሠረት ያደረገ ነው። በሌላ አገላለፅ አንድን ግብ ለማሳካት በጋለ ስሜት ከሰዎች ጋር

ለመግባባት እንፈልጋለን። ይኸውም አላማችንንና ሀሳባችንን ለመግለፅ ፣ አንድን የተወሰነ ችግር ለማቃለል፣ ማህበራዊ ግንኙነትንና ባልንጀራነትን ለመመስረትና ለመያዝ ሊሆን እንደሚችል የምንናገርበትን ምክንያት ያስረዳሉ ።

ባጭሩ እንደምሁራን እምነት አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር መስተጋብራዊ ግንኙነት የሚያደርገው ፣

- እርዳታ ለመጠየቅ
- አቅጣጫ ለመጠየቅ
- ቀጠሮ ለመያዝ
- ከሰዎች ጋር ለመግባባት ወዘተ ሊሆን ይችላል።

Harmer (2007 : 123) መናገር የምናስተምርበትን እና ተማሪዎችም በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ የምንፈልግበትን ሦስት ምክንያቶች እንደሚከተለው ጠቅሰዋል።

- የመናገር ክሂል ተግባራት የልምምድ ዕድሎችን ማለትም ለዕውኑ ዓለም ንግግር የሚያገለግል የልምምድ ዕድል በክፍል ውስጥ ስለሚሰጡ፣
- ተማሪዎች የሚገለገሉባቸው የመናገር ክሂል ተግባራት ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ሁሉም ምን ያህል ጥሩ እንደሰሩ ፣ ምን ያህል ስኬታማ እንደሆኑና ምን ዓይነት የቋንቋ ችግር እንዳጋጠማቸው ስለሚለዩበት፣
- ተማሪዎች በአእምሯቸው ያከማቹትን የቋንቋ ቅርፃችን የመገልገል ችሎታቸው ይጨምራል። ይህም ቃላትና ሀረጋትን ያለምንም ጭንቀት በጥሩ ሁኔታ መገልገል ስለሚያስችላቸው ነው ።

Scrivener (1994:59) በበኩላቸው "በቋንቋ ክፍል ውስጥ ለሚደረግ ንግግር በርካታ ዓላማዎች ቢኖሩትም ዋናው ዓላማ ለንግግር የልምምድ እድል ለመስጠት ነው ። በልምምዱ ወቅት ትኩረት የሚሰጠውም ከትክክለኛነት ይልቅ የቋንቋ ፍሰትን ለማሻሻል ነው" ይላሉ። የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት በማሳደግ ሀሳባቸውን በትክክልና በቀለጠፈ መንገድ መግለፅ እንዲችሉ የንግግር ተግባራትን በጥንድ ፣ በሶስትዮሽና በትንንሽ ቡድኖች ማደራጀትና አንዳንዴም ሁሉንም ተማሪ የሚያሳትፍ ዕድል መፍጠር ዓላማውን ለማሳካት ጠቃሚነት እንዳለው ምሁሩ ያስገነዝባሉ።

የአፍልቆት ክሂል የሆነውን የመናገር ክሂልን የማስማተር ዋና ዓላማ የቋንቋ ፍሰትን ወደሚፈለገው ደረጃ ማድረስ ቢሆንም ስኬታማ ቃላዊ ተግባቦት የሚከተሉትን ክሂሎች እንደሚያሳድግ (Nunan 1991፡32) ገልፀዋል።

- የቋንቋውን ስነ ድምፃዊ ባህርይ የመናገር (የማንበብ) ችሎታ ለምሳሌ የጥብቀት ፣ ምትና ቅላፄ ስርዓት ጠንቅቆ ማወቅ፣
- ተቀባይነት ያለው የቋንቋ ፍሰት ችሎታ፣
- የዕለታዊ ተግባራትና የሰላምታ ልውውጥ ግንኙት ክሂል፣
- ተራን ጠብቆ የመናገር ችሎታ
- መስተጋብራዊ በሆኑ የተግባቦት ሂደቶች የመሳተፍ ችሎታ ፣
- መልዕክትን የመቀበልና የመረዳት ክሂል
- የሀሳብ ማሟያ ዘዴዎችን (fillers) በአግባቡ የመጠቀም ችሎታ ናቸው።

Hammer (1991 11-15) እንደሚሉት ደግሞ አፍ ፈት ተናጋሪዎች ( native speakers ) ቋንቋቸውን በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ የንበት (Pronunciation) ፣ የሰዋስው (Grammar) ፣ የቃላት (Vocabulary) ፣ የዲስኩር (Discourse) ወዘተ ዕውቀት (እነዚህ ችሎታዎች የአፍ ፈት ተናጋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የሁለተኛና የሶስተኛ ቋንቋ ... ተናጋሪዎች ናቸው) ሊኖራቸው ይገባል።

አፍ ፈት ወይም ብቃት ያላቸው የቋንቋ ተናጋሪዎች ቃላትን ማንበብ ማወቅ አለባቸው። ይህ ዕውቀት የድምፅ (Sound) ፣ የጥብቀት (stress) እና የቅላፄ (Intonation) ዘርፍን የሚሸፍን ሲሆን የቋንቋው ተናጋሪዎች ድምፆችን ማፍለቅ ፣ ቃላት የሚጠብቁበትን ቦታ መለየትና የተለያዩ ቅላፄዎችን ድምፀት ምንነት መረዳትና መጠቀም መቻልን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል።

አንድ አፍ ፈት ተናጋሪ ከንበት በተጨማሪ የቋንቋውን ሰዋስው ማወቅ አለበት ። በከፊል ንቁ (subconscious) የሆነ የሰዋሰው ህግ ዕውቀት ተናጋሪው ስፍር ቁጥር የሌላቸው ዐረፍተ ነገሮች (infinite number of sentences) እንዲያፈልቅ ያደርጉታል። ይህ በከፊል ንቁ የሆነ የቋንቋ ህግ ዕውቀት አፍ ፈት ተናጋሪው ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ያላቸው ዐረፍተ ነገሮችን (grammatically correct sentences) ማፍለቅ እንዲችል ይረዳዋል ማለት ነው ።

አፍ ፈት ተናጋሪዎች የቃላት ዕውቀትም ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች (Literal and connotation meaning) ማወቅ ለአንድ ብቃት ያለው የቋንቋ ተናጋሪ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ አፍ ፈት ተናጋሪው ቃላትን በጥሬ ፍቻቸው ብቻ ሳይሆን በምስጢራዊ ፍቻቸውም የሚሉትን ነገር መረዳት መቻል ይኖርበታል፡፡

የሰዋሰውና የቃላት ዕውቀት ብቻውን ለተግባቦት በቂ አይደለም፡፡ ስለዚህ አፍ ፈት ተናጋሪዎች ከሰዋሰውና ከቃላት ዕውቀት በተጨማሪ ተግባቦታዊ ብቃት (communicative competence) ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ተግባቦታዊ ብቃት የቋንቋው ተናጋሪ የቋንቋውን ቅርጾች እንዴት አደራጅቶ በተገቢው መንገድ እንደሚገለገልባቸው ያለው ችሎታ ነው፡፡ ስለዚህ ተግባቡቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ተናጋሪው ቋንቋውን የሚናገርበትን ቦታ ( Setting ) ለማን እንደሚናገር (Participants)፣ የንግግሩን ዓላማ (purpose) ፣ ንግግሩ የሚተላለፍበትን ዘዴ ( channel) ወዘተ… ማወቅ ይኖርበታል፡፡

ባጭሩ የመናገር ክሂልን የምናስተምርበት ዓላማ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ሲሆን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚያከናውኗቸው ተግባራት አማካይነት ትክክለኛነትንና የቋንቋ ፍሰትን በሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ ነው ፡፡ ትክክለኛነትን ለማምጣት የቋንቋውን ህግ (የሥነ ድምፅ ፣ የቃላት ፣ የሰዋስው ) ጠንቅቆ በማወቅ ሙሉ ስሜት መስጠት የሚችል ሀሳብን አስክቶ ማፍለቅን የሚጠይቅ ሲሆን፣ የቋንቋ ፍሰት ብቃትን ለማምጣት ደግሞ ማህበራዊ አውድን፣ የቋንቋውን ተግባቦታዊ ብልሃቶችን በመጠቀም ተቀባይነት ባለው መንገድ ንግግርን እያቀናበሩ ያለመሰናክል ለማውጣት ያላሰለሰ ልምምድ ማድረግን ይጠይቃል፡፡

## 2.4 የመናገር ክሂል ተግባራት (activities) ባህርያት

ንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚደረግ የሁለትዮሽ ሂደት ሲሆን ይህንን ክሂል ለማዳበር የሚዘጋጁ መልመጃዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ከመምህር መር አቀራረብ በማላቀቅ የተማሪዎችን መስተጋብራዊ ግንኙነት የሚያበረታቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም ተግባራቱ ተማሪዎችን በጥንድ ፣ በሶስትዮሽና በቡድን የሚያሳትፉና በራስ የመተማመን ስሜት በማዳበር ሀሳባቸውን እንዲገልጹ የሚያግዙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ተግባራትን ማዘጋጀትና ማከናወን አስቸጋሪ እንደሆነ Ur (1996፡120) በመጠቆም ተከታዮቹን የስኬታማ የመናገር ክሂል ተግባራት ባህርያትን ጠቅሰዋል፡፡

ሀ. **ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች እንዲናገሩ ማድረግ** (Learners talk a lot) ፡- በተቻለ መጠን ለንግግር ተግባር የተሰጠው ጊዜ በተማሪዎች ንግግር መሸፈን ይኖርበታል ፤ ጉዳዩ ግልፅ ሆኖ እያለ ግን የክፍል ውስጥ ክንውን አብዛኛውን ጊዜ በመምህሩ ይሸፈናል፡፡ ስለዚህ የመምህሩን ሚና በመቀነስ የተማሪዎች መስተጋብራዊ ግንኙነት ጐልቶ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ለ. **ሁሉን ያማከለ ተሳትፎ** (Participation is even) ፡- የክፍል ውስጥ ክንውን ጥቂት ቁጥር ባላቸው ተማሪዎች ተፅዕኖ ስር ብቻ መውደቅ የለበትም፡፡ ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች የመናገር ዕድል ሊሰጣቸውና ተሳትፎአቸው የተመጣጠነ ሊሆን ይገባል፡፡

ሐ. **ከፍተኛ ተነሳሽነት** (Motivation is high) ፡- ተማሪዎች ለመናገር የሚነሳሱት በተመረጠው ርዕሰ - ጉዳይ ከፍተኛ ፍላጐት ስለሚኖራቸውና ርዕሰ ጉዳዩ የሚናገሩት አዲስ ሀሳብ ስለሚያጭርባቸው ነው፡፡ ወይም ደግሞ በሂደቱ ተሳትፎ በማድረግ ለንግግር ተግባር አላማ መሳካት አስተዋጽኦ ለማበርከት ነው፡፡ ስለዚህ ተግባራቱ የተማሪዎቹን ተነሳሽነት የሚያሳድጉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

መ. **የቋንቋው ቅቡልነት ደረጃ** (Language is an acceptable level) ፡- ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር ማለትም ተገቢነት ባለው መንገድ እርስ በርሳቸው መግባባት መቻላቸውንና ተቀባይነቱ ከፍ ባለ የቋንቋ ብቃት የመግለፅ አቅም ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ መምህራን ከላይ የተጠቀሱትን የስኬታማ የንግግር ክሂል ባህርያትን በቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ክንውን ወቅት መተግበር ከቻሉ ተማሪዎች የመናገር ክሂልን በቀላሉ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡

## 2.5 የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት

የቋንቋ ትምህርት የእውቀት ዘርፎችን (ስነ ልሳንና ስነፅሁፍ) እና አራቱን የቋንቋ ክሂሎችን በማሳደግ ላይ የተመሰረተ ነው ፡፡ ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ሊያሳትፉ የሚችሉ ተግባራትን መቅረፅ ያስፈልጋል፡፡ Harmer (2007 ፡ 55) እንደሚሉት ጥሩ የመናገር ክሂል ተግባራት ሲዘጋጁ ተማሪዎችን ʻሙሉ በሙሉ በትምህርቱ እንዲሳተፉ ዕድል የሚሰጡና ከልምምድ

በኋላ የመምህሩን ምጋቤ ምላሽ ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ከሆኑ ተማሪዎች በትምህርቱ ርካታ ያገኛሉ። ይህም ተማሪዎች የታለመውን አላማ በቀላሉ እንዲደርሱበት ይረዳል። ተግባራቱ ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፉ ከሆነ ክፍሉ መስተጋብራዊ ይሆናል። ይህ ደግሞ የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት ከፍ በማድረግ በንግግር ሀሳብን መግለፅ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ባህል እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የመናገር ክሂልን እንደክሂል ተማሪዎች እንዲያዳብሩት የሚረዱ ተግባራት በተለያዩ ምሁራን ስራዎች ውስጥ የተጠቀሱ ሲሆን የትኞቹ ተግባራት ለየትኛው የክፍል ደረጃ ይውላሉ? የሚለው ጥያቄ በብዙዎቹ ምሁራን የተነሳ ጉዳይ ባይሆንም Harmer (2007:129) የመረጃ ክፍተትን መሙላት ተግባራት (Information gap) እና ታሪክ መናገር (story telling) ለዝቅተኛ ክፍሎች ቢውሉ ተመራጭነት እንዳለው ጠቁመዋል። ምክንያቱም የመረጃ ክፍተት ተግባራት አቅጣጫን ማሳየት ፣ የነገሮችን (የስዕሎችን) ልዩነት መግለፅ ፣ በሰንጠረዥ መልክ የቀረቡ መረጃዎችን ማሟላት ላይ ስለሚመሰረቱ ተግባራቱ የውስብስብነት ባህሪ አይታይባቸውም። ይህም ባህሪያቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቀላሉ እንዲገልጹ ይረዳቸዋል። ተረታ ተረቶች (ታሪኮች) ደግሞ የልጆችን ባህሪ ከመቅረፅ ባሻገር የልጆችን ስሜት የማነሳሳት ኃይላቸው ከፍተኛ ስለሆነ በዝቅተኛ ክፍሎች መጠቀሙ ተገቢነት ይኖረዋል።

የመናገር ክሂልን ለማዳበር ይረዳሉ ተብለው በተለያዩ ምሁራን ከተጠቀሱት ተግባራት ዓይነቶች ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሱት ተግባራት ምንነት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 2.5.1 የመረጃ ክፍተትን መሙላት /Information gap/

በጥንድ ወይም በቡድን የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ የመልመጃዎቹ ዓላማ መረጃው የሌላቸው ተማሪዎች መረጃው ካላቸው ጋር እንዲነጋገሩ ለማድረግ ወይም መረጃው ያላቸው ተማሪዎች ለሌላቸው እንዲናገሩ ለማድረግ እንደሆነ Gowe et al. (1995:103) ገልፀዋል።

Bygate (1987:76) ፣ Gower et al. (1995 : 104) እና Harmer (2007 :129) አቅጣጫ ማሳየት፣ ቀጠሮ መያዝ ፣ የነገሮችን ልዩነት መፈለግ ፣ ንፅፅርና እና ትረካ ለመረጃ ክፍተት መሙላት ተግባራት ማሳኪያ ምሳሌዎች ሲሆኑ እንደሚችሉ ጠቅሰዋል።

### 2.5.2 ጨዋታዎች /Games/

Sesnan ( 1997፡116) "ጨዋታዎች ደስታ እየፈጠሩ የልጆችን የቋንቋ ችሎታ ለማሻሻል ይረዳሉ" ይላሉ፡፡ ጨዋታዎች በባህሪያቸውም ውድድራዊና ትብብርን የሚጠይቁ ወይም ሁለቱንም አካተው የሚይዙ ሲሆን በተወሰኑ ህጐች ይገዛሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀት ፣ ለጨዋታው ግልፅ ህግ ማዘጋጀት ፣ የጨዋታው አሸናፊዎች እስከሚታወቁበት የመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ድረስ ሂደቱ ሁሉንም የቡድኑን አባላት የሚያሳትፍ መሆኑን ማወቅ ፣ ተሸናፊዎች ከጨዋታው ውጪ ከሆኑ በኋላ እንደገና ወደ ጨዋታው የሚመለሱበት ህግ መኖሩን ማረጋገጥ፣ ወይም ጨዋታውን አሳጥሮ ቶሎ እንዲያልቅ ማድረግ ከጨዋታው በፊት የሚታሰብባቸው ጉዳዩች እንደሆኑ አስገንዝበዋል፡፡ ስለዚህ ልጆች ጨዋታዎችን እየተጫወቱ እግረ መንገዳቸውን የቋንቋ ችሎታቸውን ማሳደግ ይችሉ ዘንድ የመለማመጃ ተግባራቱ እንዴት እንደሚከናወኑ ዝርዝር መመሪያዎችን መምህሩ በቅድሚያ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

ጨዋታዎች በተለይ ለታዳጊዎች ጠቃሚዎች ሲሆኑ በሁሉም የዕድሜ ክልል ላሉ ተማሪዎች ተወዳጅ ናቸው ፡፡ ህብረ ብዙህነት (Multinational classes ) በሆኑ ክፍሎች ጨዋታዎች ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም የተወሰኑ ተማሪዎች ጨዋታውን ሲችሉ ሌሎች ደግሞ ጨዋታውን ፈፅሞ ሰምተውት የማያውቁት ሊሆንባቸው ይችላል፡፡ ይህም የጨዋታዎች ውስንነት መሆኑ ነው ( Gower et al. 1995፡110)፡፡ ስለሆነም መምህሩ ጨዋታዎችን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ሲያስብ የተማሪዎችን የዕድሜ ፣ የባህል ወዘተ ልዩነት በመረዳት ችግሩን መፍታት ይጠበቅበታል፡፡

### 2.5.3 ችግሮችን አፍለቆ መፍትሄ መሻት /Simulation/

Bygate (1987፡80) ፅንሰ ሀሳቡ ውሳኔ ሰጭነት ተግባርን የሚገልፅ ሲሆን ተማሪዎች ራሳቸው ማህበራዊ ሚና እንዳላቸው በማሰብ የሚከናወን ተግባር ነው ፡፡ ተማሪዎች አንድን ሚና ተክተው የሚጫወቱት ተግባር ሳይሆን ችግሮችን በሀሳባቸው አፍልቀው የችግሮቹን አስገዳጅ ሁኔታዎች በቡድን የሚመረምሩበት ነው ፡፡ አንድን ችግር ለመፍታት የሚደረግ የኮሚቴ ስብሰባ ፣ በአንድ ችግር ዙሪያ ህዝባዊ ውይይት ማካሄድ ለዚህ ተግባር ጥሩ ምሳሌዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ምሁሩ ጠቅሰዋል፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ ተግባር ዋና አላማ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ችግሮች ከመፍታት ባለፈ ሳይታወቃቸው እርስ በርስ በሚያደርጉት ተራክቦ የመናገር

ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ሲሆን ለመለማመጃ የሚቀርቡት ተግባራትም የተማሪዎችን ችሎታ ማገናዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ Gower et al (1995፡107) እንደሚሉት በተግባሩ የሚነሱ ችግሮች ከተማሪዎች ዕድሜ ፣ ልምድ፣ ችሎታ ወዘተ ጋር ተገቢነት ያላቸው ከሆኑ ተማሪዎችን የማሳተፍ ኃይላቸው ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ተግባሩ በመካከለኛ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች በቡድን ሊቀርብ የሚችል ሲሆን የሚከተለው ዓይነት ተግባር ጥሩ መለማመጃ ሊሆን እንደሚችል ጠቅሰዋል፡፡ *የትምህርት ቤታችሁ ክበብ ከስረት ስለደረሰበት አፋጣኝ የሆነ የአሠራር ለውጥ ካልተደረገ በስተቀር ወደመዘጋት ደረጃ ይደርሳል፡፡ የትምህርት ቤታችሁ ክበብ ከመዘጋት ድኖ ስራውን እንዲቀጥል ለማድረግ በቡድን ተወያይታችሁ የመፍትሄ ሀሳብ አቅርቡ፡፡*

ከላይ የቀረበውን ተግባር ለማከናወን ሦስት ደረጃዎችን መከተል አስፈላጊ እንደሆነ Bygate (1987፡81) ይጠቅሳሉ፡፡ የመጀመሪያው አስፈላጊውን መረጃ የመስጫ ጊዜ ሲሆን ሁለተኛው ችግሩን ለመፍታት የሚከናወን ውይይት ነው ፡፡ የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ የመምህሩ ክትትል ነው ፡፡

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው እንደነዚህ አይነት መለማመጃዎች የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ከማዳበራቸውም በላይ የተማሪዎችን የችግር ፈቺነት አቅም ለማሳደግ ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሣደግ የክፍል ደረጃውን ያገናዘቡ መልመጃዎችን ወደክፍል መርጦ ማምጣትና ተማሪዎች እንዲለማመዱ ማድረግ ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

## 2.5.4 ታሪክ መናገር (Telling Stories)

Harmer (2007፡129) ስለራሳችንና ስለሌሎች ሰዎች ታሪኮች በመተረክ አብዛኛውን ጊዜአችንን እናጠፋለን ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች በቋንቋቸው ታሪክ መናገር መለማመድ አለባቸው በማለት ሂደቱን እንደሚከተለው አቅርበውታል፡፡

ተማሪዎች በቡድን በቡድን ይቀመጣሉ፡፡ ለእያንዳንዱ ቡድን ተከታታይነት ያላቸው መልዕክት አዘል ስዕሎች ይሰጣል፡፡ ቡድኖቹ ስዕሎቹን ከተመለከቷቸው በኋላ ይሰበሰባሉ ፣ ከዚያም ከመጀመሪያዎቹ ቡድኖች አንዳንድ አባል የያዙ ሌሎች አዳዲስ ቡድኖች ይደራጃሉ፡፡ አዲሶቹ ቡድኖችም ቀደም ሲል ያዩት ስዕላዊ መግለጫ ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ይናገራሉ፡፡ በመጨረሻም እያንዳንዱ ቡድን ያቀረበው ታሪክ ተመሳሳይ ሀሳብ የያዘ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ቡድኖች የየራሳቸውን ታሪክ ለክፍሉ ያቀርባሉ፡፡

በሌላ በኩል ተማሪዎች ታሪክ እንዲናገሩ ለማለማመድ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ተግባራት ለተገልጋዮቹ ህይወት ቅርበት ያላቸው መሆን እንደሚገባቸው Harmer (2007፡130) እንዲህ ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ "የተማሪዎችን የመተረክ ችሎታ ለማሳደግ የየራሳቸውን ሁኔታ ለምሳሌ በሰውነታቸው ላይ ስላለ ጠባሳ ፣ ስለፀጉራቸው ፣ ስለጌጦቻቸው ፣ ስለየትምህርት መሣሪያዎቻቸው፣ ስዕሎቻቸው ወይም ደግሞ ቀደም ሲል ስላሳለፉት በጎ ወይም መጥፎ ገጠመኝ ወዘተ እንዲተርኩ የሚያነሳሱ ጥያቄዎችን መምህሩ እንደመነሻ ቢጠቀም ውጤቱ በጣም የተሻለ ይሆናል" ይላሉ፡፡

Sesnan (1997፡116) ልጆች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ታሪክ እንዲናገሩ ማበረታታት አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ የሚከተሉት ዓይነት ታሪኮችን እንዲናገሩ ማድረግ ጠቃሚነት እንዳለው ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በፊት የሰሟቸውን ታሪኮች ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ፣የየራሳቸውን ታሪኮች ፈጥረው እንዲናገሩ ማበረታታት እና ስለአዩአቸው ወይም ስለአከናወኗቸው ነገሮች ለክፍሉ እንዲናገሩ እድል መስጠት የልጆችን የመተረክ ችሎታ ለማሣደግ ይረዳል፡፡

ስለዚህ መምህራን በየቋንቋው በቃል የሚተረኩ ወይም በፅሁፍ የቀረቡ ታሪኮች የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ያላቸውን ፋይዳ ተገንዝበው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚያቀርቡት ንግግር ታሪኮቹን በግብዓትነት እንዲገለገሉባቸው ማድረጉ የመናገር ክሂል አቀራረቡን ቀና እንደሚያደርገው በውል ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

## 2.5.5 ሚና ጨዋታ (Role Play)

ተማሪዎች የአንድን ግለሰብ ሚና (ለምሳሌ የአንድን መስሪያ ቤት ደንበኛ እና ስራ አስኪያጅ፣ የሱቅ ሻጪ እና ገዥ ወዘተ...) ተክተው የሚያከናውኑት ተግባር ሲሆን ሚና ጨዋታ ተማሪዎች ወክለው የተወኑትን ተግባር እንዲያስተውሉና ከአዳዲስ የቋንቋ አገላለፆች ጋር እንዲተዋወቁ ከመርዳቱም በላይ ተማሪዎች የቋንቋ ፍሰት ብቃታቸውን ማሻሻል እንዲችሉ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ መምህሩንም የተማሪዎችን ጥንካሬና ድክመት በመለየት መፍትሄ እንዲፈልግ ይረዳዋል ሲሉ Gower et al. (1995፡105) የሚና ጨዋታን ፋይዳ ጠቅሰዋል፡፡

ቀለል ያሉ ሚና ጨዋታዎች (ለምሳሌ ሸቀጣሸቀጦችን ከሱቅ መግዛት፣ አቅጣጫን ማሳየት የመሳሰሉት) በዝቅተኛ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች በጣም ጠቃሚ ተግባራት ሲሆኑ ውስብስብ የሆኑ ሚና ጨዋታዎች (ለምሳሌ በአንድ ታሪክ ውስጥ የተካተቱ ገፀባህርያትን

ወክሎ መጫወት) የክፍል ደረጃው ክፍ ላሉ ተማሪዎች ተስማሚ እንደሆኑ እኚሁ ምሁር አክለው ገልፀዋል። ስለዚህ ለተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ ተገቢነት ያላቸውን መለማመጃዎች መርጦ በክፍል ውስጥ ማቅረብ ከመምህሩን ይጠበቃል።

### 2.5.6 ውይይት (Disccussion)

ውይይት ከፍተኛ ዝግጅትን የሚጠይቅ ሲሆን በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ጋር የሚደረግ ውይይት ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉትን ነጥቦች ማረጋገጥ ሲቻል እንደሆነ Gower et al. (1995፡107 -108) አስረድተዋል።

- ተማሪዎች በሚወያዩበት ርዕሰ - ጉዳይ ሲቀስቅሱና የሚናገሩት ሀሳብ ሲኖራቸው፣
- ተግባሩ በአደረጃጀቱ የመናገር ፍላጐት ለመፍጠር በቂ የሆነ የማነሳሳት አቅም ሲኖረው፣
- ተማሪዎች ለውይይት የቀረበውን ጉዳይ መግለፅ የሚያስችል የቋንቋ ችሎታ ሲኖራቸው፣
- የተማሪዎቹ ለውይይቱ ዝግጁነትና ሀሳባቸውን ለማደራጀት የሚሰጠው ጊዜ ታሳቢነት፣
- የተግባሩ በሚፈለገው አግባብ መሄድ ማለትም ውይይቱ በተወሰኑ ተማሪዎች ተፅዕኖ አለመዋል።

በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ውይይቶች ተማሪዎችን በማነሳሳት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ከዕድሜያቸውና ከችሎታቸው ጋር የሚጣጣሙ የመወያያ ይዘቶችን ማዘጋጀት ተገቢ ነው። ከዚህ አኳያ Gower et al. (1994:108 -109) ውይይቶችን ለማነሳሳት ጠቃሚ መንገዶች ናቸው ብለው ከጠቀሷቸው ይዘቶች ውስጥ ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ሊመጥኑ የሚችሉ ይዘቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- **አባባሎችን ማሻሻል** ( Modifying statements ) ፡- ለተማሪዎች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ አከራካሪ አባባሎችን ዝርዝር በመስጠት በቡድን ተወያይተው ማሻሻያ እንዲያደርጉ ማድረግ ለምሳሌ ፡- *ወላጆች ወንድ ልጆቻቸውን የምግብ አዘገጃጀት ፣ ሴት ልጆቻቸውን ደግሞ የመኪና አጠጋገን ማስተማር አለባቸው።*
- **አባባሎችን ተከታታይነት ማስያዝ** (Sequencing statments)፡- ለተማሪዎች አወዛጋቢነት የሌለቸው አባባሎችን ዝርዝር (1-10 የሚደርሱ) ሰጥቶ እንደአፈፃፀማቸው ቅደም ተከተል እንዲያስይዙ ማድረግ

* **አባባሎችን መቃወም** (Defending statments)፡- የተለያዩ አከራካሪ አባባሎችን ለተማሪዎች በቁራጭ ወረቀት ላይ ፅፎ በመስጠት የመቃወሚያ ሀሳብ እንዲያዘጋጁ ጊዜ መስጠት ፣ ከዚያም ከመካከላቸው አወያይ መምረጥና እያንዳንዱ ተማሪ የመቃወሚያ ሀሳቡን በየተራ እንዲያቀርብ ማድረግ፣

ከላይ የመናገር ክሂልን ለማለማመድ ይረዳሉ ተብለው ከቀረቡት ተግባራት በተጨማሪ Harmer (2007 ፡ 129- 130) የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ማለማመድ የሚችሉ በርካታ ተግባራትን የጠቀሱ ሲሆን ከጠቀሷቸው ተግባራት ውስጥ በሌሎች ምሁራን ያልተጠቀሱትና የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ ተማሪዎችን ማለማመድ የሚችሉ ተግበራት ቀጥሎ ቀርበዋል።

* ተማሪዎች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ (ለምሳሌ ስለሰዎች የመኝታ ፣ የንባብ ልማድ ወዘተ) እርስ በርስ ቃለ መጠይቅ እንዲደራረጉ ማድረግ፣
* ተማሪዎች በሚፈልጉት ርዕሰ ጉዳይ መረጃ ሰብስበው በማደራጀትና በመለማመድ በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ማድረግ ወይም በቤታቸው ያነበቡትን ቅንጫቢ ወይም ሙሉ ስራ ማጠቃለያ በንግግር እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
* ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ ከሚደግፉት ሀሳብ አኳያ ወግነው እንዲከራከሩ ማድረግ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማዳበር ጥሩ የክፍል ውስጥ ተግባር ሲሆን ከንግግር ችሎታ በተጨማሪ የነገሮችን ተጠየቃዊ ግንኙነት የመመርመር ችሎታም ያደብራል።
* ተማሪዎች ዝግጅት ሳያደርጉ ለተወሰኑ ደቂቃዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በጓደኞቻቸው ፊት እንዲናገሩ ማድረግ (Sesnan, 1997፡116 )።
* ቅርፃቅርፆችን ፣ ስዕሎችን ፣ ፎቶግራፎችን በመጠቀም የሚደረግ ልምምድ የመናገር ክሂልን ለማስተማር ጉልህ ድርሻ እንዳለው ማረው (1998፡ 140-141) ጠቅሰዋል።

ለማጠቃለል Gower et al. (1995:103) እንዳሉት ተግባራቱ ለአመቺነት ሲባል ይከፋፈሉ እንጂ በተግባራቱ አከፋፈል ላይ መደራረብ ሊታይ ስለሚችል ክፍፍሉ የጠራ ነው ማለት እንደማይቻል ልብ ሊባል ይገባል። ስለዚህ ትኩረት መደረግ ያለበት ክፍፍሉ ላይ ሳይሆን የቀረቡት ተግባራት የመናገር ክሂልን ለማለማመድ ተገቢነት አላቸው ወይስ የላቸውም ? ከሚለው ላይ መሆን እንዳለበት ከምሁራኑ ገለፃ መረዳት ይቻላል። የትኞቹ ተግባራት ለየትኛው የክፍል ደረጃ ይዋሉ? ለሚለውም እንደዚሁ ግልፅ የሆነ ነገር ባብዛኛዎቹ ምሁራን ባይጠቀስም እንደየክፍል ደረጃው መጥኖ በማቅረብ አብዛኛዎቹን

ተግባራት ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው የክፍል ደረጃ መገልገል እንደሚቻል ምሁራኑ በአንድምታ ቢሆን መጠቆማቸውን መገንዘብ ይቻላል። ስለዚህ ከላይ የቀረቡትን የመናገር ክሂል መለማመጃዎች ከተማሪዎች ዕድሜ፣ የክፍል ደረጃ፣ አካባቢ ወዘተ ጋር በማጣጣም ለአፍመፍቻ ቋንቋ መጠቀም እንደሚቻል መምህራን በውል ሊገነዘቡት ይገባል።

## 2.6. የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች እና ችግሮቹን ለማስወገድ የሚረዱ ተግባራት

### 2.6.1 የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች

በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት በሚከናወንበት ወቅት ተግባሩን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎች በመምህሩም ሆነ በተማሪው የሚከሰቱ ችግሮች ይኖራሉ። ከመምህሩ አኳያ የማስተማር ችሎታ የብቃት ማነስ ፣ የዝግጅት ማነስ ፣ የክፍል አመራር ችሎታ ማጣት ወዘተ .. ሊጠቀሱ ሲችሉ፣ በተማሪዎች በኩል ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል ደግሞ ዋና ዋናዎቹ መታቀብ ፣ የሚናገሩት ነገር ማጣት ፣ ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያላማከለ ተሳትፎ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ መጠቀም እንደሆኑ Ur, (1996፡ 121) እና ቅማዩኮ (2006:26-27) ገልፀዋል። ከተጠቀሱት ችግሮች ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚለው የሁለተኛ ቋንቋን በመማር ወቅት የሚከሰት ስለሆነ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት የሚከሰቱ ችግሮች ብቻ እንደሚከተለው ቀርበዋል ።

**ሀ. መታቀብ** (Inhibition) ፡- የሚናገር ሰው ከሚያዳምጥ ፣ ከሚያነብ ወይም ከሚፅፍ ሰው የበለጠ የሌሎችን ትኩረት ይስባል። በመሆኑም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ እንሳሳታለን በሚል አመለካከት የፍርሃት ስሜት ስለሚያድርባቸው ከመናገር ይቆጠባሉ። በተጨማሪም ትችትን በመፍራትና ንግግራችን የሌሎችን ስሜት መሳብ አይችልም በሚል እምነት ሀሳባቸውን በውስጣቸው አምቀው የመያዝ ባህርይ ይታይባቸዋል። በዚህም የተነሳ በክፍል ውስጥ ለንግግር በሚዘጋጁ ተግባራት በፈቃደኝነት አይሳተፉም።

**ለ. የሚናገሩ ነገር ማጣት** (Nothing to say) ፡- ተማሪዎች የመናገር ፍላጐት እያላቸው አንዳንድ ጊዜ ለንግግር ስለተመረጠው ጉዳይ በቂ መረጃ ስለማይኖራቸው ለመናገር አይደፍሩም ። ተማሪዎቹ ለንግግር በተመረጠው ርዕሰ - ጉዳይ ዙሪያ በቂ ዳራዊ ዕውቀት ከሌላቸው (የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ፣ ፍላጐት ያላገናዘበ ከሆነ) ለመናገር ግላዊ ፍላጐትና ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡ ይህ ዓይነቱ

ሁኔታ በተደጋጋሚ ከተከሰተ ተማሪዎች ለንግግር ስር የሰደደ ጥላቻ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡

ሐ. **ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያላማከለ ተሳትፎ** (Low or uneven participation) ፡- አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራት በአንድ ጊዜ የሚያሳትፉት አንድ ተማሪ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ በርካታ ተማሪዎችን በንግግር ተግባር ላይ ማሳተፍ ለቋንቋ ትምህርት ከተመደበው ጊዜ ጋር ሊጣጣም የማይችል ተግባር ነው ፡፡ ይህም ሁኔታ የተወሰኑ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባርን በመቆጣጠር የሌሎች ተሳትፍ ውስን እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## 2.6.2 የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥው ችግሮችን ለማስወገድ የሚጠቅሙ ተግባራት

Ur (1996፡121) እና ቅማዩከ (2006:28-29) ንግግርን በማስተማር ሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች የሚከተሉትን ተግባራት በመፍትሄነት የጠቆሙ ሲሆን ከአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ማስተማር ጋር ግንኙነት ያላቸው ብቻ ቀጥሎ ቀርበዋል ፡፡ ተግባራቱም፡-

ሀ. **የቡድን ስራ መጠቀም** (Use group work) ፡- የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራትን ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲያካሄዱ ማድረግ በልምምዱ የሚናገሩ ተማሪዎች ቁጥር ይጨምራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በክፍሉ ተማሪዎች ፊት ቆመው ለመናገር የሚፈሩና የሚያፍሩ ጭምት ተማሪዎች በአራትና በአምስት ተማሪዎች አድማጭነት ንግግር እንዲለማመዱ እድል ይሰጣል፡፡ ስለዚህ የሁሉንም ተማሪዎች ተሳትፎ ለማጎልበት መምህራን ትኩረት ሊሰጡና ሊከታተሉ ይገባል፡፡

ለ. **ተግባሩ/መልመጃው በቀላል ቋንቋ እንዲቀርብ ማድረግ** (Base the activity on easy language)፡- አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች ጥሩ ይናገራሉ ብለው የሚገምቷቸውን ሰዎች ንግግር አስመስሎ ለመናገር የሚሞክሩበት ሁኔታ አለ ፡፡ ሁኔታው ተማሪዎች ሊገልፁት በሚፈለጉት ጉዳይ ላይ ሙሉ ትኩረታቸውን እንዳያሳርፉ እንቅፋት ይሆናል፡፡ በሚናገሩት ሀሳብና በቋንቋ አጠቃቀማቸው መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዳይኖርም ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላለፅ ችሎታ ተጠቅመው እንዲያቀርቡ ማድረግ የንግግርን ተግባር ከባድ አድርገው እንዳያስቡት ያደርጋል ፤ በራስ የመተማመን ደረጃቸውንም ከፍ ያደርጋል፡፡

**ሐ. ፍላጎትን ለማነሳሳት ሳቢና አነቃቂ የመወያያ ርእስ ወይም ተግባር መምረጥ** (Make careful choice of topic and task to stimulate interest) ፡- ለተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር የሚመረጥ ርዕስ ወይም የሚዘጋጅ መልመጃ ግልፅ ፣ ሳቢ ፣ ተማሪዎችን ለንግግር የሚያነሳሳና ሊያነጋግር የሚችል ሰፊ ሀሳብ የያዘ መሆን ይኖርበታል። ርዕሱ የተመረጠው ወይም መልመጃው የተዘጋጀው የተማሪዎችን ፍላጐት መሰረት አድርጐ ከሆነ የተማሪዎች ተሳትፎ ይጨምራል።

**መ. የንግግር ክሂልን በሚመለከት መመሪያ ወይም ትምህርት መስጠት** (Give some instruction or training in discussion skills ) ፡- ተግባሩ በቡድን ውይይት የሚከናወን ከሆነ ፣ ተግባሩ ከመጀመሩ በፊት የተማሪዎች ተሳትፎ ምን መምሰል እንዳለበት መመሪያ መስጠት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ያህል እያንዳንዱ ተማሪ በቡድኑ ውስጥ መሳተፍ እንዳለበት ፣ የቡድኑን ውይይት የሚያመቻች የቡድን መሪ መምረጥ አስፈላጊ መሆኑን ማወቅ አለባቸው። ተማሪዎች ይህንን ማወቃቸው የተወሰኑ ተሳታፊ ተማሪዎች ብቻ ብዙውን የልምምድ ጊዜ እንዳይወስዱና ጭምት ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይረዳል ። መምህራንም በልምምዱ ሂደት ለልምምዱ የተመለከተው መመሪያ ተግባራዊ መሆኑን መከታተል አለባቸው ። ስለዚህ የመናገር ክሂልን የክፍል ውስጥ ክንውን ውጤታማ ለማድረግ በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተራክቦ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮችን ለመቀነስ ከላይ በመፍትሄነት የቀረቡትን ነጥቦች ተግባራዊ ማድረግ ለነገ የማይባል ጉዳይ መሆኑን መምህራን በውል ሊገነዘቡት ይገባል።

## 2.7 የክፍል አመራር

የክፍል አመራር የሚለው ፅንሰ - ሀሳብ የመምህሩን ሚና ፣ የተማሪውን አቦዳደን (አደረጃጀት) እና የዲስፕሊን ችግርን እንደሚያመለክት Harmer, (1991:235) ይገልፃሉ። የክፍል አመራር ችሎታ የመምህሩንና መምህሩ ለትምህርቱ የሚገለገልባቸውን ተግባራት ስኬታማነት ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ጠቃሚ ነው ። በጣም ውጤታማ የሆኑ ተግባራት መምህሩ በተገቢው ሁኔታ ካላደራጃቸው ዋጋ ሊያጡ ስለሚችሉ በመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል አመራር እጅግ ወሳኝ ነው ። ስለሆነም በቋንቋ ትምህርት ክፍል የተማሪዎች አደረጃጀትና የመምህሩ ሚና ምን መምሰል እንዳለበት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 2.7.1 በመናገር ክሂል አቀራረብ የክፍል አደረጃጀት

መምህራን የሚያስተምሩትን ክፍል የማደራጀት ችሎታና ቴክኒክ ሊኖራቸው ይገባል። እንዲህ ዓይነቱ ተግባር በጥቅሉ የክፍል አመራር በመባል እንደሚታወቅ Scrivener, (1994፡9) የጠቀሱ ሲሆን ጥሩ የክፍል አመራር ምቹ የመማር አውድ በመፍጠር ተማሪዎች ሳይሸማቀቁ ሀሳባቸውን በንግግር እንዲገልፁ የማበረታታት ሀይሉ በጣም ከፍተኛ ነው ።

የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ አቀማመጥ በሚመለከት Scrivener, (1994፡94) የፈረስ ኮቴ አቀማመጥ ለቋንቋ ትምህርት ክፍል ተስማሚ እንደሆነ ይገልፃሉ። በፈረስ ኮቴ አቀማመጥ አንዱ ተማሪ ሌላውን ማየት ስለሚችል ተማሪዎቹ በቡድኑ ውስጥ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ እንዲሳተፉ ያግዛል። ይህ ዓይነቱ አቀማመጥ በተማሪዎች መካከል የእኩልነት ስሜት ከመፍጠሩም በላይ ደከም ያሉ ተማሪዎች እንዳይደበቁና በጉበዝ ተማሪዎች እንዳይዋጡ ይረዳል።

የጥንድ ፣ ትንንሽ ቡድኖች እና ክፍሉን በአንድ ማድረግ (whole class organization) በጣም የተለመዱ የቋንቋ ትምህርት አረደጀቶች ሲሆኑ ከእነዚህ አደረጃጀቶች መካከል ለዕለቱ ትምህርት ተገቢነት ያለውን አደረጃጀት መምህሩ መርጦ መጠቀም እንደሚችል Bygate, (1987፡97) እና Scrivener, (1994፡13) ጠቁመዋል።

በቡድኖች ውስጥ መካተት የሚገባቸውን ተማሪዎች ቁጥር በሚመለከት በተለያዩ ምሁራን የተለያየ አህዝ የሚጠቀስ ሲሆን Sesnan (1997፡175) ግን በአንድ የቋንቋ ክፍል ውስጥ የሚደራጁ ቡድኖች ከአራት እስከ አምስት አባላት በውስጣቸው ቢይዙ ተመራጭነት እንዳለው ይጠቅሳሉ። አደረጃጀቱም በትምህርታቸው ደከም ያሉትንና ጉበዝ ተማሪዎች መያዝ አለበት ይላሉ። ምክንያቱም ደከም ያሉትን ተማሪዎች ከጉበዞች ጋር ሲሆኑ ያሉባቸውን ችግሮች ሁሉ ተቋቁመው ከጓደኞቻቸው ለመማር የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ስለሚሆን ነው ።

በሌላ በኩል Harmer (1991 ፡ 246) እንደሚሉት አንዳንድ ጊዜ በትምህርታቸው ጠንከር ያሉትንና ደከም ያሉትን ተማሪዎች ለየብቻቸው ማደራጀት ተማሪዎቹ በራሳቸው ፍጥነት ስለሚማሩ ጠቃሚ እንደሆነ በመግለፅ በቡድኖቹ ውስጥ ከስባት በላይ ተማሪዎች ከተካተቱ የቡድን አባላቱን ተሳትፎ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ እንደሚሆን ያስገነዝባሉ። ስለዚህ

መምህሩ አንድ ብቸኛ መንገድ እንደሌለ ተገንዝቦ አደረጃጀቱን በሚያመቸው ዘዴ ሊያከናውነው እንደሚችል መገንዘብ ይኖርበታል፡፡

አደረጃጀቱ ምንም ይሁን ምን በተማሪዎች መካከል እንዲሁም በተማሪዎች እና በመምህሩ መካከል የተዝናና የመማር ሁኔታ መፍጠር፣ ገለፃ ከማድረግ ይልቅ የሚያወያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅና የማሰቢያ ጊዜ መስጠት ፣የተማሪዎችን የመናገሪያ ጊዜ (Student Talking Time) ከፍ ማድረግ፣ ተማሪዎች እንዲናገሩ ለማድረግ የጥንድ ፣ የሶስተዮሽና የቡድን ስራ መጠቀም እና ተማሪዎች ለትምህርታቸው መሻሻል ሀላፊነት እንዲወስዱ የሀላፊነት ስሜት መፍጠር ፣ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ መስተጋብራዊ ግንኙነት ከፍ ለማድረግ ጉልህ ድርሻ እንዳለው Scrivener, (1994፡15) ጠቁመዋል፡፡

## 2.7.2 የመምህራንና የተማሪዎች ሚና በመናገር ክሂል አቀራረብ

ሚና (Role) መምህራንና ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ክፍል የሚጠበቅባቸውን ተግባራት ለማከናወን ያላቸውን ድርሻ እንዲሁም በተማሪዎች መካከል ያለውን ማህበራዊ የርስ በርስ ግንኙነት የሚመለክት ፅንሰ - ሀሳብ እንደሆነ Nunan, (1991፡79) ጠቅሰዋል፡፡ በጥንታዊ የቋንቋ የማስተማር ዘዴ የክፍል ውስጥ ክንውን ጐልቶ የሚታየው በመምህሩና በተማሪው መካከል ሲሆን በተማሪዎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት ዝቅተኛ በመሆኑ ተማሪዎች ስለሚማሩት ትምህርት ያላቸው ግንዛቤና ሚና ዝቅተኛ እንደነበር እኚሁ ምሁር ያስረዳሉ፡፡

የኋላ ኋላ ግን የተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ እድገት እያሳየ መምጣት በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ የተማሪዎች ሚና ተቀባይነት እንዲኖረው በጎ ተፅዕኖ አድርጓል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይ በጥንድ ፣ በቡድን በሚከናወኑ የክፍል ውስጥ ቃላዊ ተራክቦ ተግባራት እውነትነት እንዳለው ማረጋገጥ እንደሚቻል Nunan (1991፡86) ገልፀዋል፡፡ የመምህር ተማሪ ተራክቦ በብዙ መንገድ ተደጋጋፊ ሲሆን አፅንኦት ለመስጠት ያህል የእያንዳንዳቸው ምንነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 2.7.2.1 የመምህራን ሚና

Nunan (1991፡84) Richards and Rodgers (1986)ን በመጥቀስ "አንዳንድ የቋንቋ የማስተማሪያ ዘዴዎች ሙሉ በሙሉ መምህር ተኮር ሲሆኑ ፡ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎች ደግሞ መምህሩን እንደትምህርት አቀጣጣይ ፣ አማካሪ፣ ወይም መሪ ይቆጥሩታል" ይላሉ፡፡ አያይዘውም የመምህሩ ሚና መምህሩ ሊያሳካቸው ከሚፈለገው አላማዎች፣

እንዲሁም በመምህሩና በተማሪዎች መካከል ሊጐለብት ከሚፈለገው መስተጋብራዊ ግንኙነት አንፃር ሊወሰን እንደሚችል ይገልፃሉ።

በተጨማሪም Nunan (1991፡87) Breen and Candlin (1980)ን በመጥቀስ "አንድ መምህር በተግባቦታዊ የቋንቋ ክፍል ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ሚናዎች እንዳሉት ጠቅሰዋል። የመጀመሪያው በተግባቦታዊ ሂደቱ አመቻች መሆን ፡ ሁለኛው ሚናው ደግሞ ተሳታፊነት ሲሆን፣ የመጨረሻው ተግባሩ የመማር ሂደቱን መከታተልና ተማሪ መሆን ነው" ይላሉ።

በአጭሩ አንድ የቋንቋ መምህር በቡድን ስራ ወቅት ተማሪዎች የሚያከናውኑትን ተግባር በመከታተል ማበረታታት ፣ ተማሪዎች ሌሎች የቡድኑ አባላት ለሚሰነዝሩት ሀሳብ ከበሬታ መስጠት እንዳለባቸው መምከር ፣ የቡድን አባላት ስህተት አንዱ የመማሪያ መንገድ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማድረግና ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት ፤ የመረጃ ምንጭ በመሆን የክፍሉን መስተጋብራዊ ግንኙነት ከፍ በማድረግ የተማሪዎች የንግግር ችሎታ እንዲጐለብት ማድረግ ይጠበቅበታል።

ተማሪዎች የመናገር ክሂልን በሚፈለገው ደረጃ እንዲያሳድጉ ለማድረግ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ መምህራን የተለያዩ ውጫዊ ችግሮችን ተቋቁመው ማለፍ እንዳለባቸው Byrne, (1976፡1) ያሳስባሉ። አያይዘውም የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት ከሚያጋጥሙ ችግሮች ውስጥ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት ፣ የክፍሉ አደረጃጀት (የወንበሮች አቀማመጥ ለተግባቦት አመቺ አለመሆን) የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚሰጠው ጊዜ ማነስ እና የመርሀ ትምህርቱ አቀራረፅ በተለይም ፈተናዎች ለንግግር ቋንቋ አመዛዘን ትኩረት አለመስጠታቸው ጥቂቶቹ እንደሁኑ ጠቅሰዋል።

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ባሉበት ሁኔታ የመናገር ክሂልን ማስተማር ምን ያህል ከባድ እንደሆነ መረዳት አያስቸግርም ። ስለዚህ መምህራን ችግሮቹን በወጉ ለይተው በመረዳት የተለያዩ ቴክኒኮችንና ያሠራር ስርዓቶችን (Procedures) ማመቻቸት ጠቃሚ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

Byrne (1976፡1-2) የአንድ የቋንቋ መምህር ተግባር በክፍል ውስጥ የተሻለ የመማር ሁኔታዎችን መፍጠር ነው ። ከዚህ አጠቃላይ ተግባር በተጨማሪ አንድ መምህር በመናገር ክሂል አቀራረብ የተለያዩ ደረጃዎች፣ የሚከተሉት ሚናዎች እንዳሉት ይገልፃሉ።

### ሀ. በአቀራረብ ደረጃ

በአቀራረብ ደረጃ መምህሩ የመረጃ አቀባይነት ሚና ይኖረዋል፡፡ ለትምህርት የሚቀርበውን ማቴሪያል /ተግባር/ መምረጥና የተመረጠውን ማቴሪያል ግልፅነትና አይረሴነት ባለው መንገድ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ደረጃ ብዙ ጊዜ ማጥፋት ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ቋንቋውን የሚለማመዱበትን ጊዜ ስለሚሻማ ተገቢነት የለውም (Byrne, 1976፡2)፡፡

መንግስቱ (1997፡24) እንደገለፀው በዚህ ደረጃ የንግግር ትምህርት በምንባብ መልክ ወይም በምልልስ ሊቀርብ ይችላል፡፡ **ለምሳሌ**፦ መምህሩ ውይይትን በማስተማሪያነት ለመጠቀም ከፈለገ በቅድሚያ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ሰዎች ሲወያዩ የሚያሳይ ይዘት ማቅረብ ወይም ከእለቱ ምንባብ ርዕስ ጋር የተያያዙ አጫጭር ምንባቦችን በማምጣት ወይም በምልልስ ሊያቀርብላቸው ይገባል፡፡

### ለ. በልምምድ ደረጃ

ይህ ደረጃ ተማሪዎች አብዛኛውን የመናገር ተግባር የሚያከናውኑበት ነው፡፡ የመምህሩ ተግባር ልምምዶችን በተቻለ መጠን ማዘጋጀትና ማቅረብ ነው፡፡ ልምምዶቹም ትርጉም ያላቸውና አይርሴነት የሚፈጥሩ ሊሆኑ ይገባል፡፡ መምህሩ ብዙ ከመናገር በመቆጠብ ተማሪዎች በልምምዱ እንዲሳተፉ እድል መስጠትና አፈፃፀማቸው አጥጋቢ መሆኑን መከታተል (Monitor) ይጠበቅበታል Byrne, (1976፡2)፡፡

በዚህ ደረጃ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማለማመድ የሚከተሉትን ተግባራት ማቅረብ ተገቢነት እንዳለው Byrne (1976 ፡ 39 - 43) ጠቅሰዋል፡፡

- ገምተው እንዲናገሩ የሚያስችሉ መልመጃዎች (Guessing drills) ፦ ለተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት መሰረት የሆኑት ቀለል ያሉ የመረጃ ክፍተት ሁነቶች በተለይም ጨዋታዎች ለዚህ ተግባር ማሳኪያ ሊውሉ ይችላሉ ፡፡ ለምሳሌ ያህል፦ ተማሪዎች በጣም የሚወዱትን ቀለም ፣ የስፖርት ዓይነት ፣ እንስሳ እንዲያስቡና እንዲነጋገሩ ማድረግ፣ ተማሪዎች ባለፈው የሳምንቱ የመጨረሻ ቀን ወይም ምሽት የሠሩትን በየተራ እንዲጠያየቁ ማድረግ እና ራሳቸውን እንደአዛውንት በመቁጠር ወጣት በነበሩበት ወቅት የሚወዱትን ሙያ እንዲያወሩ ማድረግ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

* መላመምታዊ ሁነቶች (Imaginary situation) ፦ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ቢያጋጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ? በማለት በጉዳዩ ላይ እንዲነጋገሩ ማድረግ ፤ ለምሳሌ ሎተሪ ቢደርሳችሁ ገንዘቡን ምን ታደርጉታላችሁ ?
* ክፍት ምላሾች (Open - ended respenses)፦ ለተማሪዎች የመነሻ ሀሳቦችን ሰጥቶ ሀሳቡን በተለያየ መንገድ እንዲያሟሉ ማድረግ ወዘተ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

ሐ. በአፍልቆት ደረጃ

ተማሪዎች ከመምህሩ ትዕዛዝ ነፃ ሆነው ቋንቋውን እንደፈለጉት የሚጠቀሙበት ፤ ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለፅ የሚጥሩበት ነው። ስለሆነም መምህሩ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገለፁ የሚረዱ ተግባራትን በመስጠት የመምራትና የማማከር (Manger and guide) ሚናን መጫወት አለበት Byrne (1976፡2) ።

በተጨማሪም መምህሩ ተማሪዎች የራሳቸውን የቋንቋ ዕውቀት (የቃላት ምርጫ ፤ የሰዋሰው ህግ .....) ተጠቅመው ሀሳባቸውን የሚገልፁበት ዕድል ማመቻቸት ይጠበቅበታል። ይህንንም ተግባር ከግብ ለማድረስ ውይይቶችንና ክርክሮችን በማደራጀት በስዕሎች ፤ በፎቶግራፎች ..... ላይ ተንተርሰው ሀሳባቸውን እንዲያንሸራሽሩ ማበረታታት፣ ስዕሎችን በማቅረብ የሚያስተላልፉትን መልእክት እንዲናገሩ ማድረግ እንደሚኖርበት Byrne, (1976፡ 80 -91) ጠቅሰዋል።

ከላይ የተገለፁት የአቀራረብ ደረጃዎች በቋንቋ ትምህርት ተግባቦታዊ ችሎታን ለማሳደግ የተሞከሩና በአብዛኛው ውጤታማ አቀራረቦች ቢሆኑም ደረጃዎቹን የሙጥኝ ብለን መከተል እንደሌለብን Byrne (1976፡3) ያስርዳሉ። የተማሪዎች የትምህርት ደረጃ መምህሩ የአቀራረብ ደረጃዎቹን እንዳለ መጠቀም እንደሌለበት ጠቋሚ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነጥብ መሆኑ ልብ ሊባል እንደሚገባ ምሁሩ አያይዘው ገልፀዋል።

Scrivener (1994፡ 29-30) በበኩላቸው አንድ የቋንቋ መምህር በክፍል ውስጥ የሚከተላቸውን የመናገር ክሂል አቀራረብ ቅደም ተከተላዊ መንገዶች (Route - map) እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ።

* ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት / Before the lesson / ፦ ይህ መምህሩ ወደክፍል ከመግባቱ በፊት የሚያደርገው ቅድመ ዝግጅት ነው።

1. በዚህ ደረጃ መምህሩ ራሱን ከማቴሪያሉና ከተግባራቱ ጋር ማስተዋወቅ ፣ በአቀራረቡ ምን ያህል የአደረጃጀት ደረጃዎች እንደሚካተቱና ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስዱ መወሰን ፣ በእያንዳንዱ ደረጃ የመምህሩ ሚና ምን እንደሚሆን መለየት ፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ መሠረታዊ ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ ማሰብ ይኖርበታል፡፡

- ትምህርቱ በመከናወን ላይ እያለ ( In the lesson) ፡-

2. ቅድመ - ተግባር (Pre- activity) ፡- ተማሪዎቹ ወደተግባሩ የሚያስገባ ሂደት ሲሆን መምህሩ የተማሪዎቹን ፍላጐት ለማነሳሳት የሚገለገልበት ነው፡፡
3. ተግባሩን ማዘጋጀት (Set - up the activity):- ተማሪዎቹ ተግባሩን እንዲያከናውኑ በቡድን ማደራጀትን ፣ ለተግባሩ ግልፅ መመሪያ መስጠትን የሚመለከት ነው፡፡
4. ተግባሩን ማከናወን (Run the activity ):- ተማሪዎች ተግባሩን ያለምንም ጣልቃ ገብነት የሚያከናወኑበት ሲሆን በዚህ ደረጃ የመምህሩ ተግባር መከታተል ነው ፡፡
5. ተግባሩን ማጠቃለል (Close the activity):- ተማሪዎቹ በጥንድ ወይም በቡድን የሚያከናወኑትን ተግባር መጨረሻቸውን በማረጋገጥ ማጠቃለያ የሚሰጥበት ነው፡፡
6. ድህረ - ተግባር፡- (Post - activity):- የምጋቤ ምላሽ አላማ በርካታ ተማሪዎች በንግግር ተሳትፎ እንዲያደርጉ መርዳት ስለሆነ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ የተለያዩ ቡድኖችን አስተያየት ማወዳደር ፣ መልሶችን ማረጋገጥ ፣ የተነሱ ችግሮችን ማየት፣ የአተገባበሩን አላማ ማወያየትን የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡

**የአተገባበሩ ቅደም ተከተላዊ ሂደት በስዕላዊ መግለጫ የሚከተለውን ይመስላል ፡-**




*Scrivener (1994:29-30)*

Gower et al. (1995:102-103) ከላይ የቀረበውን ሀሳብ በማጠናከር የመናገር ክሂል አቀራረብ ክንውን ቅደም ተከተል ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት (Befere the lesson) ፣ ተግባሩ በመከናወን ላይ እያለ (During the activity) እና ከተግባሩ ክንውን በኋላ (After the activity) የሚሉ ደረጃዎችን መከተል እንዳለበት ይገልፃሉ፡፡ የመጨረሻው ተግባር

(After the activity) የሚለው በምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ላይ እንደሚያተኩር ምሁሩ የገለፁ ሲሆን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ ከስህተቶች ይልቅ መሻሻልን በሚጠቁሙ ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንደሚገባ ጠቁመዋል።

**መ. ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ / Giving feed back /**

እንደ Gower et al. (1995:163) እምነት በመናገር ክሂል አቀራረብ ምጋቤ ምላሽ መስጠት በጣም ጠቃሚ ከሆኑ የመምህራን ተግባራት ውስጥ አንዱ ነው። ቀጣይነት ያለው የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የተማሪዎችን ስኬትና ዕድገት ለመገምገም ይረዳል። የምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ የተለያዩ መንገዶችን የሚከተል ሲሆን ምስጋናና ማበረታቻ እንዲሁም እርማት መስጠት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ አላማ ግንዛቤንና መሻሻልን መፍጠር ሲሆን የቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ከድክመት ይልቅ ጥንካሬን መነሻ በማድረግ አስተያየቱ ቢሰጥ የተሻለ ይሆናል። ለምሳሌ ያህል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በትክክል መግለፃቸውንና በጓደኞቻቸው መደመጣቸውን ፣ የአዳዲስ ቃላትንና የድምፅ ቅላፄ አጠቃቀማቸውን መነሻ ማድረግ ይቻላል።

የእርማት አሰጣጥን በሚመለከት ደግሞ እርማቱን ራሱ ስህተቱን የሰራው ተማሪ፣ ሌሎች የክፍሉ ተማሪዎችና መምህሩ ሊያከናውኑት ይችላሉ። በቅድሚያ ግን ተማሪው ራሱን እንዲያርም እድል መስጠት አስፈላጊ ነው። ተማሪው የስህተቱን ምንጭ ካልተረዳው ሌሎች የክፍሉ ተማሪዎች እንዲረዱት ማድረግ ሌላው መንገድ ነው ። ምክንያቱም እንዲህ አይነቱ አካሄድም ሁሉም ተማሪዎች በእርማት አሰጣጡ ሂደት እንዲሳተፉ፣ የመማር ማስተማሩ የበለጠ ትብብራዊ እንዲሆንና ተማሪዎች በመምህሩ ላይ ያላቸውን የጥገኝነት ስሜት እንዲቀንሱ ለማድረግ ይጠቅማል Gower et al. (1995:169) ።

ለማጠቃለል የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ የአቀራረብ ቅደም ተከተሎችን ለማየት ተሞክሯል። ለምሳሌ Byrne (1976) የመናገር ክሂል አቀራረብ ሶስት ደረጃዎችን ማለትም የአቀራረብ ፣ የልምምድና የአፍልቆት ደረጃዎችን መከተል እንዳለበት በአጽንኦት የጠቀሱ ሲሆን ፣ Scrivener (1994) እና Gower et al. (1995) ደግሞ መምህራን የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ ለማቅረብ ከሚያከናውኗቸው ዝርዝር ተግባራት በተጨማሪ መምህራን ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት የሚያከናውኑትን

ቅድመ ዝግጅት እንዲሁም የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ክንውኖችንም ጭምር ለማሳየት ሞክረዋል።

ስለዚህ ከላይ የቀረቡትን ተግባራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተለይም የዚህ ጥናት ተተኳሪ መምህራን ማወቃቸው በመጀመሪያ ደረጃ ያለበቂ ዝግጅት ተንደርድረው ወደ ክፍል ከመግባት በመቆጠብ የመናገር ክሂልን ለማቅረብ የሚረዱ ቅድመ - ዝግጅቶችን በውል እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል። በመቀጠልም የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ መከተል የሚገባቸውን ደረጃዎች (የአቀራረብ፣ የልምምድ፣ የአፍልቆት፣ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ) መምህራን ለይተው እንዲያውቁና እንዲተገብሯቸው ይጠቅማቸዋል።

ስለሆነም የመናገር ክሂል የአቀራረብ ደረጃዎችን መምህራን ማወቃቸው በአቀራረብ ደረጃ የዕለቱን ትምህርት አላማ ለማስተዋወቅ ፣ የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት ለማነሳሳት፣ ተማሪዎች ስለሚያከናውኑት ተግባር አጭርና ግልፅ መመሪያ ለመስጠት ይረዳቸዋል። በልምምድ ደረጃ ደግሞ ተማሪዎች ወደ አፍልቆት ደረጃ ከመሸጋገራቸው በፊት በጥንድ ፣ በቡድን በመሆን በመምህሮቻቸው መሪነትና አመቻችነት መለማመዳቸው ስለሚከራከሩበት ወይም ስለሚወያዩበት ጉዳይ እርስ በርስ በሚያደርጉት መስተጋብር በቂ ግብአት ለማግኘት ይረዳቸዋል። መድረክ ወጥተው መናገር የሚፈሩ ተማሪዎችም የሚናገሩበት ዕድል ለማንግኘት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርላቸው ተገንዝበው በስራ ላይ እንዲያውሉት ያግዛቸዋል። በአፍልቆት ደረጃም ቢሆን ተማሪዎች ሀሳባቸውን ያለመምህሩ ጣልቃገብነት በነፃነት የሚገልጹበትን ዕድል የሚያገኙበት መሆኑን መምህራን አውቀው ከእነሱ የሚጠበቀውን ሁሉ ለማድረግ ግንዛቤ እንዲጨብጡ አስተዋጽኦ ያደርግላቸዋል። በመጨረሻም ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች በቀረበው ትምህርት ላይ አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ የእነሱን ሀሳብ መነሻ አድርጎ ማጠቃለያ መስጠት የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት ለማዳበርና ሀሳባቸውን በንግግር የመግለፅ ብቃታቸውን ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማየት እንደሚረዳ መምህራን ተገንዝበው እንዲተገብሩት ይረዳቸዋል።

### 2.7.2.2 የተማሪዎች ሚና

በመናገር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ማቴሪያል መረዳታቸውን ለማሳየት የሚያደርጉት የክፍል ውስጥ መስተጋብራዊ ግንኙነት የተለያየ ሊሆን ይችላል ። Lee (1979:59) የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ በተማሪዎችና በመምህሩ፣ በራሳቸው በተማሪዎች መካከል ሊሆን እንደሚችል ገልፀዋል ። ስለዚህ ተማሪዎች

ለሚማሩት ትምህርት ሀላፊነት ያለባቸው መሆኑን ተገንዝበው የንግግር ክሂላቸውን ለማሳደግ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## 2.8. የመምህር - ተማሪ ተራክቦ ውቅሮች (Teacher-Student Interaction Patterns)

Ur (1996፡227) በቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ መስተጋብር በመምህሩን እጅ ብቻ መውደቅ እንደሌለበትና ተማሪዎችም ጉልህ የሆነ ተሳትፎ ሊኖራቸው እንደሚገባ ያሳስባሉ። እኚሁ ምሁር የመናገር ክሂል አቀራረብ ተራክቦ ውቅር የመምህር ንግግር ብቻ (Teacher Talk) ፣ የመምህር - ተማሪ ተራክቦ (Teacher-Student interaction) ፣ የተማሪዎች የእርስበርስ ተራክቦ (Student-Student interaction) ገፅታ ሊኖረው እንደሚችል ጠቁመዋል። ስለዚህ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ መምህሩን የራሳቸውን የንግግር ጊዜ በመቀነስ የተማሪዎችን የንግግር ጊዜ ከፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የተማሪዎች የርስበርስ መስተጋብር ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው ለማድረግም ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ማድረግና የቡድን ስራ ማበረታታት ያስፈልጋል።

በምዕራፍ አንድ እንደተጠቀሰው የጥናቱ አጠቃላይ አላማ በደብረ ብርሃን ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂልን ሲያቀርቡ የታዩ ችግሮችን ለይቶ የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ ነው ። ስለሆነም ጥናቱ ይዟቸው የተነሳውን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ቀደም ሲል በዚሁ ምዕራፍ እንደተገለጸው Byrne (1976) ፣ Scrivener (1994) እና Gower et al. (1995) የጠቀሷቸውን የመናገር ክሂል አቀራረብ ደረጃዎች እንዲሁም Ur (1996) ያቀረቡትን የመምህር - ተማሪ ተራክቦ ውቅሮች፣ በመናገር ክሂል አቀራረብ የሚከሰቱ ችግሮችን በዋናነት መሠረት በማድረግ መረጃ ይሰበሰባል፤ የምዕራፍ አራት ትንተናም በዚሁ መሠረት ይከናወናል። ለመረጃ መሰብሰቢያ የሚውሉ መሳሪያዎችም የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብን ግምት ውስጥ በማስገባት ተጣጥመው እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ ዓይነታዊ ምርምር (Qualitative Research) ን በዋናነት የሚጠቀም ሲሆን መጠናዊ ምርምርን (Quantitative Research) ን ደግሞ በደጋፊነት ይጠቀማል፡፡ Dcrnyei (2007፡32) እንደሚሉት የዓይነታዊ ምርምር መረጃዎች ከቃለ - መጠይቅ፣ ከተለያዩ ዓይነት ቴክስቶች (ለምሳሌ ከመስክ ምልከታና ከውሎ ማስታወሻዎች ፣ ከመዛግብት) ፣ ከምስሎች (ለምሳሌ ከፎቶ ወይም ከቪዲዮ) የሚገኝ ስለሆነ ጥናቱ ባብዛኛው በገለጣዊ ዘዴ ይቀርባል፡፡

## 3.1 የናሙና አመራረጥ

### 3.1.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በአማራ ክልላዊ መንግስት በደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ስር በሚገኙ መንግስታዊ ትምህርት ቤቶች ነው ፡፡ የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ለጥናቱ የተመረጠው፡-

ሀ. ከሌሎች የአማራ ክልል አካባቢዎች የደብረ ብርሃን ከተማ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቅርበት ስላለው ከአማካሪዬ ጋር በየጊዜው ምክር ለመጠየቅ አመቺ በመሆኑ ፣

ለ. በከተማው አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ስር በሚገኙ አራት የመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በተደረገው ቅድመ ዳሰሳ ጥናት የትምህርት ቤቶቹ ተጠኚ መምህራን ፈቃደኛነት በማሳየታቸው ፣

ሐ. በከተማው አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ስር የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ለትራንስፖርት ፣ ለቪዲዮ ቀረፃ ወዘተ .... አመቺ በመሆናቸው ከጊዜ ፣ከገንዘብ፣ ከጉልበትና ከማቴሪያል አቅም አኳያ የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት አመቺ በመሆኑ በአላማ ተኮር ንሞና (Purposive sampling) ተመርጧል ፡፡

በከተማው አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ስር ሰባት መንግስታዊ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን ሶስቱ ማለትም (42.9%) በዕጣ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡት ትምህርት ቤቶችም አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፣ ብሩህ ተስፋ እና

አንድነት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው ። ጥናቱ በመንግስት ትምርት ቤቶች ላይ ያተኮረው በመምህራን የትምህርት ዝግጅት፣በተማሪ-ሴክሽን ጥምርታ ወዘተ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች ልዩነት በመኖሩ ነው።

### 3.1.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት በሚለው ለማየት እንደተሞከረው መምህራን የመናገር ክሂልን ለማቅረብ የሚከተሉት ዘዴ በተማሪዎች መካከል የርስበርስ መስተጋብር ለመፍጠር እንደማያስችል በዘጠነኛ ክፍል ላይ የተካሄደ ጥናት ጠቁሟል ።ስለዚህ የዚህ ዓይነቱን ችግር ለመፍታት የመምህራንን የመናገር ክሂል አቀራረብ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ውስጥ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መሸጋገሪያ የሆነውን ሁለተኛውን እርከን (5-8) ማየት ለትምህርቱ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል በሚል እምነት ነው ። ከሁለተኛው እርከን የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ሰባተኛ ክፍል የተመረጠውም በሁለት ምክንያት ነው።

ሀ. የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የሚያለማምዱ ተግባራት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በመጀመሪያው ወሰነ - ትምህርት በመቅረባቸው በምልከታ ወቅት መረጃ ለመሰብሰብ አመቺ በመሆኑ ፣

ለ. የዚሁ የክፍል ደረጃ መምህራን ለቪዲዮ ቀረፃ ፈቃደኛ በመሆናቸው ነው።

### 3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ የተካተቱት የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፣ ብሩህ ተስፋ እና አንድነት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ በእነዚሁ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ ሶስቱም (100%) የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል።

### 3.1.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ የተካተቱት ለጥናቱ በዕጣ በተመረጡት ሶስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። በሶስቱ ትምህርት ቤቶች ከሚማሩት 931 ተማሪዎች ውስጥ ሃያ አምስት በመቶ (25%) ማለትም 232 ተማሪዎች ዕጣ በማውጣት ዘዴ (lottery system) በጥናቱ ተካተዋል።

ሠንጠረዥ አንድ

በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች ፣ መምህራንና ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛትና የናሙና መጠን መግለጫ

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | መምህራን | | | | ተማሪዎች | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጠቅላላ ብዛት | | | የናሙና ብዛት | ጠቅላላ ብዛት | | | የመጠይቅ ናሙና ብዛት | | | |
| | | ወ | ሴ | ድ | ቃለ መጠይቅ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | % |
| 1 | አፄ ዘርዓያ ዕቆብ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት | 1 | - | 1 | 1 | 160 | 182 | 342 | 50 | 35 | 85 | 25 |
| 2 | ብሩህ ተስፋ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት | - | 1 | 1 | 1 | 166 | 222 | 388 | 48 | 49 | 97 | 25 |
| 3 | አንድነት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት | 1 | - | 1 | 1 | 95 | 106 | 201 | 22 | 28 | 50 | 25 |
| | ድምር | 2 | 1 | 3 | 3 | 421 | 510 | 931 | 120 | 112 | 232 | 25 |

ሶስቱም መምህራን ማለትም 100% በምልከታና በቃለ መጠይቅ ተሳትፈዋል።

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የአንድን ጥናት ውጤት አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ከፍ ለማድረግ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ የሚከተሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል።

### 3.2.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

በቋንቋ ትምህርት ተግባቦታዊ ክፍል ውስጥ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች የየራሳቸው የሆነ ሚና አላቸው። መምህሩ የመማር ማስተማር ሂደቱን ከመቆጣጠር ይልቅ በተማሪዎች መካከል በመንቀሳቀስ የመምራት ፣ የማነቃቃትና የማበረታታት ፣ የመጠየቅ ፣ ምጋቤ ምላሽ የመስጠት ተግባር ይጠበቅበታል። በአጭሩ ክፍለጊዜው በተማሪዎች ንግግር እንዲሸፈን ሁሉን ያማከለ ተሳትፎ እና ከፍተኛ ተነሳሽነት እንዲኖር ጥረት ማድረግ መምህሩን የግድ ይለዋል። ተማሪዎች ደግሞ ከመምህሩ በሚያገኙት የመነሻ ሀሳብ መሠረት የጥንድ ፣ የሶስትዮሽ ፣ የቡድን መስተጋብር በማድረግ በራስ የመተማመን ስሜት በመፍጠር ሀሳባቸውን በነፃነት የመግለፅ ተግባር ይጠበቅባቸዋል።

ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን የመናገር ክሂል ተግባራት ክንውኖችን መምህራን በሰባተኛ ክፍል ውስጥ እንዴት እያቀረቡት እንደሆነ ለማየት የክፍል ውስጥ ምልከታን በዋና የመረጃ መሰብሰቢያነት ጥናቱ ተጠቅሟል። መረጃዎችን ለመሰብሰብ የምልከታ መከታተያ ቅፅ በቅድሚያ ተዘጋጅቷል። የመከታተያ ቅፁ የተዘጋጀውም Mc Donough እና Shaw (1995:272-273) ፣ Scrivener (1994:202) ፣ Ur (1995:227) እና በምዕራፍ ሁለት የቀረቡትን ተዛማጅ ፅሁፎች መሠረት በማድረግ ነው ።

የምልከታ ቅጹ ሶስት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው የመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ ክንውንን የሚመለከት ሲሆን ፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ወቅሮችን የያዘ ነው። ሁሉም ክፍሎች በዝግ ጥያቄዎች (Closed - ended) ቀርበዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት Dornyei (2007:163) እንደሚሉት የተደራጀ ምልከታ (Structured observation) በክፍል ውስጥ በሚከናወኑ የተወሰኑ የትኩረት አቅጣጫዎችና ተጨባጭ በሆኑ የምልከታ ነጥቦች ላይ በማተኮር የሚከናወን በመሆኑ ሲሆን የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማሪያ ክፍልን ባገናዘበ መልኩ እንዲቀርብ ተደርጓል ።

የመጨረሻው ክፍል በመናገር ክሂል ተግባራት ወቅት የተከሰቱ ችግሮችን የሚዳስስ ሲሆን በልቅ ጥያቄዎች (open - ended) የቀረበ ነው ። ምክንያቱም ያልተደራጀ ምልከታ (unstructured observation) ለአጥኚው የተመለከተውን ጉዳይ እውነታውን ሳይለቅ የመተረክ ዕድል ስለሚሰጠው ነው Dornyei (2007 :163)። ስለሆነም አጥኚው በመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ ወቅት በመምህሩም ሆነ በተማሪዎች የተከሰቱ ችግሮችን በቅድሚያ ተመልክቶ ችግሮቹንና የችግሮቹን መንስኤዎች ከምልከታው በኋላ ሰፋ አድርጐ ለማቅረብ ስለሚረዳ ጥያቄዎቹ ልቅ እንዲሆኑ ተደርጓል።

የመከታተያ ቅጹን በተቻለ መጠን የተሟላ ለማድረግ ከመከታተያ ቅጹ ውጪ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ነጥቦች ሲያጋጥሙ መመዝገብ እንዲቻል "ሌላ" የሚል ክፍት ቦታ በመተው ማስታወሻ ለመያዝ ተሞክሯል።

የሚሰበሰበውን መረጃ አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ የመከታተያ ቅጹ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም የውጪ ቋንቋዎች የሶስተኛ ዓመት የ 'PhD' ተማሪ እና በደብረ ብርሃን መምህራንና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ በሚያስተምር መምህር (የ 'TEAM' ምሩቅ ) አስተያየት ተሰጥቶበት የዳበረ ሲሆን ለጥያቄዎቹ ግልፅነት ሲባል ጠቋሚ ነጥቦችን (Indicators) ከጥያቄዎቹ ግርጌ ለማስቀመጥ ጥረት ተደርጓል። ከዚያም በሶሬሳ አፀደ ህፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሞክሮ ማሻሻያ ተደርጓል። በሙከራው

ወቅትም የፅንሰ ሀሳብ ድግግሞሽ የታየባቸው ጥያቄዎች እንዲወገዱ ተደርጓል። ግልፅነት የሌላቸው ጥያቄዎች ደግሞ ማሻሻያ ተደርጉባቸዋል። በመጨረሻም በአማሪካው ታይቶ የተወሰነ ማስተካከያ ከተደረገ በኃላ ሥራ ላይ ውሏል።

በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረግ ምልከታ ተመልካቹ የተሳታፊነት (Participant - observer) እና የኢ-ተሳታፊ (non participant - observer) ሚና እንደሚኖረው Dornyei (2007:162) ይገልፃሉ። ከዚህ አኳያ ጥናቱ የኢ-ተሳታፊነት የምልከታ ስልት ተከትሏል።

Richards እና Nunan (1990:44) ዓይነታዊ ምርምር በባህሪው ሰፋ ያለ መረጃ የሚያስገኝ የምርምር ዓይነት ሲሆን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት ምልከታ የሚያደርገው አካል ስለሚመለከተው ጉዳይ ስልጠና ሊሰጠው እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። ስለዚህ የመምህራኑን የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አቀራረብ አጥኚው ብቻውን ከሚመለከተው ረዳቶችን ይዞ ቢመለከተው የመረጃውን የብቃት ደረጃ ከፍ ስለሚያደርገው ከኃይለማርያም ማሞ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤት ለሁለት መምህራን ስልጠና በመስጠት በሁለት ትምህርት ቤቶች ከአጥኚው ጋር በምልከታው እንዲሳተፉ ተደርጓል። በዚህም የአጥኚውን ነባራዊ ምልከታ የሚያዛቡ ነገሮችን ለመቀነስ ጥረት ተደርጓል።

በመጨረሻ በክፍል ውስጥ የታለፉ ክንዋኔዎችን ደጋግሞ በማየት መረጃውን የተሟላ ለማድረግ የቪዲዮ ቀረፃ የተደረገ ሲሆን ቀረፃው የተደረገው ከሶስቱ ተከታታይ ምልከታዎች ውስጥ የመጨረሻው ነው ። ከቪዲዮ ቀረፃው በኃላ መረጃው ወደፅሁፍ ሰነድነት ተለውጦ በአባሪነት የተያያዘ ሲሆን የተገኘውም መረጃ የክፍል ውስጥ ምልከታውን ውጤት እንዲያጠናክር ተደርጓል።

### 3.2.2 የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጋር ሲነፃፀር ጊዜን ፣ ጉልበትንና ገንዘብን ቆጣቢ በመሆኑ ፣ የመላሾቹን ማንነት ስለማይገልፅ መላሾች አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ በማበረታታትና ለሁሉም ተጠኝዎች አንድ አይነት ጥያቄ በማቅረቡ በምርምር መስኮች የበለጠ ጥቅም ላይ እንደሚውል ያለው (2001:148) ጠቅሰዋል። ስለሆነም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ከተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ የፅሁፍ መጠይቅ ሥራ ላይ ውሏል።

የፅሁፍ መጠይቁ የምልከታ መከታተያ ቅጹንና በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት የተካተቱትን ፅንሰ ሀሳቦች መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን መጠይቁ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያዎቹ አስር ጥያቄዎች በሊከርት ስኬል (Likert Scale) የቀረቡ ናቸው፡፡ Best (2006 ፡ 332) በሊከርት ስኬል አምስት አማራጭ መልሶችን በማቅረብ ፈንታ ሶስት አማራጮችን ማለትም "እስማማለሁ፣ መወሰን ያቅተኛል፣ አልስማማም " የሚሉትን አማራጮች በመጠን አመልካችነት መጠቀም እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ ከተማሪዎቹ ዕድሜ እና የትምህርት ደረጃ አኳያ ግርታን ላለመፍጠር ሲባል ሦስቱ አማራጮች ብቻ ስራ ላይ ውለዋል፡፡ በሁለተኛው ክፍል በቀረቡት ሶስት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ በምርጫ መልክ የቀረበ ነጠላ ጥያቄ ሲሆን ሁለቱ ተያያዥ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

የፅሁፍ መጠይቁ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በሶሬሳ አፀደ ህፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ ተሞክሯል፡፡ በሙከራውም በጥያቄ ሦስት እና አስራ ሁለት ላይ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

### 3.2.3 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ በአንድ ጉዳይ ዙሪያ ጥልቅ የሆነ መረጃ የሚያስገኝ ቢሆንም ከመላሾች የሚገኘውን መልስ ማደራጀት ፣ ማቀናጀትና መተንተን በጣም አስቸጋሪ ስለሚሆን ይህንን ችግር ለማቃለል ውስን ቁጥር ያላቸውን መላሾች ለመውሰድ እንደሚያስገድድ ያለው (2001፡177) ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ በሶስቱ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሶስት ብቻ በመሆናቸው ቃለ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት ተመርጧል፡፡

የቃለ መጠይቁ ዓላማ በምልከታ የተገኘውን መረጃ ማመሳከር ነው፡፡ ስለሆነም የክፍል ደረጃው መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራትንና የማስተማሪያ ዘዴዎችን እየተገለገሉ መሆን አለመሆኑን ለማየት ፣ ስለመናገር ክሂል አቀራረብ ያላቸውን ግንዛቤ ለመፈተሽ እንዲሁም የመናገር ክሂል ተግባሩን ሲያከናውኑ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መለየት በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ ጥያቄዎቹ በተቻለ መጠን ከምልከታ መከታተያ ቅጹ እና ለተማሪዎች ከተዘጋጀው የፅሁፍ መጠይቅ ጋር ተጣጥመው የተዘጋጁ ሲሆን ቃለ መጠይቁ አስር ጥያቄዎችን ያካተተ ነው ፡፡

## 3.3 የመረጃ አተናተን ሂደት

Dornyei (2007 ፡158) የክፍል ውስጥ ምልከታን የጥናት ውጤት አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ ምልከታው በቃለ መጠይቅ ፣ በፅሁፍ መጠይቅ ወዘተ ....መደገፍ እንዳለበት ይገልፃሉ፡፡ስለዚህ በጥናቱ ይኸው ሀሳብ ተግባራዊ የሆነ ሲሆን መረጃዎችን ለመተንተንም ዓይነታዊና መጠናዊ የመረጃ አተናተን ስልቶች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ስለሆነም በመጀመሪያ የክፍል ውስጥ ምልከታው ከቪዲዮ ቀረፃው ምዝግብ ጋር በመመሳከር በአሀዛዊና በገለፃዊ የአቀራረብ ስልት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ቀጥሎም ከተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በመልሶቹ ላይ የማጣራት ፣ ኮድ የማድረግ ሂደት ከተከናወነ በኋላ መረጃዎቹ በመቶኛ ተስልተው የአሀዞቹ አንድምታ በገለፃ መልክ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ ከዚያም በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በመልክ በመልክ ከተደራጁ በኋላ በዓይነታዊ የመረጃ ትንተና ስልት ማለትም በገለፃ ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት
# የጥናቱ የመረጃ ትንተና ውጤት

የዚህ ምዕራፍ አላማ ከሶስቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተገኙ መረጃዎችን ተንትኖ ውጤቱን መግለጽ ነው።የምርምር ስትራጂዎችን ማቀናጀትና ቁጥራቸውን ከፍ ማድረግ የሚጠናውን ችግር የማኘት እድማስ ለማስፋትና የአጥኚውን ማጠቃለያ የመስጠት ችሎታ ለማበልፀግ እንደሚረዳ Dornyei (2007፡149) ገልጸዋል። ስለዚህ የጥናቱን ውጤት አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ ከሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች እርስ በርስ እየተመሳከሩ እንዲቀርቡ ተደርጓል።

## 4.1 የመናገር ክሂል አቀራረብ ክንውኖች የመረጃ ትንተና

ከምልከታ የሚገኙ መረጃዎች ዋና ጥቅም አጥኚው ሰዎች የአከናወኑትን ነገር ከሚነግሩት ይልቅ ራሱ በቀጥታ ማየት መቻሉ ነው። በዚህ ዓይነት መንገድ የሚገኙ መረጃዎች ከሁለተኛ ምንጭ ከሚገኙ መረጃዎች የበለጠ ተጨባጭ እንደሆኑ Dornyei (2007፡169) ጠቁመዋል። ከዚህ መሠረተ ሀሳብ በመነሳት የተደራጀ የምልከታ ቅፅ በቅድሚያ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ምልከታው ወቅት ተተኳሪ ነጥቦች መከናወን ወይም አለመከናወናቸውን መከታተል የተቻለ ሲሆን የእያንዳንዱ የመናገር ክሂል የአቀራረብ ደረጃ ክንውን ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅና ከመምህራን ቃለ - መጠይቅ ጋር እየተመሳከረ የመረጃው ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 4.1.1 የአቀራረብ ደረጃ ክንውኖች የመረጃ ትንተና

በዚህ ጥናት የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት በሚለው ምዕራፍ እንደታየው የመናገር ክሂል ተግባራትን ለማቅረብ መምህራን የሚከተሏቸው የተለያዩ ደረጃዎች እንዳሉ ቀደም ሲል ተገልጾአል። ከአቀራረብ ደረጃዎቹ ውስጥ አንዱ የቅድመ - መናገር ተግባር ክንውን ነው። በዚህ የአቀራረብ ደረጃ መምህሩ የዕለቱን የመናገር ክሂል ትምህርት ከማቅረቡ በፊት የተማሪዎችን ፍላጐት ለማነሳሳት ከርዕሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የተለያዩ ዘዴዎችን (ለምሣሌ ስዕሎችን ፣ የጋዜጦችን ርዕስ - አንቀፅ ወዘተ) በመጠቀም የዕለቱን ትምህርት አላማና ምን ምን ተግባራትን እንደሚሠሩ ማስተዋወቅ ፣ ስለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅ መመሪያ መስጠትና መመሪያውን መረዳታቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ለሚያከናውኑት ተግባር ተገቢነት ያለው አቀማመጥና አደረጃጀት መምረጥ ይጠበቅበታል።

ስለዚህ መምህራን እነዚህን ተግባራት እንዴት እንደአከናወኗቸው ማየት ይቻል ዘንድ በቅድሚያ ከክፍል ውስጥ ምልከታና ከቪዲዮ ቀረፃ የተገኙ መረጃዎች፣ ቀጥሎም ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ ሁለት ፡- የመምህራንን የአቀራረብ ደረጃ ክንውኖች የሚያሣይ ሠንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የመናገር ክሂል አቀራረብ ክንውኖች | ት/ቤት $_1$ ም1፣2 | | ት/ቤት $_2$ ም1፣2 | | ት/ቤት $_3$ ም1፣2 | | ድምር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አዎ | | የለም | |
| | | አዎ | የለም | አዎ | የለም | አዎ | የለም | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1.1.1 | መምህሩ/ሯ የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ማለማመድ የሚያስችል አቀማመጥ (የፈረስ ኮቴ ፣ ክብ ወዘተ.. ) ተጠቅሟል/ማለች? | - | 2 | 1 | 1 | - | 2 | 1 | 16.67 | 5 | 83.33 |
| 1.1.2 | መምህሩ/ሯ የዕለቱን የመናገር ክሂል ተግባራትን አላማ አስተዋውቋል/ቃለች? | 2 | - | 1 | 1 | 2 | - | 5 | 83.38 | 1 | 16.67 |
| 1.1.3 | መነቃቃትን ለመፍጠር መምህሩ/ሯ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል/ማለች? የቀደመ- ዕውቀታቸውን ከርዕሱ ጋር አያይዞ መጠየቅ ተማሪዎች ስለሚማሩት ጉዳይ እንዲገምቱ ማድረግ ወዘተ… | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3 | 50 | 3 | 50 |
| 1.1.4 | መምህሩ/ሯ ተማሪዎች ስለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅ መመሪያ ሰጥቷል/ታለች? | 2 | - | 1 | 1 | 1 | 1 | 4 | 66.67 | 2 | 33.33 |

**መግለጫ፡-**

- ት/ቤት $_1$ = አፄ ዘርዓ ያዕቆብ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ት/ቤት $_2$ = ብሩህ ተስፋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ት/ቤት $_3$ = አንድነት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ም = ምልከታ
- ፣ = እና
- ፆታ አመልካች ቃላትን መጠቀሙ የመምህራኑን ማንነት ሊገልፅ ይችላል በሚል እምነት ፆታ አይጠቅሴ አገላለፅ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደሚታየው አብዛኞዎቹ መምህራን (83.33%) የሚሆኑት ወንበሮቹ ተንቀሳቃሽ ባለመሆናቸው ተማሪዎች የመናገር ክሂል ተግባራትን እንዲለማመዱ የሚረዱ አቀማመጥ አልተጠቀሙም፡፡ በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው የፈረስ ኮቴ፣ የክብ፣

የገፅ ለገፅ ወዘተ አቀማመጥ አንዱ ተማሪ ሌላውን ማየት ስለሚችል ተማሪዎቹ በቡድኑ ውስጥ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ እንዲሳተፉ ይረዳቸዋል፡፡ ወንበሮቹ ተንቀሳቃሽ ባለመሆናቸው ምክንያት መምህሩ የዚህ አይነት አቀማመጥን አለመምረጣቸው የተማሪዎችን የርስበርስ መስተጋብር ገድቦታል፡፡ ይህ ሁኔታም በተማሪዎች የመናገር ክሂል ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር መምህራን ሌሎች አማራጮችን (ለምሳሌ ፊትና ኋላ የተቀመጡ ተማሪዎችን በማቧደን) በመናገር ክሂል አቀራረብ ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

ሌላው በመናገር ክሂል ተግባርት አቀራረብ ስር ለማየት የተሞከረው መምህራን የዕለቱን የመናገር ክሂል ትምህርት ከማቅረባቸው በፊት አላማውንና ተማሪዎቹ የሚያከናውኑትን ተግባር ያስተዋውቃሉ ወይ? የሚል ሲሆን ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ሁሉም መምህራን ባይተገብሩትም አብዛኛዎቹ (83፡33%) ይዘውት የቀረቡትን የትምህርት ርዕስና አላማ ያስተዋውቃሉ፡፡ የቪዲዮ ቀረፃዉ ውጤትም ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

እንደቋንቋ ምሁራን እምነት ከሆነ መምህራን ወደእለቱ ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የተማሪዎችን ስሜት ማነሳሳትና ለትምህርቱ ዝግጁ እዲሆኑ ማድረግ ይገባል፡፡ ስለሆነም መምህራን ተማሪዎች ስለሚማሩት ርዕሰ ጉዳይ እንዲገምቱ የአእምሮ ማማሞቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ ፣ የተማሪዎችን የቀደመ - ዕውቀት ከእርሱ ጋር ማያያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ከፊሎቹ መምህራን (50%) የሚሆኑት ተግባሩን አከናውነውታል፡፡ የምልከታውን ውጤት አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ የቪዲዮ ቀረጻ የተከናወነ ሲሆን የቀረጻው ውጤት እንደሚያመለክተውም ከአንድ መምህር ውጪ የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት ለማነሳሳት የሞከረ አልነበረም፡፡ በአጭሩ መምህራን ያለፈውን ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦች ከመጠየቅ ወይም ባለፈው ክፍለ ጊዜ ይህንን ተምረናል ፤ በዛሬው ዕለት ደግሞ ....... እንማራለን በማለት ወደ እለቱ ትምህርት ከመግባት ውጪ ከእለቱ ትምህርት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ስዕላዊ መግለጫዎች ፣ የተለያዩ መጣጥፎችን፣ ርዕሰ - አንቀጾችን ፣ ቁም ነገር አዘል ቀልዶችን ወዘተ ከእለቱ ትምህርት ጋር አያይዞ በማቅረብ የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት ለማነሳሳት የሚያደርጉት ሙከራ አመርቂ ነው ማለት አያስደፍርም፡፡

ተማሪዎች ስለሚያከናወኑት ተግባር ከመነሻው ግልፅ የሆነ ግንዛቤ ካላቸው ተግባራቱን በሚያከናወኑበት ጊዜ ግራ አይገቡም፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታዩ 66.67% የሚሆኑት መምህራን ተማሪዎች ስለሚያከናውነት ተግባር መመሪያ ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ ርዕሱ ክርክር ከሆነ ተከራካሪዎች ፣ ዳኞች ፣ ክርክሩን የሚከታተሉት ተማሪዎች ምን ማድረግ

እንዳለባቸው መምህራን መመሪያ ሲሰጡ ታይቷል። የመመሪያ አሰጣጡ ግን በአንዳንድ መምህራን ተከታታይነት የለውም ። አንዳንድ ጊዜ ይሰጣሉ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ ይተውታል። የቪዲዮ ቀረፃ በተከናወነበት ወቅትም ከአንድ መምህር በስተቀር ስለክርክሩ / ስለውይይቱ ማን ምን እንደሚሠራ መመሪያ የሰጠ አልነበረም።

የመምህራንን የአቀራረብ ክንውኖች ለመፈተሽ ከክፍል ውስጥ ምልከታ በተጨማሪ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ስራ ላይ የዋለው የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ነው ። ወደ መረጃ ትንተና ከመግባታችን በፊት የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ / Profile / ምን እንደሚመስል ቀጥሎ ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ ሶስት ፦ የፅሁፍ መጠይቅ የሞሉና ያልሞሉ ተማሪዎችን የሚያሳይ መግለጫ**

| ዕድሜ | የፅሁፍ መጠይቅ የመለሱ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ | | | | | | | | | | የፅሁፍ መጠይቅ ያልመለሱ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማርኛ | | | | ትግረኛ | | | | ጠቅላላ | | | | | | | |
| | ወ | % | ሴ | % | ወ | % | ሴ | % | ድ | % | ወ | % | ሴ | % | ድ | % |
| ከ12-13 | 66 | 29.31 | 67 | 28.88 | - | - | - | - | 135 | 58.19 | 4 | 1.7 | 2 | 0.86 | 6 | 2.6 |
| ከ14-15 | 33 | 14.22 | 27 | 11.64 | - | - | 1 | 0.43 | 61 | 26.29 | 2 | 0.68 | 2 | 0.86 | 4 | 1.7 |
| ከ16-17 | 6 | 2.59 | 12 | 5.17 | - | - | - | - | 18 | 7.76 | 1 | 0.4 | - | - | 1 | 0.4 |
| 17 ሰላይ | 4 | 1.72 | 2 | 0.68 | - | - | - | - | 6 | 2.58 | 1 | 0.4 | - | - | 1 | 0.4 |
| ድምር | 111 | 47.84 | 108 | 46.55 | - | - | 1 | 0.43 | 220 | 94.82 | 8 | 3.4 | 4 | 1.7 | 12 | 5.1 |

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደሚታየው የፅሁፍ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ ከአንድ ተማሪ ውጪ ሁሉም የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ነው ። መጠይቁን እንዲሞሉ ከተደረጉት 232 ተማሪዎች ውስጥ 12ቱ (5.1%) ተማሪዎች መጠይቁን በትክክል ስላልሞሉ መልሳቸው እንዲወገድ ተደርጓል። ስለዚህ የፅሁፍ መጠይቁን በትክክል የሞሉት 220 (94.82%) ያህሉ ተማሪዎች ብቻ ናቸው። ከፆታ አኳያ ሲታይ ደግሞ 47.84% ወንዶች ሲሆኑ፣46.98 ያህሉ ሴቶች ናቸው። ስለዚህ በጥናቱ የሁለቱም ፆታዎች ተሳትፎ በጉልህ ታይቷል።

ሰንጠረዥ አራት፡- የቅድመ መናገር ተግባራት አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መልሶች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | መወሰን ያቅተኛል | | አልስማማም | | ጠቅላላ ድምር | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1 | መምህሩ/ሯ የመናገር ክሂል ተግባራት በክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት በተለያዩ መንገዶች ያነቃቃሉ? | 110 | 50 | 44 | 20 | 66 | 30 | 220 | 100 |
| 2 | የመናገር ክሂል ተግባራትን ከማከናወናችን በፊት መምህሩ/ሯ አጭርና ግልፅ መመሪያ ይሰጣሉ? | 156 | 70.9 | 33 | 15 | 31 | 14.1 | 220 | 100 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚታየው መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ ግማሽ (50%) ያህሉ መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን ከማቅረባቸው በፊት በተለያዩ መንገዶች ተማሪዎችን እንደሚያነቃቁ ያምናሉ፡፡ መጠይቁን ከሞሉት 30% የሚሆኑት ግን በሀሳቡ አይስማሙም፡፡ ቀሪዎቹ (20%) ደግሞ ምንም ሀሳብ እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ ከተማሪዎቹ መልስ መረዳት የሚቻለው የዕለቱ ትምህርት ከመቅረቡ በፊት መምህራን ተከታታይነት ባለው መንገድ የተማሪዎቻቸውን የቅደመ - ዕውቀት ከዕለቱ ትምህርት ጋር ለማዛመድ ፣ የዕለቱ ትምህርት በምን ዙሪያ እንደሚያጠነጥን ፍንጭ ለመስጠት ፣ የተማሪዎችን ትኩረት ወደ ትምህርቱ ለመሳብ የሚያደርጉት ጥረት መካከለኛ ነው፡፡

ሌላው የመምህራን የቅድመ - መናገር ተግባር ክንውን በሚመለከት ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ የመምህራን የመመሪያ አሰጣጥ የሚመለከት ነው ፡፡ ለዚህ ጥያቄ 70.9% ያህሉ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ ቀሪዎቹ ግን ጉዳዩን በጥርጣሬ መልክ የሚያዩና አሉታዊ መልስ ያላቸው ናቸው፡፡ Ur (1981፡18) የመምህራንን ወደዕለቱ ትምህርት ከመግባታቸው በፊት መመሪያ የመስጠት ጠቀሜታ በሚመለከት "ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅና አጥር ምጥን ያለ (clear and concise) መመሪያ መስጠት የተማሪዎች ግራ የመጋባት ችግር ተቀርፎ ክንውኑ በተሳካ ሁኔታ እንዲሄድ ይረዳል" ይላሉ፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ የመምህራኑ ግንዛቤና አፈፃፀም በተማሪዎች እይታ በጣም የተሻለ ደረጃ ላይ ነው፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታው መረጃ ውጤትም ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

## ሠንጠረዥ አምስት ፡- በጥናቱ የተካተቱ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መግለጫ

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | የመምህራን ብዛት | ጾታ | በሳምንት የክፍለ ጊዜ ጫና | የትምህርት ደረጃ | የትምህርት ስልጠና መስክ | | የአገልግሎት ዘመን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | አብይ | ንኡስ | በሰርተፊኬት | በዲፕሎማ | ድምር |
| 1 | አፄ ዘርዓ ያዕቆብ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 1 | ወ | 24 | 12 +2 | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 8 | 31 | 39 |
| 2 | ብሩህ ተስፋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 1 | ሴ | 24 | 10 +3 | አማርኛ | የለም | 24 | 2 | 26 |
| 3 | አንድነት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 1 | ወ | 24 | 12 +2 | አማርኛ | እንግሊዝኛ | - | 10 | 10 |

ሁሉም መምህራን በሚያስተምሩት የትምህርት መስክ የሰለጠኑ ናቸው። ስለሆነም መምህራኑ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ለደረጃው ያወጣውን ስታንዳርድ ያሟሉ ናቸው። መምህራኑ በሳምንት 24 ክፍለጊዜ ክፍል ውስጥ ገብተው የሚያስተምሩ ሲሆን በሰዓት ሲሰላ 16 ሰዓት ነው። አብክመ ትምህርት ቢሮ(2002) "የአንድ መምህር የሳምንት መደበኛ የስራ ሰዓት/40/ አርባ ሰዓት ይሆናል። በዚህ መሰረት በክፍል ውስጥ ገብቶ በመማር ማስተማር ሥራ ላይ 22 $\frac{1}{2}$ /ሀያ ሁለት ሰዓት ተኩል/ ያሳልፋል" ብሎ ካወጣው መመሪያ አኳያ ሲታይ የመምህራኑ የክፍለ ጊዜ ጫና የከፋ አይደለም።

የመምህራኑ ዳራዊ መግለጫ ከላይ የቀረበውን ሲመስል የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት መምህራን ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ ቀርቧል።

የመምህራንን የቅድመ - መናገር ተግባራት ክንውኖችን በሚመለከት ከምልከታና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ በተጨማሪ የራሳቸው የመምህራን ግንዛቤ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን ለቃል- መጠይቅ ለቀረቡት ሶስት መምህራን " አንድ የቋንቋ መምህር የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርብ /በአቀራረብ፣ በልምምድ ፣ በአፍልቆት ደረጃ/ ሚናው /ተግባሩ/ ምንድነው ይላሉ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሁለት መምህራን የአቀራረብ ደረጃ ተግባራትን በሚመለከት የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

- ርዕሱን ማስተዋወቅ
- ክፍሉን ምቹ ማድረግ
- የሚያውቁትንና የሚስባቸውን ርዕስ ማቅረብ
- ስለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅ መመሪያ መስጠት

አንድ መምህር ደግሞ ፡-

- ተማሪዎች በምክንያት የታገዘ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ማስለጠንና ሀሳቡን መግለፅ የሚችል ዜጋ ማፍራት የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

መምህራኑ ከሰጡት መልስ ሁለቱ መምህራን በቅድመ - መናገር ተግባራት ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንዳለባቸው ከሞላ ጎደል ግንዛቤው እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ የአንዱ መምህር ምላሽ ግን የመናገር ክሂል ትምህርትን ግብ ያሳይ እንደሆነ እንጂ አንድ መምህር ትምህርቱን ከማቅረቡ በፊት ተማሪዎችን ወደ ዕለቱ ትምህርት ለማስገባት የሚያደርገውን ዝርዝር ክንውንም ሆነ የልምምድ ደረጃ ወዘተ የሚያመለክት አንዳችም ነገር የለበትም፡፡

በአጠቃላይ የመምህራን የቅድመ - መናገር ተግባራት ክንውን ሲታይ የክፍል ውስጥ ምልከታውን ክፍተት ለመሙላት የተደረገው ተጨማሪ የቪዲዮ ቀረፃ እንደሚያመለክተው መምህራን ከተለመደው ረድፋዊ አቀማመጥ ውጪ የተማሪዎችን የርስበርስ መስተጋብር የሚያበረታታ አቀማመጥ (ለምሳሌ የፈረስ ኮቴ ፣ ክብ ወዘተ) በክፍል ውስጥ ሲጠቀሙ አልታየም፡፡ የዕለቱን ትምህርት ርዕስና አላማ ማስተዋወቅን በሚመለከት ግን መምህራኑ ከሞላ ጎደል ግንዛቤው እንዳላቸው በሶስቱም መሣሪያዎች የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ሌላው በቅድመ መናገር ተግባራት ክንውን ስር የተነሳው ጉዳይ የዕለቱ ትምህርት ከመቅረቡ በፊት የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በተለያዩ መንገዶች ማነሳሳት ነው፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚመለከት ከክፍል ውስጥ ምልከታውና ከቪዲዮ ቀረፃው ፣ ከተማሪዎች መጠይቅ እንዲሁም ከራሳቸው ከመምህራን ቃለ - መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንዳመለከቱት ከሆነ የመምህራኑ ግንዛቤ በሚፈለገው ደረጃ ላይ አልደረሰም ማለት ይቻላል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ስለሚያከናውኑት ተግባር የመምህራንን አጭርና ግልፅ መመሪያ አሰጣጥን በሚመለከት ከሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተገኙት መረጃዎች የመምህራኑ ግንዛቤና አፈፃፀም የተሻለ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

### 4.1.2 የልምምድ ደረጃ ክንውኖች የመረጃ ትንተና

በዚህ የአቀራራረብ ደረጃ መምህሩ ተማሪዎችን በጥንድ /በቡድን ማደራጀት ፣ የተማሪዎቹን የመናገር ችሎታ የሚያበረታቱ መለማመጃዎች ማዘጋጀትና ማቅረብ ፣ የተማሪዎቹን የመማር ርምጃ መከታተል ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መርዳትና ማበረታታት የሚጠበቅበት ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን ጠቃሚ የሆነ የንግግር ልምምድ የሚያደርጉበት እንደሆነ በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ታይቷል። ስለዚህ በምልከታው ጊዜ የልምምዱ ክንውን አፈፃፀም በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ማየት ይቻል ዘንድ መረጃውና ትንታኔው ቀጥሎ ቀርቧል።

**ሠንጠረዥ ስድስት ፡- የመምህራንን የልምምድ ደረጃ ክንውኖች የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የመናገር ክሂል አቀራረብ ክንውኖች | ት/ቤት 1 ምⅠⅠ2 | | ት/ቤት 2 ምⅠⅠ2 | | ት/ቤት 3 ምⅠⅠ2 | | ድምር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አዎ | | የለም | |
| | | አዎ | የለም | አዎ | የለም | አዎ | የለም | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1.2.1 | መምህሩ/ሯ የመናገር ክሂልን መለማመድ የሚያስችል ተግባራትን (ሪፖርት፣ ክርክር፣ ውይይት ፣ ጭውውት) ተጠቅሟል/ማለች? | 1 | 1 | 2 | - | 1 | 1 | 4 | 66.67 | 2 | 33.33 |
| 1.2.2 | ተማሪዎች የመናገር ክሂል ተግባራትን በመምህሩ/ሯ አመቻችነትና መሪነት በጥንድ /በቡድን/ ክፍሉ በአንድነት በመሆን ተለማምደዋል? | - | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 33.33 | 4 | 66.67 |
| 1.2.3 | መምህሩ/ሯ ሁሉም ተማሪዎች በልምምዱ እንዲሳተፉ ያደርጋል/ ታደርጋለች? | - | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 33.3 | 4 | 66.67 |
| 1.2.4 | መምህሩ/ሯ ተማሪዎች እንዲናገሩ ለማድረግ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል/ማለች?<br>• በርዕሱ ዙሪያ ተጨማሪ መረጃ መስጠት፣<br>• ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲረዳዱ ማድረግ ወዘተ..... | - | 2 | 1 | 1 | - | 2 | 1 | 16.67 | 5 | 83.33 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚታየው 66.67% የሚሆኑት መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ማለማመድ የሚችሉ ለምሳሌ ክርክር ፣ ጭውውት ፣ ውይይት ማቅረብ እንዲሁም የነገሮችን አሠራር ቅደም ተከተል በቡድን ተወያይቶ ሪፖርት ማድረግ የመሳሰሉት ተግባራትን ተጠቅመዋል፡፡ በእነዛሩ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ከቀረቡት የመከራከሪያ ርዕሶች ውስጥ መርጠው እንዲከራከሩ፣ በቡድን የሰሩትን ሪፖርት እንዲያደርጉ መልመጃው እያዘዘ የሁለት ትምህርት ቤት መምህራን ግን ልጆቹ ክርክር፣ ሪፖርት ሳያቀርቡ የክርክር ፅንሰ ሀሳቦችን በማብራራት እና በመምህር - ተማሪ ጥያቄና መልስ ብቻ ክፍለ ጊዜውን በሙሉ የጨረሱ ነበሩ፡፡ በአጠቃላይ አተገባበሩ ትውውቅ - ልምምድ - አፍልቆት (ክርክር፣ ጭውውት ወዘተ .. ማቅረብ) ሂደትን የተከተለ ባይሆንም አብዛኛዎቹ መምህራን የመናገር ክሂልን ማለማመድ የሚያስችሉ ተግባራት ተጠቅማዋል ማለት ይቻላል፡፡

" ተማሪዎች የመናገር ክሂል ተግባራትን በመምህራን አመቻችነት በጥንድ ፣ በቡድን ክፍሉ በአንድነት በመሆን ወዘተ ተለማምደዋል ወይ?" ለሚለው 33.33% የሚሆኑት መምህራን ተማሪዎች በጥንድና በቡድን ተግባራቱን በክፍል ውስጥ እንዲለማመዱ ሁኔታዎችን ሲያመቻቹና ሲያግዙ ታይተዋል፡፡ ለአስረጅነትም ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ በመሆን አባት/ እናትና ልጅ በመሆን ጭውውት ማድረግ ፣ የነገሮችን አሠራር ቅደም ተከተል (የሻማ ፣ የሰፌ ፣ የሸክላ ስራ ውጤቶች ወዘተ አሠራር) ጠይቆ በቃል ሪፖርት ማቅረብ ክንውኖች ይጠቀሳሉ፡፡ Byrne (1976፡2) እንደሚሉት ከሆነ የልምምድ ደረጃ የመምህሩ ተሳትፎ በእጅጉ የሚቀንስበት ተማሪዎች ግን አብዛኛውን የመናገር ዕድል የሚያገኙበት ነው፡፡ ከዚህ አባባል በልምምድ ደረጃ ተማሪዎች የቀረቡትን ተግባራት መለማመድ የሚያስችል በቂ ጊዜ ማግኘት እንዳለባቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ከሰንጠረዡ እንደሚታየው 66.67 የሚሆኑት መምህራን ተማሪዎች በጥንድ/ በቡድን ሳይለማመዱ ወደ አፍልቆት (ክርክር ማቅረብ) ደረጃ ሲገቡ ተስተውሏል፡፡

ተማሪዎች በጥንድ/በቡድን ልምምድ ሳያደርጉ ወደ አፍልቆት ደረጃ መተላለፍ የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም የልምምድ ደረጃ አላማ የክፍሉ ተማሪዎች በጥንድ /በቡድን በመሆን በቀረቡት ተግባራት ላይ እንዲለማመዱ የንግግር ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም አብዛኛውን ተማሪ አሳታፊ የሆነው የልምምድ ደረጃ ሳይከናወን ከተመደበው ጊዜ አናሳነት አኳያ የተወሰኑ ተማሪዎችን ብቻ ወደሚያሳትፈው የአፍልቆት ደረጃ ዘሎ መግባት ተገቢነት አይኖረውም፡፡ ስለዚህ ክፍለ ጊዜውን ለትውውቅ ፣ ለልምምድ ፣ ለአፍልቆት (ክርክር ፣ ጭውውት ማቅረብ ወዘተ) ብሎ ከፋፍሎ ለተወሰኑ ደቂቃዎች

በክርክሩ ወይም በጭውውቱ ርዕስ ዙሪያ ተማሪዎች ከተነጋገሩ በኋላ በቡድኑ የተመረጡ ወይም ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎች ክርክሩንም ሆነ ጭውውቱን ቢያቀርቡ፣ እንደኛ ለጭውውቱና ለክርክሩ ያልተመረጡ ተማሪዎች በልምምዱ ጊዜ የመናገር ዕድል ያገኛሉ። ሁለተኛም ተከራካሪዎች በሚያቀርቡት ጉዳይ ዙሪያ ከቡድኑ ሀሳብ ያገኛሉ። ስለዚህ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የልምምድ ደረጃን ሳይተገብሩ ወደ አፍልቆት ደረጃ ማለፍ አቀራረቡ የአበዛኛዎቹን ተማሪዎች የመናገር ችሎታ የማዳበር አቅሙ አናሳ ስለሚሆን የልምምድ ደረጃን መተግበር ግድ ይላል።

በልምምድ ደረጃ ሌላው የተነሳው ነጥብ "መምህራን በልምምዱ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያደርጋሉ? " የሚል ሲሆን አብዛኛዎቹ መምህራን (66.67%) በልምምዱ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ አላደረጉም። ምክንያቱም መምህራኑ የልምምድ ደረጃ ተግባራትን ሳያከናውኑ በቀጥታ ወደክርክሩ በመግባታቸው ነው ።

በመጨረሻም "ተማሪዎች በልምምዱ ወቅት እንዲሳተፉ መምህራን የተለያዩ የማነቃቂያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል ወይ? " የሚለውም ከልምምድ መከናወን ጋር የተያያዘ ስለሆነ አልተተገበረም። ልምምዱን ሙከራ ካደረጉት መምህራን (33.33%) ውስጥም ቢሆን ተማሪዎች የልምምድ ደረጃ ተግባራትን ሲያከናውኑ እየተዘዋወሩ የመረጃ እጥረትና ስነልቦናዊ ችግር (ፍርሃት) ያለባቸውን ተማሪዎች የማበረታታት እንዲሁም ተማሪዎቹ ርስበርስ እንዲረዳዱ የማገዝ ባህሉ የላቸውም ማለት ይቻላል። ከሰሌዳው አካባቢ ከመቆም ውጪ ወደ ተማሪዎቹ ቀረብ ብለው ክትትል እና ድጋፍ ሲያደርጉ አልታዩም።

የክፍል ውስጥ ምልከታውን ለማጠናከር የቪዲዮ ቀረፃ የተደረገ ሲሆን የቪዲዮ ቀረፃው ውጤትም ከላይ የቀረበውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው ። በቪዲዮ ቀረፃው ወቅት በሁለት ትምህርት ቤቶች ክርክር ፣ በአንዱ ደግሞ ውይይት የቀረበ ሲሆን ክርክሩ ወይም ውይይቱ ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎች በጥንድ ፣ በሶስትዮሽ ፣ በትንንሽ ቡድኖች ሆነው ለክርክር ወይም ለውይይት በቀረበው ርዕስ ዙሪያ ልምምድ አድርገው ለክርክሩ ወይም ለውይይቱ ግብአት የሚሆን ሀሳብ ሲያመነጩ አልታየም። አንድ መምህር ብቻ የክፍሉ ተማሪዎች የክርክሩን መድረክ እስከሚያመቻቹ ድረስ ተከራካሪዎች በየቡድናቸው ለተወሰነ ደቂቃ ርስበርስ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ሲያደርጉ ታይቷል። ሌሎች ግን ተከራካሪዎችን ቀደም አድርገው መርጠው ለቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ተዘጋጅተው እንዲመጡ በማድረግ የክርክሩን ሂደት እንደሚያከናውኑት ለመረዳት ተችሏል። ልምምዱን የተወሰኑ ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ከሚያከናውኑት ይልቅ ሁሉንም የመናገር ክሂል አቀራረብ ደረጃዎች (የማቅረብ - የልምምድ

- የአፍልቆት) በክፍል ውስጥ ማከናወን የሁሉንም ተማሪዎች ተሳትፎ በማረጋገጥ የመናገር ክሂላቸው ለማሳደግ ስለሚረዳ የተሻለ ይሆናል።

በአጭሩ ለክርክር የተመረጡ ተማሪዎች ብቻ ከክፍል ውጪ ለክርክሩ መረጃ አሰባስበው፣ ልምምድ አድረርገው፣ ክርክሩን እንዲያቀርቡት ማድረግ የአብዛኛዎቹን ተማሪዎች የመናገር ክሂል ለማሳደግ ብዙም ፋይዳ የለውም። ምክንያቱም ተሳትፎው ለመከራከር እድል ባገኙ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ ስለሚወሰን ነው። ከዚህ አቀራረብ ይልቅ Byrne (1976 : 22-99) ፣ Harmer (1991:51-50) እንዲሁም Scrivener (1994:29-30) እና Gower et al. (1995:102-103) እንደጠቀሱት ክፍለ ጊዜውን ለአቀራረብ - ለልምምድ - ለአፍልቆት - ለምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ብሎ ከፋፍሎ ማንኛውንም ዓይነት የመናገር ክሂል አቀራረብ ክፍል ውስጥ ቢካሄድ የክፍሉ ተማሪዎች ከሞላ ጎደል የሚለማመዱበት ዕድል ስለሚያገኙና ተሳትፎአቸውንም ማረጋገጥ ስለሚቻል የተሻለ ይሆናል።

የመምህራንን የልምምድ ደረጃ ክንውኖች በሚመለከት ከምልከታ በተጨማሪ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የፅሁፍ መጠይቅ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን ከተማሪዎች ምላሽ የተገኘው የመረጃ ትንተና ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ ሰባት :- የልምምድ ደረጃ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መ ል ሶ ች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | መወሰን ያቅተኛል | | አልስማማም | | ጠቅላላ ድምር | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3 | በግል፣በጥንድ፣ በሶስትዮሽ፣ በቡድን ውይይት ወዘተ የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ እለማመዳለሁ። | 125 | 56.8 | 36 | 16.4 | 59 | 26.8 | 220 | 100 |
| 4 | መምህሩ/ሯ/ በግል፣ በጥንድ፣ በሶስትዮሽ፣ በቡድን ወዘተ የመናገር ክሂል ተግባራትን ሲያሰሩ አፈፃፀማችንን እየተዘዋወሩ በመከታተል ያበረታታሉ። | 132 | 60 | 38 | 17.3 | 50 | 22.7 | 220 | 100 |

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ተማሪዎች የመናገር ክሂል በክፍል ውስጥ ሲቀርብ በግል፣ በጥንድ ፣ በቡድን ይለማመዱ ወይም አይለማመዱ እንደሆነና ልምምዱን ሲያከናውኑ መምህራን ክትትልና ድጋፍ ያደረጉ ወይም አያድረጉ እንደሆነ ለመፈተሽ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አወንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የእነዚህ

ተማሪዎች ግንዛቤ (ምላሽ) ከክፍል ውስጥ ምልከታውና ከቪዲዮ ቀረፃው ከተገኘው መረጃ ውጤት ጋር የሚጋጭ ነው ፡፡ ምናልባት አብዛኞዎቹ (በአማካይ 58% የሚሆኑት) ተማሪዎች " በግል ፣ በጥንድ ፣ በቡድን ወዘተ የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ አለማመዳለሁ" በሚለው ውስጥ " በክፍል ውስጥ" የሚለው ሀረግ የያዘውን ፅንስ - ሀሳብ በውል ሳይገነዘቡት ቀርተው ይሆናል፡፡ ማለትም ለቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ክርክር እንዲያቀርቡ ሲታዘዙ ከክፍል ውጪ የሚያደረጉትን ልምምድ እንደክፍል ውስጥ ልምምድ አይተውት ሊሆን ይችላል እንጂ ቀደም ሲል እንደተገለፀው በተለይ በቪዲዮ ቀረፃው ከአንድ መምህር በስተቀር ሌሎቹ መምህራን በክፍል ውስጥ ክርክር / ውይይት ሲቀርብ ተማሪዎቹ ልምምድ አድርገው ወደ አፍልቆት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ሲያደርጉም ሆነ በልምምዱ ወቅት ሲደግፉ አልታዩም፡፡

ከክፍል ውስጥ ምልከታና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ሌላ የመምህራንን የልምምድ ደረጃ ክንውኖች ለማየት ስራ ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የመምህራን ቃለ-መጠይቅ ሲሆን ከልምምድ ደረጃ ጋር ተያያዥነት ኖሯቸው ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎች ትንተና ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ለመምህራኑ ከቀረቡት ጥያቄዎች የመጀመሪያው በሰባተኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ የተካተቱ የመልመጃ ዓይነቶችንና መልመጃዎቹ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የሚያሳድጉ መሆን አለመሆናቸውን የሚመለከቱ ነበሩ፡፡ ሁሉም መምህራን መመሪያዎችን መከተል ፣ የክርክር ፣ የውይይትና የጭውውት ስርዓት በሚሉ ርዕሶች የተለያዩ የመናገር ክሂል መልመጃዎች ቀርበዋል ሲሉ መልሰዋል፡፡ መልመጃዎቹም ከዕድሜያቸውና ከትምህርት ደረጃቸው ያልራቁ በመሆናቸው ተማሪዎችን ለንግግር የመቀስቀስና የውድድር ስሜት የመፍጠር ሀይል ስላላቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ክርክር፣ ጭውውት፣ ውይይት ሲያቀርቡ ቃላትን የመምረጥና ሀሳብን አደራጅቶ የመናገር አቅማቸው እንዲያድግ ለማለማመድ ይረዳሉ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

በአጭሩ ከመምህራኑ እንደተገለፀው እና ስ.ት.ዝ.ጥ.ም ኢንስቲትዩት (1997፡118-121) እንደተጠቀሰው ለመናገር ክሂል ተግባራት የተሰጠው 7 ክፍል ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ተግባራቱን ለማከናወን ከተሰጠው ጊዜ ማነስና የመልመጃዎች ዓይነት ውስን ከመሆኑ በስተቀር የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የሚያሳድጉ ናቸው፤ የምልከታና የቪዲዮ ቀረፃው መረጃም ይህንኑ ሀሳብ የሚጠናክር ነው ፡፡

ለመምህራኑ የቀረበው ሁለተኛ ጥያቄ " በመናገር ክሂል አቀራረብ ምን ምን የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይገለገላሉ?" የሚል ሲሆን ሁለት መምህራን የቡድን ስራ (group work) በማስተማሪያ ዘዴ እንደሚገለገሉ የገለፁ ሲሆን ፣ አንድ መምህር ደግሞ በቡድን ስራ ደከም ያሉ ተማሪዎች በጉበዝ ተማሪዎች ስለሚሸፈኑ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች በግል እንዲሰሩ አደርጋለሁ። በጣም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግን አልፎ አልፎ የቡድን ስራ እጠቀማለሁ ብለዋል።

ስለዚህ የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ ለማቅረብ ከቡድን ስራ በተጨማሪ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎች መኖራቸውንና ዘዴዎቹ የተለያዩ የመናገር ክሂል ተግባራትን ለማቅረብ የራሳቸው የሆነ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን መምህራን ተገንዝበው ሊገለገሉባቸው ይገባል። ለምሳሌ ውይይት ክፍሉ በአንድነት በመሆን ፣ ታሪክ መናገርና የዱብ ዕዳ ንግግር (Impromptu speech) በግል የሚከናወኑ ሲሆኑ፣ እንደ ሚና ጨዋታ ፣ ቃለመጠይቅ መደራረግ ያሉት ደግሞ በጥንድ የሚቀርቡ ናቸው። ስለሆነም መምህራን በክፍል ውስጥ ለሚያቀርቡት የመናገር ክሂል ትምህርት አንድ ብቸኛ የማቅረቢያ መንገድ አለመኖሩን ተገንዝበው ለልምምድ ከመረጧቸው መልመጃዎች ጋር የሚጣጣም የማስተማሪያ ዘዴ መምረጥ ግድ ይላቸዋል።

በሶስተኛ ደረጃ ለመምህራን የቀረበላቸው ጥያቄ የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ቡድኖችን በምን መልክ እንደሚያደራጁ ነበር። አንድ መምህር በመቀመጫ ቡድን እንደሚያደራጁ ሲገልፁ ፣ ሁለት መምህራን ደግሞ ጎበዝና ደከም ያሉ ተማሪዎችን በማሰባጠር እንደሚያደራጁ ገልፀዋል።

በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት እንደተገለፀው እያንዳንዱ የቡድን አደረጃጀት የራሱ የሆነ ጥቅምና ጉዳት አለው። ለምሳሌ Sesnan (1997) "ጎበዝና ደከም ያሉ ተማሪዎችን በአንድ ላይ ማደራጀት ደከም ያሉት ከጎበዞች ጋር ሲሆኑ ያለባቸውን ችግሮች ሁሉ ተቋቁመው ከጓደኞቻቸው ለመማር የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ስለሚሆን ጠቃሚ ነው" ይላሉ። በሌላ በኩል Harmer (1991) "አንዳንድ ጊዜ የጎበዝና ደከም ያሉ ተማሪዎች ስብጥራዊ አደረጃጀት አስፈላጊ ቢሆንም እንደትምህርት አቀባበላቸው ተማሪዎችን ማደራጀት ተማሪዎቹ በራሳቸው ፍጥነት ስለሚማሩ ጠቃሚ ነው" ይላሉ። ከዚህ አኳያ መምህራን ተማሪዎቻቸው በየትኛው አደረጃጀት ቢሟደኑ የተሻለ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ክትትል በማድረግ አደረጃጀቱን ከተማሪዎቻቸው የመማር ዕድገት አኳያ መለዋወጥ እንዳለባቸው ልብ ሊሉት ይገባል።

በመጨረሻም መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ በልምምድ ደረጃ ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናወኑ ለቀረበላቸው ጥያቄ አንድ መምህር ብቻ "ተማሪዎች የሚያከናውኑትን ተግባር መከታተል" የሚል መልስ ሰጥቷል። ሌሎች መምህራን ግን ከልምምድ ደረጃ ተግባር ጋር የሚያያዝ መልስ አልሰጡም። ከዚህም ሁለቱ መምህራን፣አንድ መምህር በልምምድ ደረጃ ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንዳለበት ግንዛቤው እንደሌላቸው መረዳት የሚቻል ሲሆን ፣አንዱ ግን በፅንሰ - ሀሳብ ደረጃም ቢሆን ግንዛቤው አለው። ምክንያቱም የቪዲዮ ቀረፃው መረጃ እንደሚያመለክተው የተወሰኑ ተማሪዎች ውይይቱን በመቆጣጠር የሌሎች ተማሪዎች ተሳትፎ ውስን እንዲሆን ሲያደርጉት በመምህሩ የተወሰደ የማስተካከያ ርምጃ አልነበረም። ስለዚህ ግንዛቤው በውስጡ ስርጾአል ማለት አይቻልም።

ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ለማጠቃለል በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ተግባራት ተማሪዎች ስለአንድ ነገር አሠራር ተወያይተው ሪፖርት እንዲያቀርቡ ፣ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ በስልፍ ቦታ ክርክር እንዲያደርጉ ፣ በመጽሐፉ ላይ የቀረበውን ጭውውት አጥንተው በቃል እንዲያቀርቡ ወይም የራሳቸውን ጭውውት ፈጥረው እንዲጫወቱ፣ በመረጧቸው ርዕሶች እንዲወያዩ የሚያደርጉ (አብክመ ትምህርት ቢሮ ፣ 1997 ፣ 17-25) በመሆናቸው መልመጃዎቹ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የሚያስችሉ ናቸው። የምልከታውና የቪዲዮ ቀረፃው ውጤት እንደሚያሳየውም አብዛኛዎቹ መምህራን (66.67%) ከሞላ ጎደል መልመጃዎቹን ተገልግለውባቸዋል። የመምህራኑም የቃለ መጠይቅ ምላሽ ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር ነው። እነዚህን የመናገር ክሂል ተግባራት ለማከናወን የግል፣ የቡድን ውይይት ዘዴ እንደሚገለገሉ መምህራን የገለፁ ሲሆን አፈፃፀሙ ችግር ቢታይበትም የምልከታና የቪዲዮ ቀረፃው መረጃ ተማሪዎች በቡድን ፣ ክፍሉ በአድነት በመሆን ክርክር ፣ ውይይት እንደሚያቀርቡ አመልክቷል።

ተማሪዎች ወደ አፍልቆት ደረጃ ከመሸጋገራቸው በፊት በክፍል ውስጥ በግል ፣ በጥንድ ፣ በቡድን በቂ ልምምድ ማድረግንና በክንውኑ የመምህራንን ክትትልና ድጋፍ አሰጣጥን በሚመለከት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ቢሰጡም ከክፍል ውስጥ ምልከታው በተጨማሪ የተቀረፁት ክርክሮችና ውይይቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ፣ አብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች ልምምድ ሳያደርጉ በቀጥታ ወደ ክርክርና ውይይት ማቅረብ እንዲገቡ ሲያደርጉ የታየ ሲሆን፣ ክትትልና ድጋፍ አሰጣጡም ከልምምድ ጋር የተያያዘ ስለሆነ አፈፃፀሙም የተሟላ ነው ማለት አይቻለም።

### 4.1.3 የአፍልቆት ደረጃ ክንውኖች የመረጃ ትንተና

የአፍልቆት ደረጃ ተግባራት ተማሪዎች ከሞላ ጎደል የተግባቦት ፍላጐትን በሚያጭሩና ለተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም ታስበው በሚዘጋጁ ተግባራት እንዲሳተፉ የሚያርጉ ሲሆኑ እንደነዚህ ዓይነት ተግባራት በቋንቋ ትምህርት ክፍል ጠቃሚ ናቸው ። ምክንያቱም ተማሪዎች የራሳቸውን ቋንቋ ለመጠቀም ሲሞክሩ ቋንቋውን በነፃነት ወደሚጠቀሙበት ደረጃ እንዲደርሱ ስለሚያግዙ ነው Harmer (1991፡50)።

ስለዚህ ከዚህ አኳያ መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማዳበር የቀረቡትን ተግባራት እንዴት እንዳቀረቡት የሚያሳይ በቪዲዮ የተደገፈ የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ ስምንት፡- የመምህራንን የአፍልቆት ደረጃ ክንውኖች የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የመናገር ክሂል አቀራረብ ክንውኖች | ት/ቤት 1 ም 1፣2 | | ት/ቤት 2 ም 1፣2 | | ት/ቤት 3 ም 1፣2 | | ድምር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አዎ | | የለም | |
| | | አዎ | የለም | አዎ | የለም | አዎ | የለም | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1.3.1 | መምህሩ/ሯ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባር በተቻለ መጠን ራሳቸውን ችለው እንዲሳተፉ ያማክራል? ይከታተላል ? | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3 | 50 | 3 | 50 |
| 1.3.2 | ተማሪዎች ያለምንም ቁጥጥር እርስ በርሳቸው የሚነጋገሩበት ዕድል አግኝተዋል? ክርክር ያቀርባሉ ? ውይይት ያቀርባሉ ? ጭውውት ያቀርባሉ ? አስተያየት ይሰጣሉ ? | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3 | 50 | 3 | 50 |
| 1.3.3 | መምህሩ/ሯ ተማሪዎች ንግግር ሲያደረጉ ለማረም ጣልቃ ይገባል? | 2 | - | 2 | - | 1 | 1 | 5 | 83.33 | 1 | 16.67 |

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው መምህራን ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባር ሲያከናወኑ የመምራት / የማማከር ሁኔታ ብዙም የሚያበረታታ አይደለም። መምህራን ሀሳባቸውን

ለመግለፅ የ/ስነልቦና (ለምሳሌ በጓደኞቻቸው ፊት መናገር እና ሲሳሳቱ መታረም የሚፈሩ) እንዲሁም ሀሳብ አደራጅቶ የመናገር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በጥንድ /በቡድን ስራ እንዲሳተፉ ቀረብ ብሎ የማደፋፈር አቅማቸው መካከለኛ (50%) ነው፡፡

በምልከታው እንደታየው ተማሪዎች ለመከራከር ፣ ጭውውት ለማቀርብ ወዘተ ፍላጐታቸውን ከማሳየታቸው በላይ በክፍል ውስጥ በቀረቡት ክርክሮችና ጭውውቶች ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ግን ውጤታማ ነበሩ ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም አንዳንዶቹ በተወሰነ ደረጃ ፍርሀት፣ ከፊሎቹ ደግሞ ከልምድ ማጣት የተነሳ ሀሳብን አደራጅቶ የመናገር ችግር ስለነበረባቸው ሀሳባቸውን ሳይቋጩ ድንገት የሚያቆሙበት ሁኔታ ነበር፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በጥንድ / በቡድን ስራዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ ችግሮቻቸውን መቅረፍ ይችሉ ዘንድ የማደፋፈሩን ተግባር መምህራን ቸል ሊሉት አይገባም፡፡

በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት እንደተገለፀው በአፍልቆት ደረጃ ተማሪዎች ማለት የሚፈልጉትን ነገር የራሳቸውን ቋንቋ በመጠቀም ሀሳባቸውን የሚገልፁበት ፣ የንግግር ችሎታቸውን ለማሳደግ በራስ የመተማመን ስሜታቸውን ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ ጥረት የሚያደረጉበት ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ ከግብ ለማድረስም መምህራን ክርክሮችን ውይይቶችን፣ ጭውውቶችን ወዘተ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ግን በምልከታው ወቅት ተማሪዎች እንደነዚህ ዓይነት ተግባራትን ሲያከናውኑ የተገኙት በተወሰነ ደረጃ ነው፡፡ በመማሪያ መፅሐፉ የቀረቡት መልመጃዎች ተማሪዎች በጥንድ/በቡድን ተወያይተው ሪፖርት እንዲያደርጉ የሚጠይቁ፣ ከፊሎቹ ደግሞ ክርክር ፣ ጭውውት እና ውይይት እንዲያቀርቡ የሚያደርጉ ቢሆኑም መምህራኑ መልመጃዎቹን የተገበሯቸው ግን ሁሉንም ሳይሆን በከፊል (50%) ነው ፡፡

በምልከታው ወቅት አንድ ትምህርት ቤት ክርክር ፣ ሌላ ጋር ጭውውት የቀረበ ሲሆን በክርክሩ ተማሪዎች ሀሳባቸውን አደራጅተው የመናገር ፣ ከተቃዋሚ የሚሰነዘር ሀሳብን በማስታወሻ ይዞ ውድቅ የማድረግ ችግር ከዕድሜያቸው አኳያ ቢታይም ሀሳባቸውን ለመግለፅ የነበራቸው ተነሳሽነትና ያደረጉት ጥረት የሚናቅ አልነበረም፡፡ ጭውውት በቀረበበት ትምህርት ቤት ደግሞ አባት / እናትና ልጅ በመሆን በጥንድ በጥንድ ሆነው ፈጥረው ያቀረቡት ጭውውት በይዘቱ ምጥቀትም ሆነ በአቀራረቡ ይበል የሚያሰኝ ነበር፡፡ በሶስተኛው ትምህርት ቤት ደግሞ ክርክሩን ወደጎን በመተው በክርክር ምንነትና ተያያዥ ጉዳዮች ገለፃ በመስጠት ነበር ክፍለ ጊዜው የተጠናቀቀው ፡፡ ስለዚህ በክፍል ውስጥ

ክርክር፣ ጭውውት የማቅረብና በቀረበው ክርክርና ጭውውት ላይ አስተያየት የመስጠት ዕድል ያገኙት የሁለቱ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብቻ ነበሩ።

ሌላው በአፍልቆት ደረጃ በምልከታው ወቅት የታየው ተማሪዎች ንግግር ሲያደርጉ መምህራን እርማት ለመስጠት ጣልቃ የሚገቡና የማይገቡ መሆኑን የሚመለከት ነበር። ከዚህ አኳያ 83.33% የሚሆኑት መምህራን ተማሪዎች ሲከራከሩም ሆነ ጭውውት ሲያቀርቡ ማስተካከያ ለመስጠት ጣልቃ ሲገቡ አልታዩም። Byrne (1976-74) "መምህራን ተማሪዎች ቋንቋውን በራሳቸው የሚጠቀሙበትን ዕድል መፍጠር ፣ የሚገናኑትን ነገር ከመምራት ይልቅ ማለት የሚፈልጉትን እንዲሉ ማድረግ ነው" ያሉትን መርህ አብዛኛቹ መምህራን ተከትለዋል ማለት ይቻላል።

በቪዲዮ ቀረፃ ተደግፎ የቀረበውን መረጃ ስንመለከት ደግሞ በሁለት ትምህርት ቤቶች ክርክር ፣ በአንዱ ውይይት ቀርቧል። ክርክር በቀረበባቸው ሁለት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በሚደግፉትና በሚቃወሙት ሀሳብ ጎን በቡድን በቡድን ሆነው በአንድ ትምህርት ቤት ለ20 ደቂቃ ፣ በሌላው ደግሞ ለ25 ደቂቃ ያህል ክርክር አድርገዋል። ውይይት በቀረበበት ትምህርት ቤትም ቢሆን ውይይቱ በተወሰነ መልኩ በጥቂት ተማሪዎች ተፅዕኖ ያረፈበት ቢሆንም ለ35 ደቂቃ ያህል ሞቅ ያለ ውይይት አድርገዋል። በዚህ ትምህርት ቤት " የወጣትነት ጊዜያችንን እንዴት እናሳልፍ " በሚል ርዕስ ውይይት የተካሄደ ሲሆን አወያይ ሆኖ ከተመረጠው ተማሪ የመድረክ አመራር ብቃት (በተወሰነ መልኩ መድረኩን የመሻማት አዝማሚያ ቢታይበትም)፣ ተማሪዎች ይሰጡት ከነበረው ብስለት የተሞላበት አስተያየት አኳያ ውይይቱ ሲገመገም ተማሪዎች ሁኔታዎች ከተመቻቹላቸውና ለህይወታቸው ቅርበት ያላቸው የመወያያ ርዕሶች ከቀረቡላቸው ለችግሮቻቸው በራሳቸው መፍትሄ የመፈለግ አቅም እንዳላቸው የሚያረጋግጥ ነበር።

ስለዚህ Gower et al. (1995:107-108) እንደጠቀሱት በክፍል ውስጥ የሚቀርብ ውይይት ውጤታማ ይሆን ዘንድ በመጀመሪያ የመወያያው ርዕስ የተማሪዎችን ስሜት የሚያነሳሳና በቂ መረጃ የሚያገኙበት እንዲሆን ማድረግ ፣ ቀጥሎም ውይይቱ በሚፈልገው አግባብ መሄዱን ማረጋገጥ ፣ ማለትም ውይይቱ በተወሰኑ ተማሪዎች ተፅዕኖ ስር እንዳይወድቅና የሁሉንም ተማሪዎች ተሳትፎ ያማከለ እንዲሆን ማድረግ ይገባል። ስለሆነም ችግሩን በመፍታት ውይይቱ በታሰበው መንገድ እንዲጓዝ መምህራን ጉዳዩን ሊያጤኑት ይገባል።

የአፍልቆት ደረጃ ክንውኖችን ለማጠቃለል ከክፍል ውስጥ ምልከታና ከቪዲዮ ቀረፃ የተገኙ መረጃዎች እንዳመለከቱት ከሆነ በምልከታው ጊዜ ሳሳ ብሎ የታየው የአፍልቆት ደረጃ ክንውን የቪዲዮ ቀረፃ በተደረገበት ጊዜ ተጠናክሮ ተገኝቷል። በምልከታው ወቅት ተማሪዎች በቡድን የሰሩትን ሪፖርት የማድረግ ፣ ክርክርና ጭውውት የማቅረብ ክንውን ደረጃ 50% አካባቢ ነበር። በቪዲዮ ቀረፃው ወቅት ግን በሶስቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሁሉም መምህራን ተማሪዎች በቡድን በቡድን ሆነው እንዲከራከሩ ፣ የክፍሉ ተማሪዎች በአንድ ላይ በመሆን እንዲወያዩ አድርገዋል። በመሆኑም አብዛኛዎቹን ተማሪዎች ከሞላጎደል አሳታፊ የሆነው የልምምድ ደረጃ ሳይደረግ በቀጥታ ወደ ክርክርና ውይይት ማቅረብ ቢገባም በአፍልቆት ደረጃ የተወሰኑ ተማሪዎች የራሳቸውን የቋንቋ ችሎታና ሀሳብ አደራጅቶ የመናገር ብቃት ተጠቅመው ሀሳባቸውን የመግለፅ ዕድል አግኝተዋል ማለት ይቻላል።

በቪዲዮ ቀረፃ ተደግፎ የተካሄደው የክፍል ምልከታ፣ የአፍልቆት ደረጃ ክንውን ትንተና ውጤት ምንን እንደሚመስል ከላይ የታየ ሲሆን ይኸው ክንውን በተማሪዎች እይታ ምን እንደሚመስል ደግሞ ቀጥሎ ቀርቧል።

**ሠንጠረዥ ዘጠኝ ፦ የአፍልቆት ደረጃ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መልሶች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | መወሰን ያቅተኛል | | አልስማማም | | ጠቅላላ ድምር | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 5 | በክፍል ውስጥ ንግግር ፣ ጭውውት ፣ ክርክር፣ ውይይት ወዘተ .... ማቅረብ የመናገር ችሎታዬ እንዲያድግ ረድቶኛል። | 134 | 60.9 | 35 | 15.9 | 51 | 23.2 | 220 | 100 |
| 6 | በጥንድ፣ በቡድን ወዘተ በመሆን የመናገር ክሂል ተግባራትን መስራቴ የንግግር ፣ የጭውውት ፣ የክርክር ፣ የውይይት ስርዓትን እንዳውቅ ረድቶኛል። | 147 | 66.8 | 38 | 17.3 | 35 | 15.9 | 220 | 100 |
| 7 | በጥንድ ፣ በቡድን ወዘተ በመሆን ቃለ መጠይቅ መደራረግ ፣ ስዕላዊ መግለጫዎች በሚያስተላልፉት ሀሳብ ላይ መወያየትና መከራከር ወዘተ ሀሳቤን ያለፍርሃት እንድገልጽ ረድቶኛል። | 128 | 58.2 | 50 | 22.7 | 42 | 19.1 | 220 | 100 |

የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ ተማሪዎች እንዲማሩ የሚደረግበት ምክንያት ንግግር፣ ክርክር፣ ውይይት ሲያደርጉ መረጃ አሰባስበው፣አደራጅተውና ተለማምደው ሀሳባቸውን መግለፅ እንዲችሉ ለማድረግ ነው። ስለሆነም የተማሪዎች ተግባቦታዊ ችሎታ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ለመፈተሽ ለቀረበላቸው ጥያቄ 60.9% የሚሆኑ ተማሪዎች በግል ንግግር ማድረጋቸው ፣ በጥንድና በቡድን ጭውውት ፣ ክርክርና ውይይት በክፍል ውስጥ ማቅረባቸው የመናገር ክሂል ችሎታቸውን እንዳሳደገላቸው ገልፀዋል። ቀሪዎቹ ማለትም 15.9% ተማሪዎች ደግሞ በክፍል ውስጥ የቀረቡት ተግባራት የመናገር ችሎታቸውን ለማሳደግ ጉልህ ድርሻ ያበረከቱላቸው መሆኑን የሚጠራጠሩ ሲሆኑ ፣ 23.2% የሚሆኑት ግን ተግባራቱ ሀሳባቸውን በትክክልና በቀለጠፈ መንገድ መግለፅ ያላስቻላቸው መሆኑን ገልፀዋል።

ሌላው ከላይ ከቀረበው ጥያቄ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ የቀረበላቸው ጥያቄ የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ማቅረባቸው እና መከታተላቸው የጭውውት ፣ የክርክር ፣ የውይይት ወዘተ ስርዓት ለማወቅ የረዳቸው መሆንና አለመሆኑን የሚመለከት ሲሆን ፣ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ 66.8% የሚሆኑት ተማሪዎች በክርክር ፣ በጭውውት ፣ በውይይት ጊዜ በመማሪያ መፅሀፋቸው የቀረቡትን መመሪያዎች ወደ ተግባር ለመለወጥ እንደረዳቸው ያምናሉ ። ይህ ማለት ለምሳሌ በክርክር ጊዜ ክርክሩ የተራ በተራ አካሄድ ወይስ እያጠናቀቁ የመሄድ ስልትን እንደሚከተል ማወቅ አንዱ የክርክር ስርዓት ሲሆን ፣ በክርክሩም ሀሳብ እንደተዘረጋ ከተከራካሪዎችሀሳብ ሲቀርብ ሊሎች የሚያዳምጡ መሆኑን ፣ ጥያቄና የተቃራኒ ሀሳብን ውድቅ ማድረጊያ ሀሳብ ቀርቦ ፣ ውሳኔ በድምፅ ወይም በዳኞች የሚሰጥ መሆኑን ማወቅ ከተከራካሪዎች የሚጠበቅ ነው። ስለሆነም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ክርክር ፣ ጭውውት ውይይት በክፍል ውስጥ ማቅረባቸው እነዚህንና ሌሎች መሰል ስርዓቶችን ለማወቅ እንደረዳቸው አረጋግጠዋል። ከዚህ አስተሳሰብ ውጪ የሆኑት ተማሪዎች ግን በጉዳዩ ግልፅ ግንዛቤ የሌላቸውና በሀሳቡ የማይስማሙ ናቸው።

በመጨረሻም የቀረበላቸው ጥያቄ የተለያዩ የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ መለማመዳቸው ሀሳባቸውን ያለፍርሃት ለመግለፅ ያስቻላቸው ወይም ያላስቻላቸው መሆኑን የሚገልፅ ነበር ። ከግማሽ በላይ 58.2% የሚሆኑት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መከራከራቸው፣ መወያየታቸው ፍርሃትን በማስወገድ ሀሳባቸውን በንግግር የመግለፅ ችሎታቸውን እንዳዳበረላቸው ገልፀዋል። ሌሎቹ ግን በሀሳቡ የሚጠራጠሩና የማይስማሙ ናቸው።

ከላይ የቀረቡትን ተያያዥ ጉዳዮች ለማጠቃለል የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት በሚለው እንደተገለፀው የመናገር ክሂል ተግባራትን በጥንድ ፣ በቡድን ማደራጀትና እንዳንዱም ሁሉንም ተማሪ የሚያሳትፍ ዕድል መፍጠር የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ችሎታ ለማሳደግ ፣ የእያንዳንዱን የመናገር ክሂል ተግባራት በሚተገበርበት ጊዜ ተማሪዎች የሚከተሏቸውን ስርዓቶች ለማወቅ፣ ተማሪዎች ያሉባቸውን ስነልቦናዊ ችግሮች በመቅረፍ በራስ የመተማመን ስሜት ለማዳበር እንደሚረዳ ጥርጥር የለውም። ከላይ እንደተገለፀው መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ይህንኑ ሀሳብ አረጋግጠዋል።

የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ችሎታን ለመፈተሽ ከራሳቸው ከተማሪዎች በተጨማሪ መምህራን የተማሪዎቻቸው ሀሳባቸውን በንግግር የመግለፅ ብቃት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለቀረበላቸው ጥያቄ አንድ መምህር የተወሰኑ (አንድ አራተኛ የሚሆኑ) ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋችን ስለሆነ መናገር እንችላለን ብለው ስለሚያስቡ ለመናር ክሂል የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ ነው። በዚህም ምክንያት መረጃ አሰባሰበውና አደራጅተው ሀሳባቸውን በንግግር የመግለፅ ችሎታቸው ዝቅተኛ ነው ሲሉ ገልፀዋል። ሁለት መምህራን ደግሞ በጥቅሉ ከሌሎች ክሂሎች አንፃር ሲታይ የመናገር ክሂላቸው የተሻለ ነው፤ በዝርዝር ሲታይ ደግሞ የተወሰኑ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በብቃት የመግለፅ ብቃት አላቸው። አብዛኛዎቹ (75%) ደግሞ የቻሉትን ያህል በንግግር ሀሳባቸውን ለመግለፅ ይሞክራሉ ሲሉ መልሰዋል።

በጥቅሉ ሲታይ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውም ምላሽ በመጠኑ ከመጋነኑ በስተቀር ከሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተገኙ መረጃዎች ውጤት ብዙም የጎላ ልዩነት አይታይበትም ። ምልከታ በተደረገበት ጊዜ በአፍልቆት ደረጃ ሳሳ ብሎ የታየው የተማሪዎች የርስበርስ መስተጋብር የቪዲዮ ቀረፃ በተደረገበት ወቅት በቀረቡት ክርክሮችና ውይይቶች ተጠናክሮ ታይቷል። የመከራከርና የመወያየት ዕድል ካገኙት ተማሪዎች መካከል የተወሰኑት ተማሪዎች በቂ ዝግጅት የማድረግ ፣ ሀሳባቸውን አደራጅተው የመናገር ፣ የሀሳብ ማሟያ ዘዴዎችን (fillers) ተጠቅሞ ሀሳብ የማስተላለፍ ችግሮች ከልምምድ ማነስ የተነሳ ቢታይም፣ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በተሳካ ሁኔታ ለመግለፅ ጥረት ሲያደርጉ ታይቷል። ስለዚህ የክፍል ውስጥ ምልከታው ውጤት በክፍል ውስጥ ንግግር ፣ ጭውውት ፣ ክርክር ፣ ውይይት ማቅረባችን የመናገር ችሎታችንን አሳድጎልናል፤ ስርዓቱን እንድናውቅና ፍርሃትን በማስወገድ በራስ የመተማመን ስሜት እንድንፈጥር ረድቶናል በማለት ከመለሱ ተማሪዎች አመለካከት ጋር

በመሰረተ ሀሳብ የሚጣጣም እንጂ ብዙም የሚቃረን አይደለም ። የመምህራኑም መልስ ቢሆን ከምልከታውና ከተማሪዎች ምላሽ ውጤት ጋር የሚጋጭ አይደለም። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለፅ ተነሳሽነቱ እንዳላቸው የገለፁ ሲሆን ተነሳሽነቱና ጥረቱ ካለ ግን መምህራን ሳቢና አነቃቂ የመከራከሪያ ፣ የመወያያ ወዘተ ርዕሶችን በክፍል ውስጥ በማቅረብ ፣ የጥንድ ፣ የቡድን ስራን ወዘተ በመናገር ክሂል አቀራረብ በማበረታታት የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ አሁን ካለበት ወደላቀ ደረጃ ማድረስ ይቻላል።

### 4.1.4 የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ክንውኖች የመረጃ ትንተና

እንደ Scrivener (1994፡109) እምነት የእርማት አላማዎች በራስ የመተማመን ስሜት ለመፍጠር ፣ ግንዛቤን ለማሳደግ እና ተማሪዎች በቋንቋ አጠቃቀማቸው የበለጠ ትክክለኛ እንዲሆኑ ለመርዳት ነው። ከዚህ አኳያ በመናገር ክሂል አቀራረብ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ እንዴት እንደተከናወነ ማየት ይቻል ዘንድ ክንውኑ ቀጥሎ ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ አስር ፡- የመምህራንን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የመናገር ክሂል አቀራረብ ክንውኖች | ት/ቤት 1 | | ት/ቤት 2 | | ት/ቤት 3 | | ድምር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ም1፣2 | | ም1፣2 | | ም1፣2 | | አዎ | | የለም | |
| | | አዎ | የለም | አዎ | የለም | አዎ | የለም | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1.4.1 | በመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ ወቅት ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ተሰጥቷል ?<br>• ተማሪው ራሱ ስህተቱን እንዲያዩና እንዲናገር በማድረግ፣<br>• ሌሎች ተማሪዎች የተማሪውን ስህተት እንዲያርሙ በማድረግ<br>• ተማሪዎች የሰሩትን ስህተት ራሱ መምህሩ በማረም | 1 | 1 | - | 2 | 1 | 1 | 2 | 33.33 | 4 | 66.67 |

ከላይ ከሰንጠረዥ አስር እንደሚታየው የክፍል ውስጥ ምልከታ በተደረገበት ጊዜ አብዛኛዎቹ መምህራን (66.67%) በመናገር ክሂል አቀራረብ በተማሪዎች ላይ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጐኖች በሚመለከት ምጋቤ ምላሽ አልሰጡም። ቀሪዎቹ መምህራን ግን በክንውኑ ወቅት በታዩ ዋና ዋና ችግሮች ላይ የተማሪዎችን አስተያየት መነሻ በማድረግ ፣

በተወሰነ መልኩ ደግሞ ተማሪዎች የሰሩትን ስህተት ራሳቸው መምህራን ነቅሰው በማውጣት እርማት ሰተዋል። የክፍል ውስጥ ምልከታውን ለማጠናከር የተደረገው የቪዲዮ ቀረፃ መረጃ ሲታይ ደግሞ አንድ መምህር የተማሪዎችን አስተያየት መነሻ በማድረግ ተማሪዎች ያቀረቡት ክርክር በዝግጅት ማነስ ምክንያት የተወሰነ ቀሬነት ቢታይበትም ጥረታቸውን በማበረታታትና ምስጋና በማቅረብ አጠቃለዋል። ሌላው መምህር ደግሞ በክርክሩ ወቅት የታዩ ችግሮችን በጥያቄ መልክ በማንሳት ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡ ያደረጉ ሲሆን ፣ ሶስተኛው መምህር ውይይቱ የመጀመሪያ በመሆኑ የተወሰኑ ተማሪዎች ተሳትፎ ጎልቶ ቢታይም ተማሪዎች ያደረጉት ተሳትፎ አበረታች እንደሆነ በመግለፅ በራሱ ማጠቃለያ ሰጥቷል። ምጋቤ ምላሽ መስጠቱ አንድ ጉዳይ ሆኖ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ ስልት ግን የተማሪዎችን አስተያየት መነሻ አድርጎ ቢሰጥ የተማሪዎች የእርበርስ ተራክቦና በራስ የመተማመን ስሜት ይበልጥ ሊጎለብት ይችላል። ስለዚህ በምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ የተማሪዎች ተሳትፎ እንዲጎለብበት ማድረግ ከመምህራን ይጠበቃል።

**ሰንጠረዥ አስራ አንድ ፦ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መ ል ሶ ች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | መወሰን ያቅተኛል | | አልስማማም | | ጠቅላላ ድምር | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 8 | የጭውውት ፣ የክርክር፣ የውይይት ወዘተ ተግባራት በክፍል ውስጥ ከቀረቡ በኋላ አስተያየት እሰጣለሁ ። | 132 | 60 | 40 | 18.2 | 48 | 21.8 | 220 | 100 |
| 9 | መምህሩ/ሯ ስህተታችንን በቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስ በርስ እንድንተራረም ያደርጋሉ። | 116 | 52.7 | 44 | 20 | 60 | 27.3 | 220 | 100 |
| 10 | በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የመናገር ክሂል ተግባራት ከህይወት ልምዷ ጋር የተቆራኙ ናቸው ። | 88 | 40 | 88 | 40 | 44 | 20 | 220 | 100 |

በቋንቋ ትምህርት ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በተለያዩ መንገዶች ሊሰጥ እንደሚችል ከላይ ተጠቁሟል። Wajnryb (1992፡102) "ከጓደኛ የሚሰጥ እርማት ከሌላው የበለጠ አስተማሪ ነው። ምክንያቱም ለቋንቋው ተመሳሳይ ተጋላጭነት ( Exposure ) ካለው ሰው የሚሰነዘር ስለሆነ ነው" በማለት ምጋቤ ምላሽ የግድ በመምህሩ ብቻ መስጠት

እንደሌለበት ያስገነዝባሉ፡፡ Sesnan (1997፡181) በበኩላቸው "ብዙ ሰዎች በቋንቋ ትምህርት ህፃናት ሲታረሙ ስሜታቸው ይጐዳል ብለው ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ህፃናት በዕለት ተዕለት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንደሚታየው (ለምሳሌ ሲጫወቱ) እርስ በርስ ይተራረማሉ፤ መተራረሙንም በደስታ ሊቀበሉት ይታያል" ሲሉ ሀሳቡን ያጠናክሩታል፡፡ ስለዚህ በመናገር ክሂል አቀራረብ የሚደረግ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ተማሪዎች በሂደቱ እንዲሳተፉና እርስ በርስ እንዲተራረሙ ከተደረገ በኋላ በመምህራን ቢጠቃለል ከላይ እንደተገለፀው የተማሪዎች የእርስበርስ ተራክቦና በራስ የመተማመን ስሜት ወደላቀ ደረጃ ሊሸጋገር ይችላል፡፡

ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት መምህራን ተማሪዎች በመናገር ክሂል አቀራረብ እንዲሳተፉ ማድረግንና የትኛውን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ስልት እንደሚከተሉት ለተማሪዎች ጥያቄዎች ቀርቦላቸው ነበር፡፡ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ 60% የሚሆኑት ተማሪዎች በመናገር ክሂል ክንውን ወቅት ጭውውት ፣ ክርክር ፣ ውይይት ወዘተ ካቀረቡ በኋላ አስተያየት እንደሚሰጡ የገለፁ ሲሆን ፣ 52.7% የሚሆኑ ደግሞ መምህራን የተማሪዎችን ስህተት በቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስ በርስ እንዲተራረሙ እንደሚያደርጉ አረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች የተለያዩ የመናገር ክሂል ተግባራትን ካቀረቡ በኋላ አስተያየት እንደሚሰጡና መምህራኑም ተማሪዎች እርስበርስ እንዲተራረሙ እድል እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡

በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ለተማሪዎች ህይወት ቅርበት ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን በሚመለከት ለቀረበው ጥያቄ ግን መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ 40% የሚሆኑት በጉዳዩ ዙሪያ ግልፅ ሀሳብ የሌላቸው፣ 40% የሚሆኑ ደግሞ የማይስማሙ ናቸው፡፡ ሁኔታው በመፃህፍት ዝግጅት ወቅት የመናገር ክሂል ተግባራት ሲካተቱ በዓይነት የተለያዩ መሆን እንዳለባቸው እንዲሁም የተማሪዎችን ዕድሜ ፣ ፆታ፣ ዳራዊ ዕውቀት ወዘተ ያገናዘቡ መሆን እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በጥቅሉ በመናገር ክሂል አቀራረብ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሲታይ በምልከታ ወቅት እንደታየው ከሆነ አብዛኛዎቹ መምህራን (66.67%) አልተገበሩትም፡፡ ሙከራ ካደረጉትም ውስጥ ሁለት መምህራን ብቻ የተማሪዎችን አስተያየት መነሻ በማድረግ በታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ላይ አስተያየት በመስጠት አጠቃለዋል፡፡ ምልከታውን ለማጠናከር የተደረገው የቪዲዮ ቀረፃ መረጃ ውጤት እንደሚያመለክተው ደግሞ ሁሉም መምህራን ምጋቤ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ሁለቱ ብቻ የተማሪዎችን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ስለሆነም የምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ የተማሪዎችን አስተያየት መነሻ በማድረግ ቢስጥ Gower et. al (1995፡169) እንዳሉት በምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ የተማሪዎች ተሳትፎ መታየቱ የመማር ሂደቱ የበለጠ ትብብራዊ እንዲሆን ፣ ተማሪዎች በመምህሩ የሚኖራቸው የጥገኝነት ስሜት እንዲቀንስ ፣ በተማሪዎች መካከል መደጋመጥ እንዲጎለብት በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ከዚህ አኳያ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ ተከታታይነትና ወጥነት ባይኖረውም መምህራን ተማሪዎች በሂደቱ እንዲሳተፉ ያደረጉት ጅምር ከሞላጎደል አበረታች ነው ። ይህ ማለት ግን አፈፃፀሙ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት አይደለም የተማሪዎችም ምላሽ ይህንኑ ሀሳብ የሚደግፍ ነው። ምክንያቱም መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ ግማሽ (52.7%) የሚሆኑት ብቻ ናቸው መምህሩ በቀጥታ በራሱ ምጋቤ ምላሽ አይሰጥም ሲሉ የመለሱት።

## 4.2. የመምህር-ተማሪ ተራክቦ ውቅሮች የመረጃ ትንተና

የመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ ከመምህራን ንግግር ተፅዕኖ ምን ያህል እንደተላለቀ ለማየት የክፍል ውስጥ ምልከታ የተደረገ ሲሆን በእያንዳንዱ የአቀራረብ ደረጃ መምህራን፣ መምህራንና ተማሪዎች ፣ ተማሪዎች እርስበርስ የተገለገሉበትን ጊዜ ለማወቅ ሰዓት በመያዝ ለመመዝገብ ተሞክሯል።

**ሰንጠረዥ አሥራ ሁለት ፡- በመናገር ክሂል አቀራረብ የመምህራንና የተማሪዎችን ተራክቦ ውቅር የሚያሳይ መግለጫ**

| የመናገር ክሂል የአቀራረብ ደረጃዎች | ትምህርት ቤት 1 የወሰደው ጊዜ በደቂቃ | | ትምህርት ቤት 2 የወሰደው ጊዜ በደቂቃ | | ትምህርት ቤት 3 የወሰደው ጊዜ በደቂቃ | | ❖ ለእያንዳንዱ የአቀራረብ ደረጃ የተሰጠ ጊዜ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ም 1 | ም 2 | ም 1 | ም 2 | ም 1 | ም 2 | በቁጥር | % |
| የአቀራረበብ ደረጃ | መመ | 14 መመ | 14 መመ | 10 መመ | 12 መመ | መመ | 6 | 15 |
| የልምምድ ደረጃ | መመ | አልተከናወነም | አልተከናወነም | 12 መተ | 8 መተ | መመ | 10 | 25 |
| የአፍልቆት ደረጃ | መመ | 14 ተተ | 22 ተተ | 15 ተተ | 15 ተተ | መመ | 18 | 45 |
| የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ | አልተሰጠም | 5 መተ | አልተሰጠም | አልተሰጠም | አልተሰጠም | 8 መተ | 6 | 15 |

መግለጫ፡-

- አንድ ክፍለ ጊዜ 40 ደቂቃ ነው፡፡
- መመ - የመምህር ንግግር ብቻ
- መተ - የመምህር - ተማሪ ተራክቦ
- ተተ - የተማሪዎች የርስበርስ ተራክቦ

❖ ከሶሬሳ አፀደ ህጻናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህር የክፍል ውስጥ የመናር ክሂል አቀራረብ የተወሰደ ናሙና፡፡

የአቀራረብ ደረጃ ተማሪዎች በምን ጉዳይ ላይ ንግግር እንደሚያደርጉ ለማስተዋወቅ ፣ በክንውኑ ወቅት ምን እንደሚሠሩ መመሪያ ለመስጠት መምህራን የሚጠቀሙበት ጊዜ ሲሆን በተዛማጅ ፅሁፍ እንደተገለፀው በዚህ ደረጃ ብዙ ጊዜ ማጥፋት ተማሪዎች ቋንቋውን የሚለማመዱበትን ጊዜ ስለሚሻማ ተገቢነት የለውም፡፡ ከዚህ አኳያ ከሰንጠረዥ አስራ ሁለት እንደሚታየው እያንዳንዱ መምህር በአማካይ 12 ደቂቃ አካባቢ የተጠቀመ ሲሆን ይህም ለትምህርቱ ከመደበው ጊዜ 30% መሆኑ ነው ፡፡ ስለሆነም መምህራን ለትምህርቱ ከተመደበው ጊዜ አኳያ ሲታይ የሌሎች የመናገር ክሂል የአቀራረብ ደረጃዎችን ጊዜ ተሻምተዋል ማለት ይቻላል፡፡

የልምምድ ደረጃ መምህራን ብዙ ከመናገር በመቆጠብ ተማሪዎች በልምምዱ እንዲሳተፉ እድል የሚሰጥበት ሲሆን አፍልቆ ደረጃ ደግሞ ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግ መሠረት በማድረግ የራሳቸውን የቃላትና የሀሳብ አደረጃጀት ችሎታ ተጠቅመው ሀሳባቸውን በነፃነት የሚልፁበት እንደሆነ በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ምልከታ ተገልፆአል፡፡ ስለሆነም በሁለቱም የአቀራረብ ደረጃዎች የተማሪዎች የርስ በርስ መስተጋብር የሚጎለብትበትና የመምህራን የንግግር ጊዜ በእጅጉ የሚቀንስበት ነው ፡፡

ከዚህ መርህ አንፃር በልምምድ ደረጃ የመምህራኑ አፈፃፀም ሲታይ በሶስት ትምህርት ቤቶች ከተደረጉት ስድስት ምልከታዎች ውስጥ ሁለቱ በመምህር - መር ዘዴ በመቅረባቸውና በሁለቱ ምልከታዎች ደግሞ የልምምድ ደረጃ ሳይከናወን መምህራኑ ወደ አፍልቆት ደረጃ በመሸጋገራቸው የተማሪዎች የእርስ በርስ መስተጋብር አልታየም፡፡ በቀሪዎቹ ሁለት ምልከታዎች ግን ተማሪዎች ጭውውትና የቡድን ሪፖርት ከማቅረባቸው በፊት በመምህራን አመቻችነት ልምምድ በማድረግ ወደ አፍልቆት ደረጃ ስለተሸጋገሩ የተማሪዎች የርስበርስ ተራክቦ በተወሰነ ደረጃ ታይቷል፡፡ ተማሪዎች ለልምምድ የተጠቀሙበት ጊዜ ሲታይ ከቀረበው ናሙና ጋር ተቀራራቢ ነው፡፡ የአፍልቆት ደረጃን

ስንመለከት ደግሞ ከስድስቱ ምልከታዎች አራቱ የተማሪዎች ተሳትፎ የታየባቸው ሲሆኑ በአራቱም ምልከታዎች ከቀረበው ናሙና አኳያ ሲታይ ለአፍልቆት የዋለው ጊዜ በቂ ነው ማለት ይቻላል። ሁለቱ ምልከታዎች ግን የመምህራን የንግግር ጊዜ ጎልቶ የታየባቸው ናቸው። የምጋቤ ምላሽ አሰጣጡም ሲታይ ከ6 ምልከታዎች ውስጥ በሁለቱ ምልከታዎች ብቻ ምጋቤ ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ፣ ሁለቱም የመምህርና ተማሪ መስተጋብር የታየባቸው ነበሩ።

በጥቅሉ የምልከታው ውጤት ሲታይ የመምህራን የንግግር ጊዜ በአቀራረብ ደረጃና በምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ጎልቶ ታይቷል። በልምምድ ደረጃ የተማሪዎች መስተጋብር በተወሰነ ደረጃ የታየ ሲሆን፣ በአፍልቆት ደረጃ ደግሞ የተማሪዎች መስተጋብር የተሻለ ነበር ማለትይቻላል። ምልከታውን ለማጠናከር የተቀረፀውን የቪዲዮ መረጃ ውጤት ስንመለከት ደግሞ ክርክር በቀረበባቸው ሁለት ትምህርት ቤቶች ከዝግጅት ማነስ ይመስላል በአማካይ 22.5ደቂቃ (የክፍለ ጊዜውን 56%) ተጠቅመዋል። ውይይት በቀረበበት ትምህርት ቤት ግን ክፍለጊዜው የመጨረሻ ስለነበር 35 ደቂቃ (የክፍለ ጊዜውን 87.5%) ተማሪዎች ተወያይተዋል። ለምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ግን ክርክርም ሆነ ውይይት በተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉም መምህራን ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ጊዜ ተጠቅመዋል። ስለዚህ ተማሪዎች የተሻለ የመናገር ዕድል አግኝተዋል።

**ሰንጠረዥ አስራ ሶስት ፡- የመምህር - ተማሪ ተራክቦ ውቅርን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | መ ል ሶ ች | | | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በመምህሩ ንግግር ብቻ ይሸፈናል | | በተማሪዎች የእርስበርስ መስተጋብር ይሸፈናል | | በመምህሩና በተማሪው አቻዊ መስተጋብር ይሸፈናል | | | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 11 | በመናገር ክሂል ተግባራት ክንውን ወቅት ክፍለ - ጊዜው አብዛኛው ጊዜ | 38 | 17.3 | 46 | 20.9 | 136 | 61.8 | 220 | 100 |

ከላይ ከቀረበው የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ እንደሚታየው መጠይቁን ከሞሉት 220 ተማሪዎች ውስጥ 139 (61.8%) የሚሆኑት በመናገር ክሂል አቀራረብ የመምህር - ተማሪ ተራክቦ ውቅር ከሞላ ጎደል አቻዊ /እኩል መሆኑን ገልፀዋል። ስለዚህ

የተማሪዎችን መስተጋብር አሁን ካለበት ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ መምህራን የየራሳቸውን የንግግር ጊዜ በመቀነስ ተማሪዎች በጥንድ ፣ በቡድንና ክፍሉ በአንድ ላይ በመሆን የተለያዩ መናገር ክሂል ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በዚህ ርዕስ የተነሳውን ጉዳይ ለማጠቃለል በክፍል ውስጥ ምልከታው የመምህራን የንግግር ጊዜ ከሞላጎደል ጎልቶ ታይቷል። በቪዲዮ ተደግፎ በቀረበው ምልከታ ግን የተማሪዎች የንግግር ጊዜ ከመምህራን በጣም የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ ደግሞ የመምህር - ተማሪ ተራክቦ አቻዊ እንደሆነ ያሳያል። በአጠቃላይ ከሶስቱም መሣሪያዎች የተገኘው የመረጃ ውጤት ሲታይ ግን በመናገር ክሂል አቀራረብ የተማሪዎች የርስበርስ መስተጋብር ጎልቶ አልወጣም። ስለዚህ መምህራን የተማሪዎች የእርስ በርስ ተራክቦ ጉልህ ቦታ እንዲኖረው የራሳቸውን የንግግር ጊዜ በመቀነስ የተማሪዎች የርስበርስ መስተጋብር እንዲያድግ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## 4.3 የመምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ግንዛቤ የመረጃ ትንተና

መምህራን ሙያቸውን በግል የንባብ ባህል የሚያዳብሩ ቢሆንም ከተማሩበት የትምህርት ተቋም ወይም በስራ ላይ በሚሰጡ አጫጭር ስልጠናዎች ከአዳዲስ አስተሳሰቦችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ሊተዋወቁ እንደሚችሉ ይታመናል። ከዚህ አኳያ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ግንዛቤ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆን የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ለመምህራኑ “ከተመረቁበት የትምህርት ተቋም የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የወሰዱት ኮርስ አለ? የተማሩትስ ኮርስ ለማስተማር ምን ያህል አግዞዎታል? ” የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ሁለት መምህራን የወሰድነው ኮርስ የለም ሲሉ ፣ አንድ መምህር ግን የአራቱን የቋንቋ ክሂሎች ፅንሰ ሀሳብና አቀራረብ በሚመለከት ኮርስ መውሰዱን ገልፆአል። “ ለማስተማር ምን ያህል አግዞዎታል? “ ለሚለው ጥያቄ ግን የተማርኩበትን ማስታወሻ አይቼው ስለማላውቅ በእርግጠኝነት ጠቅሞኛል ማለት የምችል አይመስለኝም በማለት መልሷል።

ለመምህራኑ የቀረበው ሁለተኛ ጥያቄ “ በስራ ላይ እያሉ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት ስልጠና ወስደዋል?” የሚል ሲሆን ሁሉም መምህራን የወሰዱት ስልጠና እንደሌለ መልሰዋል።

ከቃለ- መጠይቁ ከተገኘው ምላሽም መምህራን በተማሩበት ተቋምም ሆነ የስራ ላይ ስልጠና ባለማግኘታቸውን የመናገር ክሂልን ለምን እንደሚያስተምሩ ፣ የክሂሉን ባህርያትና ክሂሉን ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራት ዓይነቶችን ፣ ክሂሉን በማስተማር ላይ እያሉ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮችና ችግሮቹን ለማስወገድ የሚወሰዱ ርምጃዎችን በሚመለከት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህ ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ማሳደሩ ግልፅ ነው።

መምህራን የሚያስተምሩትን የትምህርት ዓይነት ጠንቅቆ ከማወቅ በተጨማሪ የሚያስተምሩትንም ትምህርት እንዴት ማቅረብ እንዳለባቸው ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል። ስለሆነም መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ለማቅረብ መሠረታዊ የሆኑ ቅድም ተከተሎችን ( Procedures) ማወቅ ይኖርባቸዋል። ከዚህ አኳያ ቀደም ሲል በክፍል ውስጥ ምልከታ እንደታየው መምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት ያላቸው ግንዛቤ በጥቅሉ ሲታይ ዝቅተኛ ነው። ምክንያቱም በአቀራረብ ደረጃ መምህራን ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንዳለባቸው ከሞላ ጎደል ግንዛቤው ቢኖራቸውም ተማሪዎች ወደ አፍልቆት ደረጃ ከመሸጋገራቸው በፊት በጥንድ ፣ በቡድን ወዘተ በመሆን የመናገር ክሂል ተግባራትን እንዲለማመዱና ከልምምዱ በኋላ ክርክር ፣ ውይይት ፣ ጭውውት እንዲያቀርቡ ሲያደርግ የታየ መምህር አልነበረም።

የመናገር ክሂል አቀራረብ እንደተከናወነ ምጋቤ ምላሽ መስጠት የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት ለማዳበርና ተማሪዎች በቋንቋ አጠቃቀማቸው የበለጠ እንዲሻሻሉ ለመርዳት የሚያግዝ ሲሆን የመምህራኑ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ተከታታይነት ያለው አልነበረም። አንዳንድ ጊዜ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ይታለፋል።

በጥቅሉ ከክፍል ውስጥ ምልከታና ከራሳቸው ከመምህራን ቃለ - ምልልስ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ መምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብን የሚያከናውኑት በልምድ በአገኙት ግንዛቤ እንጂ ዘመናዊ ዕውቀትና ክህሎት ተላብሰው ነው ማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም ለቃለ - መጠይቅ ከቀረቡት ሶስት መምህራን ሁለቱ ከተመረቁበት የትምህርት ተቋምም ሆነ በስራ ላይ እያሉ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት ያገኙት ስልጠና አልነበረም። ስልጠና የወሰደውም ቢሆን " ሉሚ ካልመጠጡት ......" እንዲሉ አዘውትሮ ሲሰራበት አልታየም።

## 4.4 በመናገር ክሂል አቀራረብ የተከሰቱ ችግሮች የመረጃ ትንተና

በተዛማጅ ፅሁፍ እንደተጠቀሰው በመናገር ክሂል አቀራረብ ጊዜ ክንውኑን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎች በመምህራን ፣ በተማሪዎች እንዲሁም በሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎች የሚከሰቱ ችግሮች ይኖራሉ። የክፍል ውስጥ ምልከታና የቪዲዮ ቀረፃ በተካሄደበት ወቅት በመናገር ክሂል አቀራረብ የታዩ ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ተደጋግሞ እንደተባለው መምህራን በመናገር ክሂል የተለያየ የአቀራረብ ደረጃዎች የመረጃ አቀባይነት ፣ የተሳታፊነት ፣ የመከታተል (የማማከር) ሚና አላቸው። ስለሆነም መምህራን በአቀራረብ ደረጃ በዕለቱ ትምህርት የተመረጠውን ተግባር ግልፅነት ባለው መንገድ ማቅረብ ፣ በልምምድ ደረጃ ደግሞ ተማሪዎች በልምምዱ እንዲሳተፉ ማበረተታትና እገዛ ማድረግ ሂደቱን መከታተል ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ አኳያ የመምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ሲታይ ሶስቱን ደረጃዎች ተከትሎ የሚቀርብ አይደለም። ከሞላ ጎደል የትውውቅ ደረጃ ከተደረገ በኋላ የልምምድ ደረጃ ሳይከናወን ወደ አፍልቶት ደረጃ መሸጋገር በሁሉም መምህራን ላይ የታየ ጉልህ ችግር ነው፡

ተማሪዎች የቡድን ሪፖርት ፣ ክርክር ፣ ጭውውት ፣ ውይይት ካቀረቡ በኋላ የተማሪዎችን ስሜት በማይነካ መልኩ ጉድለቶችን ማሳየት በቀጣይ ጊዜ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፅሙ ይረዳል። ስለዚህ መምህራን ተማሪዎች የመናገር ክሂል ተግባራትን ካቀረቡ በኋላ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡ ማበረታታና የተማሪዎችን ሀሳብ መነሻ አድርጎ ጉልህ በሆኑ ችግሮች ላይ የተጠቃለለ ምጋቤ ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ነው። ይህን በማድረግ በኩልም ክፍተት እንዳለ በምልከታው ጊዜ ማየት ተችሏል።

የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ታስበው በመመሪያ መጽሐፉ የቀረቡ ተግባራትን በዋዛ ፈዛዛ በማየት ሳያከናውኑ ማለፍ ሌላው በምልከታው ወቅት የታየ ችግር ነው። የቀረቡት መልመጃዎች ትዕዛዝ “ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው ሪፖርት ያቀረቡ ፣ የክርክር መመሪያውን መሠረት በማድረግ ከቀረቡት የመወያያ ርዕሶች አንዱን መርጠው ይከራከሩ” እያለ ክፍለ ጊዜውን ገለፃ በመስጠት ጨርሶ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የሚያዳብሩ ተግባራትን ማለፍ ተስተውሏል፡

በመጨረሻም በቡድንም ይሁን ተማሪዎች በአንድነት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ሁሉን ያማከለ ተሳትፎ እንዲኖር የመምህራን ክትትል ማነስ የሚጠቀስ ችግር ነው ። ለምሳሌ ያህል ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሲወያዩ በተለያየ ምክንያት (በፍርሃት ፣

የሚናገሩት ነገር በማጣት ወዘተ ሊሆን ይችላል) የማይሳተፉ ልጆችን ተሳትፎአቸው እንዲጐለብት አለመርዳት፣ በተቃራኒው ደግሞ የተወሰኑ ልጆች በተደጋጋሚ እድል እየተሰጣቸው በውይይቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲያሳድሩ እወያዩ ለሁሉም ተማሪዎች ዕድል እንዲሰጥ ጠጋ ብሎ ከማማከር ይልቅ መምህራን ራስን ገለልተኛ አድርጎ ማየት፣ በክፍል ውስጥ ምልከታውም ሆነ በቪዲዮ ቀረፃው የታዩ ችግሮች ናቸው።

የክፍል ውስጥ ምልከታ በተደረገበት ጊዜ ሌላው ለማየት የተሞከረው ጉዳይ ተማሪዎችን የሚመለከቱ ችግሮች ሲሆኑ፣ ሴት ተማሪዎች ሲከራከሩ ወንዶች፣ ሴቶች የሚናገሩትን ሀሳብ አለማክበርና በማኩተምተም ሀሳባቸውን ለማሳከር መሞከር በአንድ ትምህርት ቤት ታይቷል። ይህም ድርጊት ሴት ተከራካሪዎች ሀሳባቸው አደራጅተው እንዳይናገሩና እንዲደነጋገሩ በማድረግ የበኩሉን አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። መምህሩ ተገሳፅ ለመስጠትና ለማስቆም ቢሞክሩም ሴቶች በሚከራከሩበት ወቅት አልፎ አልፎ ማኩተምተም ይሰማ ነበር። ሁኔታው ከልጆቹ ዕድሜ ዝቅተኛ መሆን የተነሳ የተከሰተ ስለሆነ እንደዘላቂ ችግር ላይታይ ይችላል። ችግሩ በሌሎች ትምህርት ቤቶች ስላልተከሰተ የተወሰኑ ልጆች የግል ችግርም ሊሆን ይችላል። በወቅቱ ግን ሴት ተከራካሪዎች በተረጋጋ ሁኔታ የመከራከሪያ ሀሳባቸውን እንዳያቀርቡ በማድረግ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል።

በምልከታው እና በቪዲዮ ቀረፃው የታየው ሌላው ችግር ተከራካሪዎች በሚከራከሩበት ርዕሰ ዙሪያ ዝግጅት ባለማድረጋቸው ምክንያት በተሰጣቸው ጊዜ የሚናገሩት ነገር ማጣት ሲሆን ፣ ችግሩን ለመቅረፍ ተማሪዎች ክርክር /ውይይት ከማቅረባቸው በፊት በልምምድ ደረጃ በክፍል ውስጥ በቡድን ሆነው መረጃ እንዲያመነጩ ማድረግ ከመምህራን ይጠበቃል። ተማሪዎች ክርክሩን /ውይይቱን ከክፍል ውጪ ቀደም ብለው ተዘጋጅተው በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ የሚያቀርቡ ከሆነ ደግሞ ከመፃህፍት ፣ ከጋዜጦች ፣ ከሬዲዮ ወዘተ የሰበሰቧቸውን መረጃዎች ዋና ዋና ነጥቦች በመልክ በመልክ አደራጅተውና ተለማምደው እንዲመጡ ማድረግ ችግሩን ሊፈታው ስለሚችል መምህራን ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል።

በአጠቃላይ የክርክርና የውይይት ስርዓትን (ለምሣሌ በክርክር /በውይይት መግቢያ፣ ማጠቃለያ ላይ አስፈላጊ የሆኑ አባባሎችን) አለማወቅ፣ ከመረጃ እጥረትና ከልምድ ማነስ መፍራት ፣ ከተቃዋሚ ወገን የሚሰነዘሩ ሀሳቦችን በማስታወሻ ይዞ ውድቅ ማድረግ ወዘተ በክፍል ውስጥ በቀረቡ ክርክሮች /ውይይቶች ከሞላ ጎደል የታዩ ችግሮች ናቸው ማለት ይቻላል።

በመጨረሻም ከመናገር ክሂልን አቀራረብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዩች ለማየት የተሞከረ ሲሆን አብክመ ትምህርት ቢሮ (2002 ጥቅምት) ከ5ኛ - 8ኛ ያሉት የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ ስታንዳርድ 6.2 በ7.26 = 50.24 ካሬ (ገጽ 8) ሲሆን ፣ የዚሁ የክፍል ደረጃ ተማሪ - ሴክሽን ጥምርታ 1:40 (ገፅ 6) ነው፡፡ አሁን ምልከታ የተደረገባቸው የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ ግን 5.7 በ7.1 ማለትም 40.47 ካሬ ሲሆን፣ ተማሪ - ሴክሽን ጥምርታ ደግሞ በአማካይ (931÷20) 1:46 ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ የመማርያ ክፍሉቹ መጨናነቅ ይታይባቸዋል፡፡ መምህራን ተማሪዎችን ለመርዳት እንደልብ መዘዋወር አይችሉም፡፡ ለመናገር ክሂል አቀራረብ የተለያዩ የአቀማመጥ ዓይነቶችን ለመጠቀምም አያስችልም፡፡ ያለው አማራጭ ተማሪዎች በረድፍ እንደተቀመጡ በጥንድ /በሶስትዮሽ ማሰራት ወይም ደግሞ ፊትና ኃላ መቀመጫ ላይ ያሉ ተማሪዎችን በማዟደን ማሰራት ነው፡፡ ይህንን ደግሞ መምህራኑ ሲጠቀሙበት አልታየም፡፡

የመማሪያ ክፍሎች በሚመለከት ሌላው የታየው ችግር የመማሪያ ክፍሉቹ መስኮቶች በአንድ ጎን ብቻ መሆን የክፍሉ ብርሃናማነት በፀሐዩ አቅጣጫ መለዋወጥ ተፅዕኖ ስር እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ጧት ብርሃናማ የነበረ ክፍል ከስዓት በኂላ ጨለማ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በክፍሉ ብርሃን ማጣት ምክንያት የቪዲዮ ቀረፃ ማካሄድ ባለመቻሉ በሁለት ትምህርት ቤቶች የክፍል ለውጥ ለማድረግ ሁኔታው አስገድዷል፡፡

**አስራ አራት ፡-በመናገር ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተከሰቱ ችግሮችን በሚመለከት ፣**

**የተማሪዎች ምላሽ**

| ተ.ቁ | ጥ ያ ቄ | መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | የለም | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 12 | የመናገር ክሂልህን/ሽን ለማሳደግ በ7ኛ ክፍል በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ወዘተ በመሆን ሪፖርት ፣ ጭውውት ፣ ክርክር ፣ ውይይት ፣ ወዘተ አቅርበህ/ሽታውቀለህ/ቂያለሽ | 99 | 45 | 121 | 55 |

የዚህ መጠይቅ አላማ በክፍል ውስጥ በሚቀርቡ ሪፖርቶች፣ ክርክሮች ጭውውቶች፣ ውይይቶች ምን ያህል ተማሪዎች የመሳተፍ እድል አግኝተዋል? ምን ያህሉስ አላገኙም? የሚለውን ለማወቅና ዕድሉን ያላገኙት ተማሪዎች በምን ምክንያት እንዳልተሳተፉ ለማወቅ ነው፡፡ ከላይ ከሰንጠረዡ እንደሚታየው መጠየቁን ከሞሉት 220 ተማሪዎች ውስጥ 99(45%) የሚሆኑት ተማሪዎች ጭውውት ፣ ክርክር ፣ ውይይት ወዘተ የማቅረብ እድል

ያገኙ ሲሆን፣ 121(55%) የሚሆኑት ግን እድሉን አላገኙም። ይህ መረጃ በሰንጠረዥ ዘጠኝ (ገጽ-57) ከቀረበው መረጃ ጋር ሲተያይ በተወሰነ መልኩ ልዩነት ይታይበታል። ምክንያቱም ከሰንጠረዡ እንደሚታየው 134(60.9%) የሚሆኑት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሪፖርት ፣ ክርክር፣ጭውውት፣ ውይይት በማቅረባችን የመናገር ክሂል ችሎታችን አድጓል የሚል መልስ የሰጡ ሲሆን ፣ በሰንጠረዥ አስራ አራት ከቀረበው መረጃ ግን ሪፖርት ፣ ክርክር፣ ጭውውት፣ውይይት አቅረበናል በማለት የመለሱት 99(45%) የሚሆኑት ተማሪዎች ብቻ ናቸው። ለመናገር ክሂል ከተመደበው ክፍለ ጊዜ ማነስ አኳያ ግን በርካታ ተማሪዎች (60.9%) በአፍልቆት ደረጃ ሪፖርት ፣ክርክር፣ ጭውውት፣ ውይይት የሚያቀርቡበት እድል ሊያገኙ አይችሉም። በአፍልቆት ደረጃ የክፍል ውስጥ ምልከታው ከነውን ውጤት የሚያሳየውም 50% አካባቢ ነው። ስለሆነም በሰንጠረዥ ዘጠኝ መልስ የሰጡት ተማሪዎች በልምምድ ደረጃ ወደ አፍልቆት ከመሸጋገራቸውም በፊት የሚያደርጓቸውን ክንውኖች ግምት ውስጥ በማስገባት እንጂ የአፍልቆት ደረጃን ብቻ በማሰብ የመለሱ አይመስልም። ስለዚህ በሰንጠረዥ ዘጠኝ ከቀረበው መረጃ ይልቅ በሰንጠረዥ አስራ አራት የቀረበው መረጃ የተሻለ አሳማኝነት አለው ብሎ አጥኚው ያምናል።

**ሰንጠረዥ አስራ አምስት ፦ ተማሪዎች በመናገር ክሂል ተግባራት ያልተሳተፉበትን ምክንያት**

**የሚያሳይ መግለጫ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | መ ል ሶ ች | | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕድሉን አግኝቼ ስለማሳውቅ | | ንግግሬ የሌሎችን ስሜት አይስብም በሚል እምነት ትችት ስለምፈራ | | በተሰጠው ርዕስ ዙሪያ በቂ መረጃ ስለሌለኝ ባለመሳተፌ | | መምህሬ በማበረታታት ፈንታ ሞራሌን ስለሚነኩኝ | | |
| | | በቁ ጥር | % | በቁጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁጥር | % | |
| 13 | በተራ ቁጥር 12 ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ "የለም" ከሆነ ምክንያትህ/ሽ ምንድነው | 55 | 45.5 | 39 | 32.2 | 27 | 22.3 | - | - | 121 |

ቀደም ሲል እንደተጠቀው ለመናገር ክሂል የተሰጠው የክፍል ጊዜ መጠን 7 ብቻ ነው ። ለክሂሉ ከተሰጠው የክፍለ ጊዜ መጠን አኳያ የክፍሉ ተማሪዎች በጥንድ /በቡድን

በመሆን ተግባራቱን ከተለማመዱ በኋላ በቡድን ተወካዮች አማካይነት የተወያዩበትን ሪፖርት እንዲያደርጉ፣ ክርክር እንዲያቀርቡ ከማድረግ ውጪ ሁሉም ተማሪ ሪፖርትና ክርክር የማቅረብ ዕድል በግል እንዲያገኝ ማድረግ አይቻልም። ስለሆነም ክርክር፣ ጭውውት ወዘተ የማቅረብ ዕድል አላገኘንም ካሉት 121 ተማሪዎች ውስጥ 55 (45.5%) የሚሆኑት ተማሪዎች በክፍለ ጊዜው ማነስ ምክንያት የመሳተፍ እድሉን ላያገኙ ይችላሉ። ስለዚህ መምህራን እንዲህ ዓይነቱን ችግር ለመፍታት በአንድ ጊዜ በርካታ ተማሪዎችን ሊያሳተፉ የሚችሉ ተግባራትን ለምሳሌ ውይይት ፡ ጭውውት፣ቃለ መጠይቅ መደራረግ ወዘተ የመሳሰሉትን ተግባራት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲየከናውኑ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ 39 (32.2%) ያህሉ ደግሞ በፍርሃት ምክንያት መሳተፍ ያልቻሉ ናቸው። Ur (1996:21) እንደገለፁት መታቀብ በመናገር ክሂል አቀራረብ ሊያጋጥም የሚችል ሌላው ችግር ነው። ስለሆነም መምህራን ችግሩን ለመቅረፍ የቡድን ስራ በመጠቀም ፍርሃት ያለባቸው ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማበረታታት፣ የራሳቸውን የቃላትና የአገላለፅ ችሎታ ተጠቅመው እንዲናገሩ መገፋፋት ይጠበቅባቸዋል።

ከላይ ከቀረቡት ችግሮች በተጨማሪ በተማሪዎች የተጠሰው ሌላው ችግር ለክርክር፣ ለጭውውት ፣ ለውይይት በቀረበው ርዕስ ዙሪያ በቂ መረጃ ማጣት ሲሆን ፣ በዚህ ችግር ምክንያት መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ 27(22.3%) የሚሆኑት ተሳትፎ እንደማያደርጉ ገልፀዋል። ስለዚህ ችግሩን ለመፍታት ለመናገር ክሂል መለማመጃ የሚቀርቡ ተግባራት የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ ፣ ፍላጐት ያገናዘቡና ሳቢነት ያላቸው መሆን ስላለባቸው ፣በመፅሐፉ የቀረቡት ተግባራት ይህንን መስፈርት የማያሟሉ ከሆነ ተማሪዎች ሌሎች ርዕሶችን እንዲመርጡ ዕድል መስጠት ከመምህራን ይጠበቃል።

በመጨረሻም መጠይቁን ከሞሉ ተማሪዎች ውስጥ መምህሬ ሞራሌን ስለሚነኩኝ በክፍል ውስጥ በሚቀርቡ ክርክሮች ፣ ጭውውቶች ፣ ውይይቶች ወዘተ አልሳተፍም ያለ አንድም ተማሪ የለም ። መምህራን የተማሪዎቻቸውን ሞራል መጠበቃቸው አንድ በጎ ርምጃ ሲሆን ተማሪዎች ሌሎች ችግሮቻቸውን ተቋቁመው ሳይሸማቀቁ ሀሳባቸውን በተዝናና ሁኔታ እንዲገልፁ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

Ur (1996:133) "ንግግርን ከመፈተን ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮች አሉ። ከችግሮቹም ውስጥ አዘገጃጀቱ ፣ አፈታተኑ/ አመዛዘኑ የሚጠቅሱ ናቸው። ችግሮቹ ስር የሰደዱ ሲሆኑ በአብዛኛዎቹ የቋንቋ ፈተናዎች ንግግርን መፈተን አይካተትም ፤ ቢካተትም የሚሰጠው ዋጋ ዝቅተኛ ነው" ይላሉ ። ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት የሰባተኛ ክፍል

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂልን የሚፈትኑ ወይም የማይፈትኑ መሆኑን ለማረጋገጥና የማይፈትኑ ከሆነ ችግሮቹን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ለመስጠት ፣ የሚፈትኑ ከሆነ ደግሞ ልምዱን ለሌሎች መምህራን ለማስፋት ቃለ - መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡

ለመምህራኑ የቀረበው የመጀመሪያው ጥያቄ " የመናገር ክሂልን እንደመፃፍ ፣ ማንበብ ፣ ማዳመጥ ክሂሎች ፈትነው ያውቃሉ? " የሚል ነበር ፡፡ ለቃለ - መጠይቅ ከቀረቡት ሶስት መምህራን ውስጥ ሁለቱ የመናገር ክሂልን ፈትነው እንደማያውቁ የመለሱ ሲሆን የማይፈትኑበትን ምክንያት እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

- በአንድ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች መብዛት
- የሳምንት የክፍለ - ጊዜ ጫና (24 ክፍለ ጊዜ) ከፍተኛ መሆን
- ግልፅ የሆነ የመገምገሚያ መስፈርት አለመኖርና በአፈታተኑ ዙሪያ ግንዛቤ አለመኖር

ለቃለ - መጠይቅ ከቀረቡት መምህራን አንዱ ግን ከተማሪዎች ብዛትና ከክፍለ ጊዜ ጫና ከፍተኛ መሆን ጋር ተያይዞ ፈተናውን ለመተግበር አስቸጋሪ ቢሆንም ተማሪዎች ከፈረቃ ውጪ በሚሰጣቸው ርዕስ ዙሪያ ተዘጋጅተው እንዲመጡ በማድረግ የመናገር ክሂል ችሎታቸውን እንደሚመዝን ተናግሯል፡፡

ለማጠቃለል የመናገር ክሂልን መፈተንን አስፈላጊነት ደግፈው የሚከራከሩ ወገኖች እንዳሉ ሁሉ ክሂሉን ለመፈተን አስቸጋሪ ሁኔታዎች (ለምሳሌ ብዙ ጊዜና ገንዘብ የሚጠይቅ መሆኑ ፣ አፈታተኑ ተጨባጭነትና አስተማማኝነት የሌለው መሆኑ ፣ ክሂሉን ለመፈተን ግልፅ የሆነ መስፈርት አለመኖሩ ወዘተ..) በመኖራቸው ምክንያት በተቃራኒ ጎራ ቆመው የሚከራከሩ አልጠፉም Ur (1996፡134)፡፡ የሆነ ሆኖ ግን ችግሮችን ተቋቁሞ የመናገር ክሂልን መፈተን ከተቻለ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሻሻል እንደሚረዳ ጥርጥር የለውም፡፡ ስለዚህ መምህራን ጉዳዩን በውል ሊያጤኑት ይገባል፡፡

ሌላው ለመምህራን የቀረበላቸው ጥያቄ በመናገር ክሂል አቀራረብ "ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር እንዳይገልፁ የሚያደርጉ ችግሮች ምን ምን ናቸው?" የሚል ነበር ፡፡ መምህራኑ ችግር ብለው የጠቀሷቸው ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ስለሆነ አውቀዋለሁ በሚል እምነት ትኩረት አለመስጠት፣
- የማንበብ ባህል ባለመዳበሩ ለሚናገሩት ነገር መረጃ ማጣት፣
- በንግግሬ መጥፎ ግምት ይወሰድብኛ ይሆን በሚል እምነት ራስን ማግለል፣

- በተወሰኑ ተማሪዎች የፍርሃት ስሜት መኖር፣
- ከተማሪዎች ብዛት አኳያ የተደበቁ ተማሪዎችን አነሳስቶ አለማሳተፍና አምባይ ተማሪዎችን ብቻ ይዞ መጓዝ፣
- ደከም ያሉት ተማሪዎችን ለማገዝ ከፊረቃ ውጪ ሲጠሩ ደካማ እንባላለን በሚል እምነት አለመምጣት፣

በመምህራኑ የተጠቀሱት ችግሮች Ur (1996፡121) በመናገር ክሂል አቀራረብ ጊዜ ከተማሪዎች ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ብለው ከጠቀሷቸው ጋር የሚቀራረቡ ሲሆን ፣ ለእነዚህ ችግሮች መፍትሄ ይሆናሉ ብለው መምህራን ያቀረቧቸውን ነጥቦችም ፦

- የንባብ ዝንባሌ እንዲኖራቸው ማበረታታት፣
- የመምህራንን የትምህርት አቀራረብ አሳታፊ ማድረግ፣
- ርዕሱ የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ያገናዘበና ሳቢነት ያለው እንዲሆን ማድረግ፣
- የጥንድ / የቡድን ስራን ማበረታታት፣
- ለሚፈሩ ተማሪዎች ተደጋጋሚ ዕድል መስጠት የሚሉ ነበሩ፡፡

በመናገር ክሂል አቀራረብ የተከሰቱ ችግሮችን ለማጠቃለል መምህራን መሠረታዊ የመናገር ክሂል አቀራረብ ቅደም ተከተልን በሚመለከት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን ፣ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት ተግባራት የሁሉንም ተማሪ ተሳትፎ ያማከለ እንዲሆን የመምህራን ክትትል ማነስ ፣ የመናገር ክሂልን ለመፈተን ከተማሪዎች ብዛትና ከስራ ጫና በተጨማሪ አፈታተኑን በሚመለከት መምህራን ግልፅ የሆነ ግንዛቤ የሌላቸው መሆን በመምህራን በኩል የታዩ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡ ተማሪዎችን በሚመለከት ደግሞ በክፍል ውስጥ በሚቀርቡ የለያዩ ተግባራት ለመሳተፍ ተነሳሽነት ማጣትና በፍርሃት ምክንያት የተማሪዎች ተሳትፎ ማነስ ፣ የክርክር ፣ የውይይት ወዘተ ስርዓቶችን ጠንቅቆ አለማመቅ፣ በቂ ዝግጅትና ልምምድ አድርጎ ሀሳብን በተሳካ ሁኔታ ለመግለፅ አለመጣር የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው፡፡ የክፍል ጥበት የመናገር ክሂልን በጥንድ /በቡድን አደራጅቶ ለማስተግበር አለመቻልም ሌላው ተያያዥ ተጠቃሽ ችግር ነው ፡፡ ከላይ የቀረቡትን ችግሮች ለመፍታት ደግሞ የመምህራን የመናገር ክሂል አሳታፊ ማድረግ ፣ የሚፈሩ ተማሪዎችን በቡድን ስራ እንዲሳተፉ ማድረግና የመከራከሪያ ፣ የመወያያ ወዘተ ርዕሶች ሳቢነት እንዲኖራቸው ማድረግ የሚል መፍትሄ ከራሳቸው ከመምህራን እንደቀረበ ለማየት ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው ጥናቱን ለማጥናት መነሻ ሀሳብ የሆነው ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ ለማንበብና ለመፃፍ ክሂሎች የተሰጠውን ያህል ለመናገር ክሂል የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን Sesnan (1997) ፣ McDonough እና Shaw (1995) መግለፃቸው ፣ የመናገር ክሂል፣ ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ተቀባይነት እያገኘ መምጣት ጋር ተያይዞ እንደአንድ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ቢካተትም የክሂሉን አቀራረብ በሚመለከት ችግር መኖሩን Scrivener (1994)፣Ur(1996) መጠቆማቸው ፣ በአገራችንም የተካሄደ የጥናት ውጤት መምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን ታደሰ (1997) ማመልከቱ ነው፡፡ ስለሆነም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ምን ምን መልመጃዎችን /ተግባራትን ይገለገላሉ? የተግባራቱን አቀራረብ በሚመለከት ግንዛቤው አላቸው ወይ? ግንዛቤው ካላቸው እንዴት እየሰሩ ነው? በስራቸው ምን ምን ችግሮች ያጋጥሟቸዋል? ችግሮቹንስ እንዴት ይፈቷቸዋል? የመምህር-ተማሪ ተራክቦ ውቅርስ ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ፈትሾ ምላሽ መስጠት የጥናቱ መነሻ ሀሳቦች ናቸው ፡፡

ስለዚህ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ከምልከታና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በአሀዝና በመቶኛ ተሰልተው እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን እንድምታቸው ተብራርቷል፤ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘው ምላሽም በገለጻ መልክ ቀርቧል፡፡ ስለሆነም ከሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በተገኘው መረጃ መሰረት የጥናቱ ውጤት በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ መምህራን የሚገለገሉባቸውን ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ ለማረጋገጥ የክፍል ውስጥ ምልከታና የመምህራን ቃለ-መጠይቅ ምላሽ እንዲሁም የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት መነሻ ተደርጓል፡፡ ከመሣሪያዎቹ በተገኘው መረጃ መሰረትም የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ በመለማመጃነት ክርክር ፣ ጭውውት፣ ውይይት ቀርበዋል፡፡ መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን የመናገር ክሂል የሚያሳድጉ መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ በተደረገው ፍተሻ ደግሞ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ ከግማሽ በላይ (72%) የሚሆኑት የቀረቡት የመናገር

ክሂል መልመጃዎች የመናገር ችሎታቸውን ለማሳደግ እንደረዷቸውም ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ውጪ የሆኑት ግን በጉዳዩ የማይስማሙና ለመወሰን የሚቸገሩ ናቸው፡፡ መምህራን በበኩላቸው የቀረቡትን ተግባራት ለማለማመድ የተመደው ጊዜ ማነሱን እንደክፍተት አንስተዋል፡፡ ሆኖም ግን የቀረቡት የመለማመጃ ተግባራት ከተማሪዎቹ ዕድሜና ዳራዊ ዕውቀት ብዙም ያልራቁ ስለሆኑ ፣ ከተማሪዎቹ የህይወት ልምድ ጋር የማይጣጣሙ ርዕሶች ሲያጋጥሙም ተማሪዎች ሌሎች ርዕሶችን የመምረጥ ዕድል ስላላቸው ፣ ለመለማመጃነት የቀረቡት ተግባራት የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የማሳደግ አቅም እንዳላቸው መምህራን አረጋግጠዋል፡፡ ሌላው ከመልመጃዎች ጋር ተያያዞ የተነሳው ጉዳይ መምህራን የሚጠቀሙበትን የማስተማሪያ ዘዴ ማወቅ ሲሆን ፣ መምህራን ክሂሉን ለማቅረብ የቡድን ስራ እንደሚገለገሉ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን መምህራን ከቡድን ስራ በተጨማሪ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎች (የግል ፣ የጥንድ ፣ ክፍሉ አንድ ላይ በመሆን) መኖራቸውንና የተጠቀሱት የማስተማሪያ ዘዴዎች ምን ዓይነት ተግባራትን ለማለማመድ እንደሚረዱ የመለየትና የመተግበር ችግር እንዳለባቸው ከክፍል ውስጥ ምልከታና መምህራኑ ራሳቸው ከሰጡት ቃለ- ምልልስ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ 43% የሚሆኑትም ይህንን ሀሳብ ተጋርተዋል፡፡

ሌላው በጥናቱ የታየው ጉዳይ የመምህር - ተማሪ ተራክቦ ወቅር ሲሆን በመርህ ደረጃ የተማሪዎች የእርስ በርስ መስተጋብር ከመምህራን የንግግር ጊዜ ጎልቶ መታየት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አኳያ በመናገር ክሂል አቀራረብ ጎልቶ የታየው የመምህራን የንግግር ጊዜ ወይስ የተማሪዎች የእርስበርስ ተራክቦ ? የሚለውን ለማየት ተሞክሯል፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታው መረጃ እንዳመለከተው ከስድስት ምልከታዎች ውስጥ ሁለቱ ሙሉ በሙሉ ፣ ሁለቱ ደግሞ ከሞላ ጎደል መምህር - መራሽ አቀራረብ ስለነበሩ የመምህሩ የንግግር ጊዜ ጎልቶ መታየቱን ፣ በቪዲዮ ቀረፃ የተደገፉት ሶስት ምልከታዎች በአንፃራዊነት የተማሪዎች ተራክቦ የተሻለ ሆኖ መገኘቱን አመልክተዋል፡፡ ከተማሪዎች የዕሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ሲታይ ደግሞ የመናገር ክሂል አቀራረብ በመምህሩና በተማሪዎች አቻዊ መስተጋብር እንደሚሸፈን አመልክቷል፡፡ ከምልከታና ከተማሪዎች የዕሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ውጤት በጥቅሉ ሲታይ በመናገር ክሂል አቀራረብ የተማሪዎች የርስበርስ ተራክቦ ጉልህ የሆነ ድርሻ እንደሌለው የሚያረጋግጥ ነው፡፡

መምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት ግንዛቤው ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ሶስተኛው የጥናቱ የትኩረት ነጥብ ሲሆን፣ ሁለት መምህራን ከተመረቁበት የትምህርት ተቋምም ሆነ በስራ ላይ እያሉ የመናገር ክሂል አቀራረብን

በሚመለከት ምንም ዓይነት ሥልጠና አለመውሰዳቸውን ፣ አንድ መምህር ግን ከተማረበት የትምህርት ተቋም ክሂሎችን እንዴት ማስተማር እንደሚችል ኮርስ መውሰዱን ከቃለ-ምልልሱ ማወቅ ተችሏል። ሁሉም መምህራን ግን በተለያዩ የመናገር ክሂል የአቀራረብ ደረጃዎች የመረጃ አቀባይነትን ፣ የመምራትንና የመደገፍን ፣ የተማሪዎችን ርምጃ የመከታተልን ፣ የተማሪዎችን ስራ ለማሻሻልና በራስ የመተማመንን ስሜት ለመፍጠር የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሚናን መቼ ማከናወን እንዳለባቸው የግንዛቤ እጥረት እንደታየባቸው የክፍል ውስጥ ምልከታው ውጤት አረጋግጧል።

በመናገር ክሂል አቀራረብ የመምህራን ዋና ተግባር የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ለማሳደግ በክፍል ውስጥ ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ እየሰጡ መሄድ ነው ። ከዚህ አኳያ በመናገር ክሂል አቀራረብ መምህራን ምን ምን ችግሮች እንዳጋጠማቸው ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ሲሆን በመምህራን በኩል ለመናገር ክሂል የተሰጠውን ጊዜ በተማሪዎች እንዲሸፈን አለማድረግ ፣ አማካዩን ተማሪ ብቻ ይዞ መጓዝና የተደበቁ ተማሪዎችን ለማሳተፍ ጥረት አለማድረግ ፣ መምህራን በተግባቦታዊ ሂደቱ የማመቻቸት ፣ የመከታተልና የማማከርን ሚና አለመገንዘብና አለመተግበር የታዩ ችግሮች ናቸው። በተማሪዎች በኩል ደግሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ስለሆነ አውቀዋለሁ በሚል እምነት ለመናገር ክሂል ትኩረት አለመስጠት ፣ የንባብ ባህል አለመዳበር ፣ በንግግሬ መጥፎ ግምት ይወሰድብኛል ይሆን በሚል እምነት በክፍል ውስጥ በሚደረጉ የመናገር ክሂል ተግባራት ከመሳተፍ  መታቀብ እንደችግር ተጠቅሰዋል። የመማሪያ ክፍሎች ግንባታና የተማሪ - ሴክሽን ጥምርታ በክልሉ ትምህርት ቢሮ ስታንዳርድ መሰረት አለመሆን በተያያዥ የታዩ ዋና ዋና ችግሮች ሲሆኑ፣ የአብኛዎቹ  ችግሮች መንስኤ ግን መምህራን በተማሩበት የትምህርት ተቋምም ሆነ በስራ ላይ እያሉ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የሙያ ማሻሻያ ስልጠና አለማግኘታቸው ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

በአጠቃላይ በጥናቱ ውጤት መሠረት የሚከተሉት ግንዛቤዎች ተገኝተዋል።

- በመማሪያ መጽሐፉ የተካተቱ የመናገር ክሂል  ተግባራት /መልመጃዎች በዓይነት የተለያዩ አለመሆን እና መልመጃዎቹን ለመተግበር የተመደበው ጊዜ ማነስ እንደክፍተት ቢጠቀስም መልመጃዎቹ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማዳበር ብቃት ያላቸው መሆኑ፣

- የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ከቡድን ውይይት በተጨማሪ የግል ፣ የጥንድ ወዘተ የማቅረቢያ ዘዴዎች መኖራቸውን መምህራን ተገንዝበው መተግበር አለመቻላቸው፣
- የመምህር - ተማሪ ተራክቦ እኩል /እቻ እንደሆነና የተማሪዎች የእርስበርስ ተራክቦ በመናገር ክሂል አቀራረብ ጉልህ ድርሻ የሌለው መሆኑ፣
- የመናገር ክሂል አቀራረብ ደረጃዎችን ተከትሎ የማቅረብ እና በእያንዳንዱ ደረጃ ምን እንደሚከናወን ያለመረዳት ችግር በተወሰነ ደረጃ በመምህራን መታየቱ፣
- የመምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ሁሉንም ተማሪ አሳታፊ አለመሆንና ተማሪዎች በምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ጉልህ ተሳትፎ እንዲኖራቸው አለማድረግ፣
- የተማሪዎች ብዛት ከሚፈጥረው የስራ ጫና በተጨማሪ መምህራን የመናገር ክሂልን መመዘን / መፈተን የሚያስችል ግልፅ የሆነ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑ፣
- የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ስለሆነ አውቀዋለሁ በሚል እምነት ለመናገር ክሂል ትኩረት አለመስጠት በተወሰኑ ተማሪዎች መታየቱ፣
- የተማሪዎች የንባብ ባህል ባለመዳበሩ ምክንያት ተማሪዎች በሚከራከሩበት፣ በሚወያዩበት ወዘተ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ በቂ ሀሳብ የማፍለቅና የማደራጀት ችግር ቢታይም የተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር የመግለፅ ችሎታ አበረታች መሆኑ፣
- የተማሪ - ሴክሽን ጥምርታ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ባወጣው ስታንዳርድ መሠረት አለመሆን ለመናገር ክሂል አቀራረብ አመቺ አለመሆን ናቸው።

## 5.2 አስተያየት

ለጥናቱ መነሻ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የታዩ ችግሮች ለወደፊት ይፈቱ ዘንድ መፍትሄ መጠቆም ነው ። ስለሆነም ጥናቱ ያነሳቸውን ጥያቄዎች ግኝቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል።

- የመናገር ክሂልን ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራት /መልመጃዎች የተማሪዎችን ዕድሜ ፣ ፆታ ፣ የዕውቀት ደረጃ ፣ የመጡበትን አካባቢ ወዘተ የአገናዘቡ እንዲሆኑ በመጻህፍት ዝግጅት ወቅት የፍላጐት አሰሳ ማድረግ ትኩረት ቢሰጠው፣
- መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የተማሪዎቻቸውን የቀደመ-እውቀት መነሻ ቢያደርጉ፣
- የመናገር ክሂልን ለማሳደግ የቀረቡትን ተግባራት ለማለማመድ የሚሰጠው ጊዜ ከመልመጃዎቹ ስፋት ጋር እየታየ ቢሆን፣

- ከክርክር ፣ ከጭውውት ፣ ከውይይት በተጨማሪ የግልና የጥንድ ስራን የሚያበረታቱ እንደ ታሪክ መናገር ፣ የዱብ ዕዳ ንግግር ፣ ቃለ-መጠይቅ መደራረግ የመሳሰሉ ተግባራት በቀጣዩ ዝግጅት እንዲካተቱ ትኩረት ቢደረግ፣
- የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ መምህራን ከተማሪዎች ህይወት ጋር የተያያዙና ሳቢነት ያላቸውን ርዕሶች ከተለያዩ ምንጮች (ጋዜጦች፣ መፃህፍት ወዘተ) ወደ ክፍል ለማምጣት ቢሞክሩ፣
- መምህራን ተማሪዎቻቸው ያሉባቸውን የንግግር ግብዓት ማጣት ችግር መቅረፍ ይችሉ ዘንድ ጋዜጦችን ፣ መጻህፍትን ወዘተ. እንዲያነቡ ቢያበረታቱ፣
- መምህራንን ከአዳዲስ ፅንሰ-ሀሳቦችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ለማስተዋወቅ የትምህርት ቢሮዎች ፣ የወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች ፣ ትምህርት ቤቶች ወዘተ... ስልጠናዎችን እንደአስፈላጊነቱ ቢያዘጋጁ፣
- የመማሪያ ክፍል መጨናነቅ በመናገር ክሂል አቀራረብ አሉታዊ ተፅዕኖ ስላለው፣ የተማሪ - ሴክሽን ጥምርታ እና የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ በክልሉ ትምህርት ቢሮ ስታንዳርድ መሰረት እንዲሆን የየወረዳው አስተዳደር እና የየወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች፣ የአካባቢው ህብረተሰብ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትኩረት ቢሰጡት የሚሉ ናቸው።

# <u>ዋቢ ፅሁፎች</u>


መንግስቱ ታደሰ:: (1997):: "በአዲስ አበባ መስተዳድር የ9ኛ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ አተገባበር ግምገማ":: የአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም::

ማረው አለሙ:: (1998):: *የአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ዘዴ::* አዲስ አበባ ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት:: ስ.ት.ዝ.ጥ.ም ኢንስቲትዩት::(1994):: *የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች ከ5ኛ - 8ኛ ክፍሎች ::* አዲስ አበባ ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ::

ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ:: (2007):: "የአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ዘዴ I" :: አዲስ አበባ ፣ ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ::

ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ :: (2006):: "መሠረታዊ አማርኛ I" :: አዲስ አበባ፣ ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ::

ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ :: (2006):: "በስነጽሁፍ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር":: አዲስ አበባ፣ ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ::

አብክመ ትምህርት ቢሮ:: (1997):: *ሰባተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ::* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት::

አበክመ ትምህርት ቢሮ:: (1997):: *ሰባተኛ ክፍል አማርኛ የመምህሩ መምሪያ::* አዲስ አበባ ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ::

አብክመ ትምህርት ቢሮ :: (2002 ዓ.ም ፣ ጥቅምት):: የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መለኪያ :: ስታንዳርድ ቁጥር ሁለት ፣ ገፅ 6-8፣22::

ያለው እንዳወቀ:: (2001):: *የምርምር መሠረታዊ መርሆዎች አተገባበር::* ሁለተኛ እትም:: ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

Bailey, K.M. (2006). Issues in Teaching Speaking Skills to Adult ESOL Learners. Retrieved Sept. 12, 2010. From Addis Ababa University web site: WWW. ncsall. net / index. Php? Id = 64-cached. Partners in Teaching.

Best, J.W.and James, V.K. (2006). *Research in Education.* Pearson: prentice Hall.

Bygate, M. (1987). *Speaking.* Oxford: OUP.

Byrne, D.(1976). *Teaching Oral English.* London: Longman.

Cunningsworth A. (1995). *Choosing your Course book* Oxford: Heinemann.

Dinzil, M. et al. (1987). *Manual of 1987 Confrence Materials.* Toronto: Humber College.

Dornyei, Z. (2007) *Research Methods in Applied Linguistics: Quantitative, Qualitative and Mixed Methodologies.* Oxford. OUP.

Gower, R., Phillips, D., and Walters, S. (1995). *Teaching Practice Handbok.* Oxford. Heinemann.

Harmer,J.(1991). *The practice of English Language.* London: Longman Group UK Limited.

Harmer,J. (2007). *How to Teach English.* London: Longman.

Lee, W.R. (1979). *Language Teaching Games and Contents.* Hong Hong: OUP.

McDonough, J. and Shaw, C. (1995). *Materials and Methods in ELT: A Teacher's Guide.* Oxford: Blackwell Publishers Ltd.

Nunan, D. (1991). *Designing Tasks for the Communicative Classroom.* Cambridge: CUP.

Richards, J.C. and Nunan, D. (Eds.). (1990). *Second Language Teacher Education.* Combridge: CUP.

Scrivener,J. (1994). *Learning Teaching.* Oxford: Heinemann.

Sesnan, B. (1997). *How to Teach English.* Oxford: CUP.

Ur,P. (1981) . Discussions that Work: Task - centred fluency Practice. Cambrodge:CUP.

Ur, P. (1996). *A course in Language Teaching. Practrice and Theory.* Cambridge: CUP.

Wajnryb, R. (1992). *Classroom Observation Tasks: A resource books for language teachers and trainess.* Cambridge: CUP.

# አባሪ

## አባሪ አንድ

የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚያቀርቡ ለመፈተሽ የተዘጋጀ የምልከታ መከታተያ ቅፅ (Cheek List)

ምልከታ የተደረገበት ትምህርት ቤት ________________

ምልከታ የተደረገበት ቀን ________________

ምልከታው የተጀመረበት ሰዓት ________ ያለቀበት ________

በምልከታው ወቅት ይሰጥ የነበረው የትምህርት ርዕስ ________________

ይህ የመከታተያ ቅፅ የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል ተግባራትን የክፍል ውስጥ አቀራረብ በሰባተኛ ክፍል ለመከታተል ታስቦ የተዘጋጀ ነው ። በክፍል ውስጥ ምልከታው ወቅት ተግባራቱ ተከናውነው ከሆነ / ✓ / ምልክት " አዎ " ከሚለው ላይ ይደረጋል ። ተግባራቱ ያልተከናወኑ ከሆኑ ደግሞ / X / ምልክት " የለም " ከሚለው ላይ ይመለከታል።

1. የመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ ክንውን

| 1.1 የአቀራረብ ደረጃ / presentation phase / ክንውኖች | አዎ | የለም |
|---|---|---|
| 1.1.1 መምህሩ/ሯ የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ማለማመድ የሚያስችል አቀማመጥ ተጠቅሟል/ማለች?<br>• የፈረስ ኮቴ (horse shoe)<br>• ገጽ ለገጽ (face to face)<br>• ክብ (circle)<br>• ሌላ--------------------------------------------------- | | |
| 1.1.2 መምህሩ/ሯ የእለቱን የመናገር ክሂል ተግባራትን ዓላማ አስተዋውቋል/ቃለች ? | | |
| 1.1.3 መነቃቃትን ለመፍጠር መምህሩ/ሯ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል/ማለች?<br>• ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች መጠየቅ<br>• የበፊት ልምዳቸውን ከርዕሱ ጋር አያይዞ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች ስለሚማሩት ጉዳይ እንዲገምቱ ማድረግ<br>• ሌላ --------------------------------------------------- | | |
| 1.1.4 መምህሩ/ሯ ተማሪዎች ስለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅ መመሪያ ሰጥቷል/ታለች? | | |

| | | |
|---|---|---|
| 1.2 የልምምድ ደረጃ / practice phase/ ክንውኖች | | |
| 1.2.1. መምህሩ/ሯ የመናገር ክሂልን ማለማመድ የሚያስችል ተግባራትን ተጠቅሟል/ማለች ?<br>• ክርክር<br>• ጭውውት<br>• ውይይት<br>• ሌላ------------------------------------------------------- | | |
| 1.2.2 ተማሪዎች የመናገር ክሂል ተግባራትን በመምህሩ/ሯ አመቻችነትና መሪነት አከናውነዋል ?<br>• በጥንድ<br>• በሶስትዮሽ<br>• በትንንሽ ቡድኖች<br>• ክፍሉ በአንድነት (whole class) በመሆን<br>• ሌላ------------------------------------------------------- | | |
| 1.2.3 መምህሩ/ሯ ሁሉም ተማሪዎች በልምምዱ እንዲሳተፉ ያደርጋል/ታደርጋለች? | | |
| 1.2.4 መምህሩ/ሯ ተማሪዎች እንዲናገሩ ለማድረግ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል /ማለች?<br>• በርዕሱ ዙሪያ ተጨማሪ መረጃ መስጠት<br>• ስነልቦናዊ ችግር (ለምሳሌ ፍርሃት) ያለባቸውን ተማሪዎች ማበረታታት<br>• ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲረዳዱ ማድረግ<br>• ሌላ------------------------------------------------------- | | |
| 1.3. በአፍልቆት ደረጃ /production stage/ ክንውኖች | | |
| 1.3.1. መምህሩ/ሯ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባር በተቻለ መጠን ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ፣<br>• ያማክራል?<br>• ይከታተላል ? | | |
| 1.3.2. ተማሪዎች ያለምንም ቁጥጥር እርስ በርሳቸው የሚነጋገሩበት ዕድል አግኝተዋል? | | |

| | | |
|---|---|---|
| • ጭውውት ያቀርባሉ ?<br>• በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ - ይወያያሉ?<br>- ይከራከራሉ?<br>• በጥንድ /በቡድን የሠሩትን ለክፍሉ ተማሪዎች ሪፖርት ያደርጋሉ?<br>• በቀረበው ሪፖርት ላይ አስተያየት ይሰጣሉ? | | |
| 1.3.3 መምህሩ/ሯ ተማሪዎች ንግግር ሲያደርጉ ጣልቃ አይገባም? | | |
| 1.4. የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ክንውኖች | | |
| 1.4.1. በመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ ወቅት ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ተሰጥቷል?<br>• ተማሪው ራሱ ስህተቱን እንዲያይና እንዲናገር በማድረግ<br>• ሌሎች ተማሪዎች የተማሪውን ስህተት እንዲያርሙ በማድረግ<br>• ተማሪዎች የሰሩትን ስህተት ራሱ መምህሩ በማረም<br>• ሌላ------------------------------------------------------------ | | |

## 2. የመምህር - ተማሪ ተራክቦ ውቅሮች (patterns)

ቅንፉ ውስጥ "✓ " በማድረግ ይመለከታል፡፡

**2.1. የመምህሩ የንግግር ጊዜ** (teacher talk time) **በጣም ጎልቶ የታየው**

( ) በአቀራረብ ደረጃ (-------- ደቂቃ)

( ) በልምምድ ደረጃ (-------- ደቂቃ)

( ) በአፍልቆት ደረጃ (-------- ደቂቃ)

( ) ምጋቤ ምላሽ (-------- ደቂቃ)

**2.2. በመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ውቅሮች አጠቃላይ ገጽታ**

( ) የመምህሩ ንግግር ከፍተኛ፣ ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ አድማጮች ናቸው፡፡

( ) የመምህሩና ተማሪዎች ተራክቦ ተመጣጣኝ ነው፡፡

( ) የተማሪዎች ተራክቦ ከፍተኛ፣ መምህሩ አብዛኛውን ጊዜ አድማጭ ነው፡፡

3. በመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብ የሚከሰቱ ችግሮች

3.1. መምህሩን በሚመለከት

---------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

3.2. ተማሪዎችን በሚመለከት

---------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

3.3 ሌሎች ተያያዥ ችግሮች

---------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ ሁለት

የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ክንውን የቪዲዮ ቀረፃ ምዝግብ / transcription /

❖ **ናሙና አንድ**

የትምህርት ቤቱ ስም ፡- አፄዘርዓያዕቆብ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት

ምልከታ የተደረገበት ቀን ፡- 09/03/2003

ምልከታ የተደረገበት ክፍል 7G

ምልከታው የተደረገበት ሰዓት 7፡10 - 7፡50

በምልከታው ወቅት ይሰጥ የነበረው ርዕስ ፡- ክርክር

መምህሩ ወደ ክፍል ሲገቡ ተማሪዎች ከመቀመጫቸው ተነስተው ተቀብሏቸው፡፡ መምህሩም ሰላምታ አቅርበው እንዲቀመጡ አደረጉ ፡፡ ከዚያም ለክርክሩ የተመረጡ ተማሪዎችን ወደ መድረኩ እንዲወጡ ካደረጉ በኋላ ተከራካሪ ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ለሶስት ደቂቃ ያህል በየቡድናቸው እንዲነጋገሩ አደረጉ ፡፡ ቀጥለውም ክርክሩን የሚዳኙ ሁለት ተማሪዎች አስመረጡ ፡፡ ዳኞችን ካስመረጡ በኋላ የተከራካሪ ተማሪዎችን ስም እና የመከራከሪያ ርዕሳቸውን ጥቁር ሠሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ አያይዘውም ዳኞች ክርክሩን የሚዳኙበትን መስፈርቶች በመጥቀስ የክርክሩን መሪ (አስተዋዋቂ) አስመረጡ፡፡ ተከራካሪዎች ወደ ክፍል ገብተው ቦታ ቦታቸውን እንደያዙም ለክርክሩ መሪ ቦታውን ለቀው መምህሩ ተቀመጡ፡፡

መምህሩ ከመቀመጣቸው በፊት በሰጡት መመሪያ መሰረት ከሁለቱ ዳኞች አንደኛው ከመጽሐፉ ላይ የክርክር መመሪያ አነበበ፡፡ መመሪያው ከተነበበ በኋላ የክርክሩ አስተዋዋቂ ለክርክሩ የቀረቡት ወገኖች የተራ በተራ አካሄድ ስልት **"ገበሬ መሆን ይሻላል ወይስ ነጋዴ"** በሚል ክርክራቸውን እንደሚያቀርቡ በመጥቀስ የሁለቱን ተከራካሪዎች ስምና የሚከራከሩበትን ርዕስ ለተማሪዎች አስተዋወቀች፡፡

አስተዋዋቂ፡- ለመምህራችን እንዲሁም ለእንግዶች በዛሬው እለት ሁለት ተከራካሪ ቡድኖች ለመከራከር ቀርበዋል፡፡ ተማሪ ቤዛዊት ፣ ሙሉጌታ ወርቁና ሙሉጌታ ሀብታሙ ነጋዴን በመደገፍ ለመከራከር የቀረቡ ሲሆን ፣ ስንታየሁ ፣ በረከትና ፋጡማ ደግሞ ገበሬን በመደገፍ ፣ ነጋዴን በመቃወም ለመከራከር ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያውን እድል **ገበሬን** ደግፈው ለሚከራከሩ ወገኖች ሰጥቻለሁ፡፡

ገበሬ1፡- ገበሬ የተለያዩ የሰብል ዓይነቶችን ያመርታል፡፡ ስለዚህ ገበሬ ባይኖር ነጋዴ የሚሸጠው ነገር አያገኝም ነበር፡፡ እናም ገበሬ ከነጋዴ ይሻላል፡፡

አስተዋዋቂ፡- አሁን ደግሞ ቤዛዊት **ነጋዴን** በመደገፍ ክርክሯን ታቀርባለች፡፡

ነጋዴ1፡- እድሉ ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ፡፡ ነጋዴ በየእለቱ የምንጠቀምባቸውን የተለያዩ ሸቀጦች ማለት ስኳር ፣ ቡና የመሳሰሉትን ከቦታ ወደ ቦታ በማዘዋወር ለህዝብ ያቀርባል፡፡ ገበሬ ያመረተውንም ገዝቶ ወደተለያዩ አካባቢዎች በመውሰድ ሸጣል፡፡ ስለዚህ ባንዱ አካባቢ የማይገኘውን ወደ ሌላ ቦታ በመውሰድ ሻጭና ሸማችን ያገናኛል፡፡ ለገበሬውም ቢሆን እንደማዳበሪያ ፣ ጸረ ተባይ መድሃኒቶች የመሳሰሉትን በማምጣት ገበሬው ምርታማ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በአጭሩ ነጋዴ ለገበሬው ተለያዩ የግብርና ግብአቶችን በማቅረብ ምርቱ እንዲያድግ ከመርዳቱም በላይ በአንድ አካባቢ የማይገኘውን ከሌላ አካባቢ በማምጣት ህብረተሰቡ በቀላሉ አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ነው፡፡ ስለሆነም ከገበሬ ነጋዴ መሆን ይሻላል፡፡

አስተዋዋቂ፡- ቀጥሎ ደግሞ በረከት **ገበሬን** በመደገፉ ነጋዴን በመቃወም ክርክሩን ያቀርባል፡፡

ገበሬ2፡- ነጋዴ የተለያዩ ምርቶችን ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላው በማዘዋወር የሚሸጠው ገበሬ ያመረተውን ነው፡፡ ስለዚህ ገበሬ ያላመረተውን ነጋዴ ሊሸጥ አይችልም፡፡ ገበሬ ግን ያመረተውን ወደተለያዩ አካባቢዎች በመውሰድ ራሱ ሊሸጥ ይችላል፡፡ ነጋዴ ግን የሚያመርት ሀይል ከሌለ የሚሸጠው ነገር አያገኝም፡፡ ስለዚህ ገበሬ ከነጋዴ የተሻለ ነው፡፡

አስተዋዋቂ፡- አሁን ደግሞ ሙሉጌታ ወርቁ **ነጋዴ** ይበልጣል እያለ ይከራከራል፡፡

ነጋዴ 2፡- ነጋዴ በጣም አስፈላጊ የሆኑ የፋብሪካ ውጤቶችን ማለትም የእርሻ መሣሪያዎች (ማረሻ ፣ ማጭድ፣ ዶማ) ለገበሬ ያቀርባል፡፡ ስለዚህ ነጋዴ እነዚህን መሣሪያዎች ለገበሬው ባያቀርብለት ማምረት አይችልም፡፡ ነጋዴ ገበሬው ስራ ፈትቶ የእርሻ መሣሪያዎችንና ሌሎች ሸቀጦችን ፍለጋ እንዳይንገላታ ይረዳዋል፡፡ ስለዚህ ያለነጋዴ እገዛ ገበሬ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ማምረት ስለማይችል ነጋዴ ለገበሬ አጋሩ ነው፡፡

አስተዋዋቂ፡- **ገበሬን** በመደገፍ የመጨረሻውን ክርክር ፋጡማ ታቀርባለች፡፡

ገበሬ3፡- ነጋዴ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችም ሆነ ለገበሬ የሚያቀርበው ራሱ ያመረተውን አይደለም፡፡ ገበሬ ግን ራሱ አምርቶ ራሱ ለገበያ ስለሚያቀርብ ከነጋዴ የተሻለ ነው፡፡

አስተዋዋቂ፡- **ከነጋዴ** ወገን የመጨረሻውን የመከራከሪያ ሀሳብ ሙሉጌታ ሀብታሙ ያቀርባል፡፡

ነጋዴ 3፡- ነጋዴ ለገበሬ የተለያዩ ማቴሪያሎችን ያቀርባል። ስለዚህ ነጋዴ ለገበሬ ድጋፍ የሚሰጥ ነው።

አስተዋዋቂ፡- ሁለቱ ተከራካሪ ቡድኖች ክርክራቸውን ጨርሰዋል። ውጤት ከዳኞች እስከሚደርስ አስተያየት ካለ....

አስተያየት ሰጪ1፡- ተከራካሪዎች ራሳቸውን ለተመልካች ያለማስተዋወቅና ያለማመስገን ችግር እና የፍርሀት ስሜት ታይቶባቸዋል። ስለዚህ እነዚህን ችግሮች እንዳይደገሙ ለወደፊቱ ማስተካከል ይኖርባቸዋል።

አስተያየት ሰጪ 2፡- ሀሳብን ሳይቋጩ የመቀመጥ ችግር ታይቷል። ስለዚህ ችግሩን ለመፍታት በቂ ልምምድና ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

ዳኛ፡- ክርክሩ ከፍተኛ ፉክክር የታየበት ነው። (ዝርዝር ነጥቡ በዳኛው ተገልጿል።) ስለሆነም በተደረገው ክርክር ነጋዴ አሸናፊ ሆኗል።

ዳኞች አሸናፊውን ገልፀው እንደተቀመጡ መምህሩ ለክርክሩ ዝግጅት ከተሰጠው ጊዜ አኳያ ክርክሩ የተጠበቀውን ያህል የተጋጋለ ባይሆንም " ለማመስገንም ሆነ ለመተቸት ምክንያት በመሆንናችሁ አመሰግናለሁ" በማለት ተከራካሪዎችን ፣ ቀጥለውም አስተያየት በመስጠት የተሳተፉ ተማሪዎችን አበረታትተዋል። በመጨረሻም መምህሩ ዳኞች ጭማቂውን ውጤት እንጂ ዝርዝሩን መግለፅ እንደሌለባቸው በማሳሰብ የክርክሩ ሂደት በ20 ደቂቃ ተቋጭቷል።

❖ ናሙና ሁለት

የትምህርት ቤቱ ስም ፡- ብሩህ ተስፋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት

ምልከታ የተደረገበት ቀን ፡- 16/03/2003

ምልከታ የተደረገበት ክፍል ፡- 7H

ምልከታው የተደረገበት ሰዓት ፡- 10፡05 - 10፡45

በምልከታው ወቅት ይሰጥ የነበረው ርዕስ ፡- ውይይት

መምህሯ ወደ ክፍል ሲገቡ ተማሪዎች ከመቀመጫቸው ተነስተው ተቀበሏቸው ። መምህሯም ተማሪዎች እንዲቀመጡ ካደረጉ በኋላ ቀኑንና የትምህርት ዓይነቱን ጥቁር ሠሌዳ ላይ ፃፉ። በመቀጠልም የዕለቱ ትምህርት ውይይት መሆኑን ጠቅሰው በመንደርደሪያነት አራት የቋንቋ ክሂሎች እንዳሉ በማስታወስ ምን ምን እንደሆኑ ተማሪዎችን ጠየቁ። አንዲት ሴት ተማሪ መልስ እንደሰጠች መምህሯ አበረታትተዋት ተቀመጠች። ከዚያም መምህሯ ንግግር ከአራቱ ክሂሎች አንዱ እንደሆነ በመጥቀስ

የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማሳደግ ከሚረዱ ተግባራት አንዱ ውይይት መሆኑን በመጥቀስ **"የወጣትነት ጊዜያችንን እንዴት እናሳልፍ"** በሚል ርዕስ ተማሪዎች እንደሚወያዩ ገለፁ ። አያይዘውም በውይይቱ የሚነሱ ጠቃሚ ነጥቦችን በመጠቆም የውይይቱን መሪና ቃለ - ጎባኤ ያዥ ወንድና ሴት ተማሪዎች አስተዋውቀው መድረኩን ለውይይቱ መሪዎች ለቀቁ።

መምህሯ መድረኩን እንደለቀቁ አወያዩቹ ቦታቸውን ያዙ ። ከዚያም የውይይቱ መሪ የመወያያ ርዕሱን በድጋሚ በማስታወስ "የወጣትነት ዕድሜ የትኛውን የዕድሜ ክልል ይሸፍናል? " በማለት የመወያያ ጥያቄ ሰነዘረ። ከሁለቱም ፆታዎች ሀሳብ ተሰነዘረ።

ተወያይ1፡- ወጣት የሚባለው አምራች ሀይል የሆነው የህብረተሰብ ክፍል ሲሆን ከ15-49 ዓመት ያለውን ይሸፍናል።

ተወያይ2፡- የወጣትነት ዕድሜ ከ15-49 ዓመት ያለውን የዕድሜ ክልል ይሸፍናል። ከ49ዓመት በላይ ያለው ወደ አዛውንት የሚጠጋ ነው።

አወያይ፡- የወጣትነት ዘመን ከ18-49 ያለውን የዕድሜ ክልል ይሸፍናል በሚለው እንስማማ። በወጣትነት ዘመን (በጥንካሬ ወይም በድክመት) የሚያጋጥሙን ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ተወያይ3፡- በትምህርትና በስራ ላይ መገኘታችን በጠንካራ ጎን ሊጠቀስ ይችላል።

ተወያይ4፡- በወጣትነት ዘመናችን ጥሩ ደረጃ ላይ ለመድረስ ጠንክረን መስራት ይጠበቅብናል። ጥሩ ደረጃ ለመድረስ በምናደርገው ጉዞ ችግር ሊገጥመን ይችላል፡ ፡ ችግሩን ግን ተቋቁመን ማለፍ አለብን። ብዙዎቻችን ለሚያጋጥሙን ችግሮች አማራጭ መኖሩን ሳናውቅ እንችላለን። ስለዚህ ለችግሮቻችን አማራጮች እንዳሉ አውቀን ጠቃሚውን መንገድ መምረጥ ይኖርብናል።

ተወያይ 5፡- በትምህርት ላይ ሆነን ግባችንን ለማሳካት ጥረት እያደረግን ነው። ስለዚህ የወደፊት ራዕያችንን ለማሳካት የምናደርገው ጥረት ጥንካሬያችንን ያሳያል። በሌላ በኩል አጉል ዕድሜ (Fire age) ላይ በመሆናችን የሚጠቅሙን የሚመስሉን ግን የሚያታልሉንና የሚያዘናጉን ነገሮች አሉ። እንደነዚህ አይነት መሰናክሎችን በትዕግስት ካልተወጣን ድክመት ነው። ስለዚህ ወደአልፈለግነው ነገር ውስጥ ከሚያስገቡ ነገሮች መጠንቀቅ አለብን።

አወያይ፡- በእኔ እምነት ከ18-49ባለው ዕድሜ የሚገኝ የህብረተሰብ ክፍል ድክመት ቢታይበትም በርካታ ጠንካራ ጎኖች አሉት፤ እስኪ እናብራራቸው።

ተወያይ6፡- በአቅማችን መስራት የሚገባንን ከሰራን ጥንካሬያችንን ያሳያል።

ተወያይ7፡- ወጣት አምራች ሀይል ነው። መማር ፣ መስራት የሚችል ሀይል ነው ወጣቱ። "ዛሬ ያልቋጠሩት ለነገ አይሆንም" እንዲሉ ዛሬ የሰራነው ጥሩ ነገር ጉልበት እየደከመ ሲሄድ ለራሳችን ከዚያም ለአገራችን ስለሚጠቅመን በርትተን የምንሰራበት ጊዜ ነው። ስለዚህ በወጣትነት ዘመን ያልሰራነው ነገ ሊገኝ ስለማይችል ህይወታችንን ለመለወጥ፣ ለተተኪው ትውልድ አርአያ ለመሆን ጥሩ ነገር ሰርተን የምናልፍበት ዘመን ነው ወጣትነት። እናም በወጣትነት ዘመናችን በርካታ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉን ሁሉ ጥሩ የሚመስሉን ግን የሚያዘናጉን ስላሉ እነሱን በትዕግስት ማለፍ ይኖርብናል።

አወያይ፡- እንደተባለው ከ18-49 ያለው ሀይል አምራች ሀይል ነው። በወጣትነት ዘመናችን ካልሰራን ኋላ ንቆጫለን። እስኪ የአቻ ጓደኛ ግፊት በሚለው ላይ አስተያየት እንስጥበት።

ተወያይ 8 ፡-ወደ አልተፈለገ ነገር መሄድ አይኖርብንም ፣ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን (ለእኛ የሚጠቅመንን) ብቻ ማድረግ አለብን።

ተወያይ9 ፡-የወጣትነታችንን ዘመን በትምህርት ፣ በስራ ማሳለፍ አለብን ፣ ለኋላው ጊዜያችን ስለሚጠቅመን።

ተወያይ 10 ፡- ይህ የህብረተሰብ ክፍል አምራች ሀይል ነው። እስከ 30ዎቹ ባሉት ዓታት የምንማርበት ነው። እናም በትምህርት ላይ እያለን ፍቅር ዓለም ውስጥ መግባት የለብንም። ፍቅር ከያዘን ትምህርታችንን መከታተል እንቸገራለን። ከቤተሰብ ጋር ልንጋጭ እንችላለን። ስለዚህ እንደነዚህ ካሉ ነገሮች ራሳችንን መቆጠብ አለብን።

ተወያይ 11፡- የአቻ ጓደኛ ግፊት ጥሩ ወይም መጥፎ ሊሆን የሚችል ሲሆን ከተመሳሳይ ወይም ከተቃራኒ ጾታ ሊመጣ ይችላል። በትምህርት መረዳዳት ማለትም አብሮ ማጥናት ፣ መጠያየቅ ጥሩ ጎኑ ሲሆን ወደ አልባሌ ነገር መገፋፋት ደግሞ መጥፎ ጎኑ ነው። ስለዚህ የአቻ ጓደኛ ግፊት ቀስ በቀስ ወደ መልካም ነገር ወይም ወደ መጥፎ ነገር ሊመራ ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

የተለያዩ ሀሳቦች ከተማሪዎች ተሰንዝሮ እንዳበቃ አወያዩ ሰፋ ያለ ሀሳብ ከሰጠ በኋላ" መሆን እፈልጋለሁ ሳይሆን መሆን አለብኝ "የሚል ቁርጠኛ አላማ ሰንቀን ትምህርታችንን መማር ከኛ ይጠበቃል። ለዚህም የተማሪ ባህርያትን ተላብሰን መገኘት አለብን በማለት ውይይቱን አጠቃሎ ለቃለ - ጉባኤ ያዥዋ መድረኩን ለቀቀ። እሷም በበኩሏ "ወደ አዘናጊ ነገሮች የሚገፋፉ ነገሮችን በትዕግስት ማለፍ አስፈላጊ" መሆኑን በማሳሰብ መድረኩን ለመምህሯ ለቀቀች።

በመጨረሻም መምህሯ ውይይቱ የመጀመሪያ በመሆኑ አብዛኛው ተማሪ መሳተፍ ባይችልም ጠቃሚ ሀሳቦች እንደተነሱ ጠቅሰው ውይይቱን በመምራት ፡ ቃለ ጉባኤ በመያዝና በውይይቱ የተሳተፉ ተማሪዎችን አመስግነው ውይይቱ ለ35 ደቂቃ ያህል ሞቅ ደመቅ ባለ ሁኔታ ተከናውኖ ተጠናቀቀ።

## ❖ ናሙና ሶስት

የትምህርት ቤቱ ስም ፡- አንድነት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት

ምልከታ የተደረገበት ቀን ፡- 22/03/2003

ምልከታ የተደረገበት ክፍል 7D

ምልከታው የተደረገበት ሰዓት ፡- 7:10 - 7:50

በምልከታው ወቅት ይሰጥ የነበረው ርዕስ ፡- ክርክር

መምህሩ ወደ ክፍል እንደገቡ ተማሪዎች ተነሱ። መምህሩም ለተማሪዎች ሰላምታ አቀርበው እንዲቀመጡ ካደረጉ በኃላ ተከራካሪዎች እና ዳኞች ወደ ጥቁር ሰሌዳው ወጥተው ከተማሪዎች ፊት ለፊት ቦታ ቦታቸውን እንዲይዙ አደረጉ። ቀጥለውም የመከራከሪያ ርዕሱን፣ ተከራካሪዎች የሚደግፉትንና የሚቃወሙትን ርዕስ ጉዳይ እንዲሁም ዳኞችን አስተዋውቀው መድረኩን ከሶስቱ ዳኞች መካከል የውይይቱ መሪ ለሆነው ተማሪ ለቀቁ።

መድረኩን በመሪነትም በዳኝነትም የሚመራው ተማሪ የዕለቱ የመከራከሪያ ርዕስ **"ከገጠር ኑሮ የከተማ ኑሮ ይሻላል"** የሚል እንደሆነ አስተዋውቆ ለእያንዳንዱ ተከራካሪ ሁለት ሁለት ደቂቃ እንደተሰጠ ገለጠ። ከዚያም በመጀመሪያ የገጠር ኑሮን የሚደግፉትን ፣ ቀጥሎም የከተማ ኑሮ ይሻላል ብለው የሚከራከሩት ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ አደረገ ። ትውውቅ ከተደረገ በኂላ ክርክርን እያጠናቀቁ በመሄድ ስልት **"ከገጠር ኑሮ የከተማ ኑሮ ይሻላል?"** የሚሉት ወገኖች ተከራከሩ።

ተከራካሪ 1፡- ከተማ ለኑሮ ተስማሚ ነው። ችግር ቢገጥመን ችግራችንን ቶሎ የምንፈታበት ቦታ ነው። ለምሳሌ የጤና ችግር ቢገጥመን ተሽከርካሪ እንደልብ ስለሚገኝ ወደ ህክምና ቦታ ቶሎ እንደርሳለን።

ተከራካሪ2፡- በከተማ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ የተስፋፋ ነው። የመብራትና የውሃ አገልግሎት እንደልብ ይገኛል። የስልክ ፣ የጋዜጣ ፣ አገልግሎትም በከተማ ይገኛሉ። ሆስፒታሎች ስለተስፋፉ የመሞት እድል ከገጠር አኳያ ሲታይ

ዝቅተኛ ነው። የትምህርት እድል ከገጠር በተሻለ ሁኔታ በከተማ ይገኛል። ኢንዱስትሪዎች በከተማ ስለሚተከሉ የስራ እድል ይኖራል።

ተከራካሪ 3፡- በከተማ እንደገጠር የመብራት ፣ የውሃ አገልግሎት ችግር የለም። በከተማ የሚኖሩ ተማሪዎች የመብራት ችግር ስለሌለ እንደልባቸው ያጠናሉ። የገጠር ተማሪዎች ግን እንደልብ ማጥናት አይችሉም። የህክምና መስጫ ተቋሞች በከተማ ስለተስፋፉ የጤና ችግር አይኖርም። ከተማ የስልጣኔ ምንጭ ነው። የተለያዩ ቅርሶች ተጠብቀው የሚገኙት በከተማ ነው።

ተከራካሪ 4፡- የከተማ ነዋሪ እንደገጠር የኢንፎርሜሽን ችግር የለበትም። በኢንተርኔት ፣ በኢሜል ፣ በቴሌቪዥን የተለያዩ መረጃዎችን ያገኛል። በከተማ ዩኒቨርሲቲዎች ፣ ኮሌጆች ፣ የሁለተኛና የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ስለሚገኙ የትምህርት እድል ይገኛል። ጭስ አልባ የምግብ ማብሰያ መሣሪያዎች ለምሳሌ የኤሌክትሪክ ማብሰያዎች በከተማ ይገኛሉ። መሣሪያዎቹ ጭስ ስለሌላቸው ፊት አያበላሹም። የአየር ብክለትም አይኖርም። የጤና፣ የባንክ አገልግሎት በከተማ ይገኛል። ስለዚህ ከተማ ለኑሮ አመቺ ነው። ከተማ ለሴቶች ኑሮ አመቺ ነው። ትምህርት ቤቶች በየቅርብ ርቀት ስለሚገኙና ሴቶች ርቀው ስለማይጓዙ ለጥቃት አይጋለጡም። ስለዚህ ሴቶች በነጻነት ይኖራሉ።

ዳኛ፡- ሰዓት አልቋል። አሁን ደግሞ **"ከከተማ በገጠር መኖር ይሻላል"** የሚሉት ተከራካሪዎች ክርክራቸውን ያቀርባሉ።

ተከራካሪ1፡- የገጠር ነዋሪ የተለያዩ ሰብሎችን በማምረት ይጠቀማል ፤ የከተማ ግን ማምረት አይችልም።

ተከራካሪ2፡- በከተማ የተለያየ የመሰረተ ልማት ቢኖርም ለልማቱ የሚሆነው ጥሬ እቃ የሚገኘው ከገጠር ነው። ለምሳሌ ትምህርት ቤት መገንባት ቢፈለግ እንጨት ያስፈልጋል። እንጨቱ የሚገኘው ከገጠር ነው። ፋብሪካ በከተማ ቢገነባም (ለምሳሌ የወረቀት ፋብሪካ) ጥሬ ዕቃው ከገጠር ካልተገኘ መገንባቱ ብቻ ትርጉም የለውም። ስለዚህ ለፋብሪካ ውጤቶች ግብዓት ከገጠር ካልተገኘ የተገነቡት ፋብሪካዎች ቀጥ ነው የሚሉት። የከተማ ህዝብ የዕለት ምግቡን የሚያገኘው የገጠሩ ህዝብ ከሚያመርተው ነው። በተጨማሪም የገጠሩ ህዝብ የተለያዩ እንስሳትን በማርባት ከእነሱ ጥቅም ያገኛል። የተረፈውን ለከተማ

ህዝብ ይሸጣል። ስለዚህ የገጠር ህዝብ ባይኖር የከተማ ህዝብ ለኑሮ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን ሊያገኝ አይችልም።

ተከራካሪ 3:- የገጠር አኗኗር እንደከተማ የተጨናነቀ አይደለም። በገጠር ቤቶች ተራርቀው ስለሚኖሩ ፣ ንጹህ አየር ያገኛል። የኢንዱስትሪ ጭስ ስለሌለ አየሩ ንጹህ ነው።

ተከራካሪ 4:- የገጠር ቤቶች ራቅ ራቅ ብለው ስለሚሰሩ የአየር መበከል የለም። በተጨማሪም ዛፎች ስለ አሉ የአየር ብክለት የለም። ነዋሪው የተለያዩ ሰብሎችን በማምረት ራሱን መመገብ ይችላል። በከተማ የሚኖር ግን አምርቶ ራሱን መመገብ አይችልም። በገጠር የሚኖር ህዝብ የመተባበር ባህል ስላለው አንድ ነገር ለመስራት የሰው ሀይል ችግር አይገጥመውም።

ዳኛ:- አሁን የማጠቃለያ ሀሳብ የሚቀርብበት ጊዜ ስለሆነ በቅድሚያ **ከተማን የምትደግፉ** እድሉን ተሰጥቷቹኋል።

- የገጠር ሰው የቤት መስሪያ የሚሆኑ ነገሮችን ቆርቆሮ ፣ ቢስማር ፣ የሚያገኘው ከከተማ ነው። ማዳበሪያ የሚመረተውም በከተማ ነው። ስለዚህ የገጠር ሰው እነዚህን ነገሮችን ካላገኘ ቤት መስራትም ሆነ ማምረት አይችልም፡ ፡ በከተማ የአየር መበከል የለም ፤ በኤሌክትሪክ በሚሰሩ ምድጃዎች ስለሚጠቀም። የቆሻሻ አወጋገድ ትምህርት ነዋሪው ስለሚያውቅም የአካባቢ ብክለት የለም። የግል ንጽህና አጠባበቅ ግንዛቤም ስለአለው ጤንነቱ የተጠበቀ ነው።

ዳኛ:- ሰዓት አልቋል። **ገጠርን የምትደግፉ** የማጠቃለያ ሀሳብ እንድትሰጡ እድሉ ተሰጥቷችኋል።

- የተለያዩ ማዕድኖች ፣ ሌሎች ጥሬ እቃዎች የሚገኙት በገጠር ነው። ስለዚህ ፋብሪካዎች በከተማ ቢገነቡም ያለጥሬ እቃ ተገትረው ነው የሚቀሩት። የገጠር ነዋሪ ማሳውን አርሶ የተለያዩ ሰብሎችን ስለሚያመርት ፣ እንስሳትን ስለሚያረባና አድልቦ ስለሚሸጥ ስራ አጥነት የለም። የከተማ ነዋሪ ግን ተምሮ የመንግስት ስራ ጠባቂ ነው። በገጠር የአየር ብክለት ስለሌለ የጤና ችግር የለም ፤ የከተማ ነዋሪ ግን በአየር ብክለት ምክንያት ጤናው ይታወካል።

ተከራካሪዎች በዚህ መልክ ለ25 ደቂቃ ያህል ክርክራቸውን አቅርበው እንደጨረሱ መምህሩ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን የክርክር መመሪያ መሠረት በማድረግ በቀረበው ክርክር ላይ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡ አደረጉ። አስተያየት ሰጪዎቹም በተከራካሪዎች የሰዓት አጠቃቀም ችግር እንደታየ፣ በዳኞች በኩል ደግሞ ከአንዱ በስተቀር ሁለቱ ማስታወሻ ሲይዙ እንዳልታዩና የዳኝነት ሚናቸውን በአግባቡ ይወጣሉ የሚል እምነት እንደሌላቸው ሁለት ሴት ተማሪዎች ተችተዋል። ከሁለቱ ተማሪዎች አስተያየት በኋላ መምህሩ በክርክሩ ዙሪያ የተወሰኑ ጥያቄዎችን በማንሳት ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡ አድርገው የእለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ።።

## አባሪ ሶስት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ፋካልቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የመናገር ክሂል አቀራረብ ለመፈተሽ የተዘጋጀ የጽሁፍ መጠይቅ፡፡

**ውድ ተማሪዎች**

ይህ መጠይቅ በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ እንዴት እያቀረቡ እንዳሉ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው ፡፡

ስለሆነም የምትሰጡት ምላሽ ለጥናቱ በመረጃ ግብአትነት የላቀ ድርሻ ስላለው ትክክለኛውን መልስ በመስጠት ትተባበሩኝ ዘንድ እየጠየቅሁ ለምታደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

**ክፍል አንድ፡-**

**አጠቃላይ መረጃ**

- የትምህርት ቤቱ ስም ...........................
- ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት የከተማ አስተዳደር ............
- የተማሪው የክፍል ደረጃ ............
- ዕድሜ ........ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ....................
- ፆታ ☐ ወንድ ☐ ሴት

**ክፍል ሁለት**

**መመሪያ አንድ፡-**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያለህን/ሽን አመለካከት በትክክል ያመለክታል የምትለውን/ይውን ሀሳብ በቀኝ በኩል ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንዱን በመምረጥ የ ☑ ምልክት በማድረግ አመልክት/ች፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | መወሰን ያቅተኛል | አልስማማም |
| 1 | መምህሩ/ሯ/ የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት በተለያዩ መንገዶች ያነቃቃሉ፡፡ | | | |
| 2 | የመናገር ክሂል ተግባራትን ከመጀመራችን በፊት መምህሩ/ሯ/ አጭርና ግልጽ መመሪያ ይሰጣሉ፡፡ | | | |
| 3 | በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት ፣ ክፍሉ በአንድነት በመሆን ወዘተ. የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ እለማመዳለሁ፡፡ | | | |
| 4 | መምህሩ/ሯ/ በግል በጥንድ፣ በሶስትዮሽ ፣ በቡድን ወዘተ. የመናገር ክሂል ተግባራትን ሲያሰሩ አፈፃፀማችንን እየተዘዋወሩ በመከታተል ያበረታታሉ፡፡ | | | |
| 5 | በክፍል ውስጥ ሪፖርት፣ ጭውውት ፣ ክርክር፣ ውይይት ወዘተ. ማቅረቤ የመናገር ችሎታዬ እንዲያድግ ረድቶኛ፡፡ | | | |
| 6 | በጥንድ፣ በቡድን ወዘተ በመሆን የመናገር ክሂል ተግባራትን መስራቱ እና መከታተሌ የንግግር ፣ የጭውውት ፣ የክርክር የውይይት ስርዓትን እንዳውቅ ረድቶኛል፡፡ | | | |
| 7 | በጥንድ ፣ በቡድን ወዘተ. በመሆን ቃለ መጠይቅ መደራረግ ፣ ስዕላዊ መግለጫዎች በሚያስላልፉት ሀሳብ ላይ መወያየትና መከራከር ወዘተ ሀሳቤን ያለፍርሃት እንድገልጽ ረድቶኛል፡፡ | | | |
| 8 | የጭውውት ፣ የክርክር ፣ የውይይት ወዘተ ተግባራት በክፍል ውስጥ ከቀረበ በኋላ አስተያየት እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 9 | መምህሩ/ሯ/ ስህተታችንን በቀጥታ ከመናገር ይልቅ ርስበርስ እንድንተራረም ያደርጋሉ፡፡ | | | |
| 10 | በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የመናገር ክሂል ተግባራት ከህይወት ልምዴ ጋር የተቆራኙ ናቸው | | | |

መመሪያ ሁለት ፡-

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በሳጥኑ ላይ የ / ✓/ ምልክት በማድረግ**

**መልስን/ሽን አመልክት/ቺ፡፡**

11. በመናገር ክሂል ተግባራት ክንውን ወቅት ክፍለ ጊዜው አብዛኛውን ጊዜ

☐ በመምህሩ ንግግር ብቻ ይሸፈናል

☐ በተማሪዎች የእርስ በርስ መስተጋብር / ንግግር/ ይሸፈናል

☐ በመምህሩና በተማሪዎች አቻዊ /እኩል/ መስተጋብር ይሸፈናል፡፡

12. የመናገር ክሂልን /ሽን ለማሳደግ በ7ኛ ክፍል በግል ፣ በጥንድ ፣በቡድን ወዘተ. በመሆን ሪፓርት ፣ ጥውውት ፣ ክርክር ፣ ውይይት ወዘተ. አቅርበህ/ሽ ታውቃለህ/ቂያለሽ ?

☐ አዎ ☐ የለም

13. በተራ ቁጥር "12" ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ " የለም " ከሆነ ምክንያትህ/ሽ ምንድነው ?

☐ ዕድሉን አግኝቼ ስለማሳወቅ

☐ ንግግሬ የሌሎችን ስሜት አይስብም በሚል እምነት ትችትን ስለምፈራ

☐ በተሰጠው ርዕሰ ዙሪያ በቂ መረጃ ስለሌለኝ ባለመሳተፌ

☐ መምህሩ በማበረታታት ፈንታ ሞራሌን ስለሚነኩኝ

ሌላ ካለ ይገለጽ

..........................................................................................

..........................................................................................

## አባሪ አራት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የቋንቋዎች ተቋም ፋካልቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የመናገር ክሂል የአቀራረብ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ።

1. በሰባተኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የመናገር ክሂል መልመጃ/ ተግባር ዓይነቶችን ቢጠቅሱልኝ ? ተግባራቱ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የሚያሳድጉ ናቸው?
2. የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ምን ምን የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይገለገላሉ?
3. የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲያከናውኑ ተማሪዎችን በቡድን ያደራጃሉ?
   የሚያደራጁ ከሆነ ቡድኖችን እንዴት ያደራጃሉ ?
4. አንድ የቋንቋ መምህር የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርብ /በአቀራረብ ፣ በልምምድ ፣ በአፍልቆት ወዘተ ደረጃ /ሚናው /ተግባሩ/ ምንድነው ይላሉ?
5. ከማስተማር ልምድዎ በመነሳት የተማሪዎችን ሀሳባቸውን በንግግር የመግለጽ ብቃት እንዴት ይገመግሙታል?
6. ከተመረቁበት የትምህርት ተቋም የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የወሰዱት ኮርስ አለን? የተማሩት ኮርስ ለማስተማር ምን ያህል አግዞዎታል?
7. በስራ ላይ እያሉ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት ስልጠና ወስደዋል?
   - ሀ. ከወሰዱ መቼ ?
   - ለ. ስልጠናው ለስራዎ ምን ያህል አግዞዎታል?
8. የመናገር ክሂልንን እንደመፃፍ ፣ ማንበብ ፣ ማዳመጥ ክሂሎች በክፍል ውስጥ ፈትነው ያውቃሉ?
   - ሀ. ፈትነው የሚያውቁ ከሆነ አተገባበሩን ቢገልጹልኝ?
   - ለ. ፈትነው የማያውቁ ከሆነ ችግሩ ምንድነው ይላሉ?
9. ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር እንዳይገልፁ የሚያደርጉ ችግሮች ምን ምን ናቸው?
10. ችግሮቹ ለመፍታት ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

*ጊዜዎንና ጉልበትዎን መስዋእት በማድረግ ለሰጡኝ መረጃ አመሰግናለሁ።*

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስምና ፊርማዬን ያስፈርኩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ፋካልቲ በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር የትምህርት መስክ የድኅረ ምረቃ ተማሪ፣ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የራሴ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸውን ዋቢዎች በሙሉ የጠቀስኳቸው በትክክል መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም እጅጉ ይማም

ፊርማ ……………………

አድራሻ ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋካልቲ

አዲስ አበባ